# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት

## የ1994 በጀት ዓመት የፌዴራል ዋናው ኦዲተር
## የልዩ ልዩ መንግሥት መ/ቤቶች ኦዲት
## ዓመታዊ ሪፖርት

**ክፍል 2**

**ሰኔ 1995**
**አዲስ አበባ**

# የ1994 በጀት ዓመት የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት
# የልዩ ልዩ መንግሥት መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርት ማውጫ


ገጽ

1. መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

2. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች

2.1 የጉምሩክ ባለሥልጣን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

2.1.1 የባላሥልጣኑ ዋና መ/ቤት

2.1.2 የአ.አ ላጋር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

2.1.3 የአ.አ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

2.1.4 የናዝሬት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

2.2 የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

2.2.1 የባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት

2.2.2 የናዝሬት ቅ/ጽ/ቤት

2.2.3 የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት

2.2.4 የሰሜን ምዕራብ ቅርንጫፍ

2.2.5 የፌዴራል ግብር ይግባኝ ኮሚስዮን ጽ/ቤት

2.2.6 የገቢዎች ሚኒስቴር

2.3 የኢኮኖሚ አገልግሎት ዘርፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

2.3.1 የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈጻሚ ጽ/ቤት

2.3.2 የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ባለሥልጣን

2.3.3 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ

2.3.4 የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር

2.3.5 የብሔራዊ ዕጽዋት ዘር ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ

2.3.6 የብሔራዊ ሚቴዎሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት

2.3.7 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

2.3.8 የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ

2.3.9 የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ደርጅት

2.4 የማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

2.4.1 የአምቦ እርሻ ኮሌጅ

2.4.2 የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን መደበኛ በጀት

2.4.3 የባህርዳር ዩኒቨርስቲ ኢንጂነሪንግ ፋክልቲ

2.4.4 የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ

2.4.5 የአማኑኤል ሆስፒታል

2.4.6 የመቀሌ ቢዝነስ ኮሌጅ

2.4.7 የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ

2.4.8 እድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት

2.4.9 የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

2.4.10 የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን

የ1992 በጀት ዓመት የጡረታ ፈንድ ሂሣብ

2.5 <u>የአስተዳደር አገልግሎት ዘርፍ</u> . . . . . . . . .. . . . . . . . . .. . . . .

2.5.1 የመከላከያ ሚኒስቴር ፋይናንስ መምሪያ

2.5.2 የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ

2.5.3 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

2.5.4 የሕዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ም/ቤቶች የኦዲዮቪዡዋል ዕቃዎች ግዥ

2.5.5 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት

2.5.6 የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት

2.5.7 የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያ

- የዋና ገንዘብ ያዥ የሣጥን ሂሣብ
- የ110ኛ ኮር
- የ107ኛ ኮር

2.5.8 የፍትህ ሚኒስቴር አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት

2.5.9 ጋፋት ኢንጂነሪንግ ፋብሪካ

2.6 <u>የጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ</u> . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

2.6.1 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር

2.6.2 የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

2.6.3 የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን

2.6.4 የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

2.6.5 የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

2.6.6 በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲኘሎማቲክ ሚስዮን ሂሣብ

2.7 የድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
2.7.1 የካውንስሉ የጤና ጽ/ቤት
2.7.2 " የግብርና ጽ/ቤት
2.7.3 " የፋይናንስ ጽ/ቤት
3. የክልል መንግሥታት የድጎማ ሂሣብ
3.1 የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት . . . . . . . . . . . . . . . .
3.1.1 የጤና ቢሮ
3.1.2 የትምህርት ቢሮ
3.1.3 የእንስሳትና እርሻ ልማት ቢሮ
3.2 የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት . . . . . . . . . . . . . . . . .
3.2.1 የክልሉ ግብርና ቢሮ
3.2.2 የክልሉ ጤና ቢሮ
3.2.3 የሰሜን ሸዋ ግብርና መምሪያ
3.2.4 የደቡብ ወሎ ግብርና መምሪያ
3.2.5 የደቡብ ወሎ ጤና መምሪያ
3.2.6 የሰሜን ጎንደር ጤና መምሪያ
3.2.7 የሰሜን ጎንደር ገንዘብ መምሪያ
3.2.8 የምሥራቅ ጎጃም ገንዘብ መምሪያ
3.3 የሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት . . . . . . . . . . . . . . . . .
3.3.1 የክልሉ ጤና ቢሮ
3.3.2 " ትምህርት ቢሮ
3.4 የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት . . . . . . . . . . .
3.4.1 የክልሉ የጤና ቢሮ
3.4.2 " የውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ
3.4.3 በፋይናንስ ቢሮ የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት
3.4.4 የትምህርትና ባህል ቢሮ
3.5 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት . . .. . . . . . .
3.5.1 የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ

3.5.2 የትምህርት ቢሮ
3.5.3 የከምባታና ጠምባሮ ዞን ትምህርት መምሪያ
3.5.4 የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መምሪያ
3.5.5 የሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ
3.5.6 የጌዲኦ ዞን ጤና መምሪያ
3.5.7 የከምባታና ጠምባሮ ዞን ጤና መምሪያ
3.5.8 የጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ
3.5.9 የወላይታ ዞን ግብርና መምሪያ
3.5.10 የጌዲኦ ዞን ግብርና መምሪያ
3.5.11 የሀዲያ ዞን ግብርና መምሪያ

3.6 <u>የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት</u> . . . . . . . . . . . . . .
3.6.1 የውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ
3.6.2 የግብርና ልማት ቢሮ
3.6.3 የጤና ቢሮ
3.6.4 የትምህርትና ባህል ቢሮ

3.7 <u>የሐረሪ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት</u>
3.7.1 የክልሉ ትምህርት ቢሮ
3.7.2 " ጤና ቢሮ
3.7.3 " የፋይናንስ ቢሮ

# የ1994 በጀት ዓመት

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር ዓመታዊ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በአዋጅ ቁጥር 68/1989 አንቀጽ 8/2 መሠረት በተላከልን የ1992 በጀት ዓመት የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ላይ ያለንን አስተያየት በክፍል አንድ ባቀረብነው ሪፖርት ተገልጿል፡፡

በዚህ ሪፖርት ደግሞ ከመንግሥት በሚመደብላቸው በጀት በሚተዳደሩ መ/ቤቶችና በአንዳንድ ልዩ ሂሳቦች ላይ በተደረገው የፋይናንስ ኦዲት የተገኙ ውጤቶች በየአገልግሎት ዘርፍ በፌዴራል ገቢዎች፣ በአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት፣ በኢኮኖሚና ሶሻል አገልግሎት እንዲሁም በክልል መንግስታት በመለየት ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

## 2. ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ የገንዘብና የአሠራር ጉድለቶች

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች በርካታ የገንዘብና የአሠራር ጉድለቶች ተገኝተዋል፡፡ እነዚህ ጉድለቶች ከገጽ 27 ጀምሮ በየአገልግሎት ዘርፉ መ/ቤቶችን በመለየት የተገለጹ ሲሆን ጎላ ብለው የታዩት ችግሮች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

### 2.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ፣

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| በፌዴራል መ/ቤቶች | ብር | 75350.04 |
| በክልል መንግሥታት | ብር | 5969.98 |
| በድምሩ | ብር | 81320.02 |

ከዚህ ውስጥ ከብር 1,000.00 በላይ ጉድለት የተገኘባቸው መ/ቤቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

ሀ/ የፌዴራል መንግሥት

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት | 1274.99 |
| 2 | የኢትዩጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | 1371.68 |
| 3 | የድሬዳዋ ካውንስል ግብርና ጽ/ቤት | 2283.61 |
| 4 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ | 2810.04 |
| 5 | በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን | 2934.10 |
| 6 | አዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ | 3938.06 |
| 7 | የድሬዳዋ ካውንስል ፋይናንስ ጽ/ቤት | 4277.30 |
| 8 | የባህርዳር ዩቨርሲቲ ኢንጂነሪንግ ፋኩልቲ | 6647.58 |
| 9 | የማዕከላዊ ስታቲክስ ባለሥልጣን | 7934.92 |
| 10 | የጋፋት ኢንጂነሪንግ ፋብሪካ | 10314.44 |
| 11 | የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን (ዋናው መ/ቤት) | 10668.38 |
| 12 | የፍትህ ሚኒስቴር | 17500.74 |
| | ድምር | 71955.84 |

ለ/ በክልል መንግሥታት

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ጤና ቢሮ | 1194.57 |
| 2 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | 1366.38 |
| 3 | የጋምቤላ ክልል ውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | 2468.65 |
| | ድምር | 5029.60 |

ከተጠቀሰው የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ውስጥ አንዳንድ መ/ቤቶች በኦዲቱ ወቅት ሌሎች ደግሞ ከኦዲቱ በኋላ የተኩ መሆናቸውን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

2.1 የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ማመዛዘን ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች

በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት የፌዴራል የክልል መንግሥታት መ/ቤቶች ውስጥ በ27 መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ማመዛዘን ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ለማመዛዘን ያላስቻሉት ጎላ ጎላ ያሉ የአሠራር ድክመቶች ዝርዝር ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

ምዝገባ በአግባቡ ተከናውኖ ከወጪ ቀሪ ለተከታዩ ወር የማይዞር በመሆኑ፣

- የሚመለከታቸው ሠራተኞችና ኃላፊዎች በወር አንድ ጊዜ የመዝገብ ከወጪ ቀሪ ትክክል መሆኑን በማረጋገጥ የማይፈራረሙ በመሆኑ፣
- ርክክብ በአግባቡ ባለመፈጸሙ ገንዘብ ያዥዎች ሥራ የጀመሩበትንና ያንቀሳቀሱትን ሂሣብ ለመለየት አስቸጋሪ በመሆኑ፣
- የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥ፣ የገቢው ትክክለኛነት ሳይረጋገጥና የገቢው ዓይነት ሳይለይ በወሩ መጨረሻ የወሩ ገቢ በድምር የሚመዘገብ በመሆኑ፣
- ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የተደረገ ሂሣብ በወጪ ባለመመዝገቡ በመዝገብ የተመለከተው ከወጪ ቀሪው ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ባለመቻሉ፣
- የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ መዝገብ የገቢና የወጪ ድምር በእርሳስ የተፃፈ በመሆኑ፣

የመ/ቤቶቹን የጥሬ ገንዘብ ሃሳብ ኦዲት ለማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በመሆኑም መ/ቤቶቹ የሚመለከታቸውን ድክመት በመለየት አሰራሩ መታረም እንዳለበት በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ቢሆንም ከክልል መንግሥታት በአብዛኛው ሪፖርቱ ምላሽ ያልተሰጠ በመሆኑ የተወሰደውን እርምጃ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ የመ/ቤቶቹም ዝርዝር:-

ሀ/ በፌዴራል መንግሥት

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ስም |
|---|---|
| 1 | የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ |
| 2 | የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን |
| 3 | የናዝሬት ጉምሩክ ጽ/ቤት |
| 4 | የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን |
| 5 | የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር |
| 6 | የባህርዳር አገር ውስጥ ገቢ ቅ/ጽ/ቤት |
| 7 | የድሬዳዋ አገር ውስጥ ገቢ ቅ/ጽ/ቤት |

ለ/ በክልል መንግሥታት

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ስም |
|---|---|
| 1 | የሐረሪ ትምህርት ቢሮ |
| 2 | የሐረሪ ጤና ቢሮ |
| 3 | የሐረሪ ፋይናንስ ቢሮ የበጀት መምሪያ |
| 4 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ፋይናንስ ቢሮ |
| 5 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ትምህርትና ባህል ቢሮ |
| 6 | የደቡብ ሕዝቦች ትምህርት ቢሮ |
| 7 | የጌዲኦ ዞን ጤና መምሪያ |
| 8 | የወላይታ ዞን ግብርና መምሪያ |
| 9 | የጌድኦ ዞን ግብርና መምሪያ |
| 10 | የሐዲያ ዞን ግብርና መምሪያ |
| 11 | የከምባታና ጠምባሮ ዞን ጤና መምሪያ |
| 12 | የሐዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ |
| 13 | የጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ |
| 14 | የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መምሪያ |
| 15 | የደቡብ ሕዝቦች ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ |
| 16 | የአፋር የእንስሳትና እርሻ ልማት ቢሮ |
| 17 | የአፋር ጤና ቢሮ |
| 18 | የጋምቤላ ግብርና ቢሮ |
| 19 | የጋምቤላ ጤና ቢሮ |
| 20 | የጋምቤላ ትምህርት ቢሮ |

2.3 <u>በካዝና ተገኝቶ ስለተቆጠረው ጥሬ ገንዘብ</u>

ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ 23 መ/ቤቶች በመመሪያ ከተፈቀደው ብር 5000.00 በላይ በካዝና የተቀመጠ ጥሬ ገንዘብ:-

| | | |
|---|---|---|
| በፌዴራል መንግሥት | ብር | 871410.42 |
| በክልል መንግሥታት | ብር | <u>306832.25</u> |
| በድምሩ | ብር | <u>1178242.67</u> ተገኝቷል:: |

ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል::

ሀ/ በፌዴራል መንግሥት

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የድሬዳዋ ግብርና ጽ/ቤት | 5843.00 |
| 2 | የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | 8172.80 |
| 3 | የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት | 8682.32 |
| 4 | ጋፋት ኢንጅነሪንግ ፋብሪካ | 9132.80 |
| 5 | የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን | 10889.40 |
| 6 | ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 12588.00 |
| 7 | የ107ኛ ኮር | 12675.12 |
| 8 | የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት | 14015.12 |
| 9 | ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ኢንጅነሪንግ ፋኩልቲ | 19033.01 |
| 10 | የአማኑኤል ሆስፒታል | 32880.00 |
| 11 | የድሬዳዋ ፋይናንስ ጽ/ቤት | 45718.20 |
| 12 | የድሬዳዋ ጤና ጽ/ቤት | 47459.04 |
| 13 | የማዕከላዊ ስታቲስትክ ባለሥልጣን | 156111.87 |
| 14 | ፍትህ ሚኒስቴር | 177447.10 |
| 15 | የአየር ኃይል ጠ/መምሪያ | 310762.64 |
| | ድምር | 871410.42 |

ለ/ በክልል መንግሥታት

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የምሥራቅ ጎጃም ዞን ገንዘብ መምሪያ | 5148.35 |
| 2 | የሰሜን ጎጃም ዞን ገንዘብ መምሪያ | 10087.33 |
| 3 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ፋይናንስ ቢሮ | 11116.32 |
| 4 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | 11284.36 |
| 5 | የጋምቤላ የውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | 17576.72 |
| 6 | የሶማሌ ትምህርት ቢሮ | 62494.53 |
| 7 | የጋምቤላ ግብርና ልማት ቢሮ | 85842.47 |
| 8 | የሶማሌ ጤና ቢሮ | 103282.17 |
| | ድምር | 306832.25 |

## 2.4 ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ

ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ

በክልል መንግሥታት ብር <u>63771047.77</u>

በፌዴራል መንግሥት ብር 565918682.11

በድምሩ ብር <u>629689729.88</u>

የሰነድ ሂሣብ ሳይወራረድ ተገኝቷል። ከዚህ ውስጥ ከብር 100000 በላይ ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል።

ሀ/ የፌዴራል መንግሥት

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | እድገት የጎልማሶች አዳሪ ትምህርት ቤት | 134734.12 |
| 2 | የድሬዳዋ ግብርና ጽ/ቤት | 236895.78 |
| 3 | ፍትህ ሚኒስቴር | 305225.18 |
| 4 | አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን | 331546.37 |
| 5 | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | 333365.96 |
| 6 | የድሬዳዋ ካውንስል ጤና ጽ/ቤት | 343842.13 |
| 7 | ጋፋት ኢንጂነሪንግ | 644510.76 |
| 8 | የድሬዳዋ ፋይናንስ ጽ/ቤት | 693289.71 |
| 9 | የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ባለሥልጣን | 741627.99 |
| 10 | አዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ | 768987.85 |
| 11 | የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን | 1198635.69 |
| 12 | የገቢዎች ሚኒስቴር | 1,339,803.52 |
| 13 | የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ | 3083546.32 |
| 14 | ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 17848121.81 |
| 15 | ማዕከላዊ ስታስቲክስ ባለሥልጣን | 19987847.63 |
| 16 | የ110ኛው ኮር | 35043741.88 |
| 17 | የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 49906484.91 |
| 18 | የ107ኛ ኮር | 59654324.73 |
| 19 | ማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን የጡረታ ፈንድ | 372686235.20 |
| | ድምር | 565282767.54 |

ለ/ በክልል መንግሥታት

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የሰሜን ጎንደር ጤና መምሪያ | 138179.55 |
| 2 | የሀዲያ ግብርና መምሪያ | 155423.78 |
| 3 | የጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ | 299746.34 |
| 4 | የአፋር ትምህርት ቢሮ | 769183.28 |
| 5 | የሐረሪ ጤና ቢሮ | 913876.26 |
| 6 | የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መምሪያ | 1676119.06 |
| 7 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | 1972275.46 |
| 8 | የአፋር እንስሳትና እርሻ ልማት ቢሮ | 2222936.08 |
| 9 | የጋምቤላ ግብርና ልማትቢሮ | 2843437.29 |
| 10 | የሱማሌ ትምህርት ቢሮ | 3021072.56 |
| 11 | የአፋር ጤና ቢሮ | 4355810.47 |
| 12 | የሱማሌ ጤና ቢሮ | 5387410.26 |
| 13 | የደቡብ ሕዝቦች ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | 5618552.63 |
| 14 | የጋምቤላ ውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | 6653178.51 |
| 15 | የአማራ ጤና ቢሮ | 13586996.02 |
| 16 | የአማራ ግብርና ቢሮ | 13680520.16 |
| | ድምር | 63294717.71 |

በደንቡ መሠረት ገንዘብ በሰነድ ወጪ መሆን የሚገባው ወዲያውኑ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደመሆኑ መጠን ገንዘቡ ለታዘዘለት ዕቃ መግዣ ወይም አገልግሎት ማስፈጸሚያ ከዋለ ሂሣቡን ለማወራረድ ችግር አይኖረውም፡፡ በሌላም በኩል ውዝፍ የሰነድ ሂሣቡ በመዝገብ ተመዝግቦ የሚያዝበት ሁኔታ አልተመቻቸም፡፡ ለመ/ቤቶች በምንልከው ሪፖርት የሰነድ ሂሣብ በደንቡ መሠረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወራረድ ያሳሰብን ቢሆንም ሁኔታው መሻሻል አላሳየም፡፡ ሂሣቡን በወቅቱ አለማወራረድ በመንግሥት ገንዘብ ላይ ጉድለት ሊያስከትል ስለሚችል በመ/ቤቶች በኩል የሚደረገው ቁጥጥር እንዲጠናከር እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

## 2.5 ተሰብሳቢ ሂሣብ

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ መሰብሰብ ይኖርባቸዋል:: ሆኖም ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ11 የፌዴራል መ/ቤቶች ብር 658296074.35 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል::

ገቢው ሳይሰበሰብ ከቀረበት ምክንያት ውስጥ በስሌትና በታሪፍ አመዳደብ ስህተት፣ መመሪያን ተግባራዊ ባለማድረግ እና ተገቢው ህጋዊ እርምጃ አለመውሰድ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ከብር 50000 በላይ ያልተሰበሰበ ሂሣብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል::

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ | 77702.11 |
| 2 | ናዝሬት ጉምሩክ | 296599.08 |
| 3 | የአገር ውስጥ ገቢ ሰሜን ምዕራብ ቅ/ጽ/ቤት | 3042004.69 |
| 4 | የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን | 3192584.76 |
| 5 | የአገር ውስጥ ገቢ ናዝሬት ቅ/ጽ/ቤት | 3703207.93 |
| 6 | የአገር ውስጥ ገቢ ድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት | 106285206.04 |
| 7 | አዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ | 118175551.53 |
| 8 | የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን | 171243376.59 |
| 9 | የአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ | 252275511.20 |
| | ድምር | 658291743.93 |

## 2.6 የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሣብ

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም የመንግሥት ገቢ በሕጋዊ ደረሰኝ መሰብሰብና መመዝገብ ያለበት ቢሆንም ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ12 መ/ቤቶች ብር 1748940.45 የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለትና በገቢ ሳይመዘገብ ተገኝቷል:: ይኸውም የፌዴራል መንግሥት ብር 1268015.10 የክልል መንግሥታት ደግሞ ብር 6480925.35 ነው::

ከዚህም ውስጥ ከብር 10000 በላይ የተገኘባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ሀ/ በፌዴራል መንግሥት

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ድርጅት | 12480.00 |
| 2 | የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | 26636.00 |
| 3 | ድሬዳዋ የሀገር ውስጥ ገቢ ቅ/ጽ/ቤት | 68311.84 |
| 4 | በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን | 130141.53 |
| 5 | የአገር ውስጥ ገቢ የሰሜን ምዕራብ ጽ/ቤት | 441960.67 |
| 6 | የማዕከላዊ ስታስቲክስ ባለሥልጣን | 585490.46 |
| | ድምር | 1265020.50 |

ለ/ በክልል መንግሥታት

| ተራ ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የከምባታ ጠምባሮ ዞን ትምህርት መምሪያ | 10154.43 |
| 2 | የወላይታ ዞን ግብርና መምሪያ | 25957.18 |
| 3 | የሶማሌ ጤና ቢሮ | 60750.39 |
| 4 | የአፋር ጤና ቢሮ | 2806430.73 |
| 5 | የሶማሌ ትምህርት ቢሮ | 3573683.22 |
| | ድምር | 6476975.95 |

## 2.7 የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት የገቢ ሂሣብ

ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ3ቱ የፋይናንስ ደንብ ከሚያዘው ውጪ የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብለት በገቢ የተመዘገበ ብር 40318035.65 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ | 9583.09 |
| 2 | አዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ | 5603377.61 |
| 3 | ማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን የጡረታ ፈንድ | 34705074.95 |
| | ድምር | 40318035.65 |

2.8 የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበላቸው እና ከመመሪያ

<u>ውጭ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>

ክፍያዎች በአግባቡ ሥልጣን በተሰጠው ኃላፊ መታዘዛቸውንና ለወጪውም የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ ወጪ የተደረገ፣

| | | |
|---|---|---|
| በክልል መንግሥታት | ብር | <u>66269400.70</u> |
| በፌዴራል መንግሥት | ብር | 95943926.23 |
| በድምሩ | ብር | <u>162213326.93</u> |

ከመመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች፣

| | | |
|---|---|---|
| በክልል መንግሥት | ብር | <u>282759.48</u> |
| በፌዴራል መንግሥት | ብር | 3301817.44 |
| በድምሩ | ብር | <u>3584576.91</u> |

**<u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ</u>**

***ሀ/ በፌዴራል መንግሥት***

| ተራ ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 26235.62 |
| 2 | የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | 33081.80 |
| 3 | የድሬዳዋ ግብርና ጽ/ቤት | 33450.80 |
| 4 | የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን | 44508.55 |
| 5 | 107ኛ ኮር | 73056.45 |
| 6 | የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት | 92194.21 |
| 7 | የድሬዳዋ ጤና ጽ/ቤት | 116251.28 |
| 8 | ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 133961.00 |
| 9 | የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት | 264854.10 |
| 10 | 110ኛ ኮር | 489151.90 |
| 11 | የአማኑኤል ሆስፒታል | 853929.21 |
| 12 | እድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት | 1081620.60 |
| 13 | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | 1406006.80 |
| 14 | በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን | 10113480.92 |
| 15 | የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን | 19251170.00 |
| 16 | የገቢዎች ሚኒስቴር | 61929377.94 |
| | ድምር | 95942331.18 |

***በክልል መንግሥታት***

| ተራ ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የጌድኦ ዞን ግብርና መምሪያ | 5369.55 |
| 2 | የሐረሪ ጤና ቢሮ | 9771.18 |
| 3 | የቤ/ጉ/ክ/ የውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | 23457.72 |
| 4 | የደቡብ ሕዝቦች ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | 29273.37 |
| 5 | የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ | 41388.88 |

| | | |
|---|---|---|
| 6 | የደቡብ ሕዝቦች ትምህርት ቢሮ | 53289.15 |
| 7 | የሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ | 72588.26 |
| 8 | የጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ | 90722.03 |
| 9 | የሰሜን ጎንደር ዞን ጤና መምሪያ | 149932.07 |
| 10 | የሰሜን ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ | 408043.70 |
| 11 | የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መምሪያ | 467654.06 |
| 12 | የአማራ ጤና ቢሮ | 485902.60 |
| 13 | የቤ/ጉ/ክ ትምህርትና ባህል ቢሮ | 1167445.78 |
| 14 | የሐረሪ ፋይናንስ ቢሮ | 1328307.60 |
| 15 | የጌዴኦ ዞን ጤና መምሪያ | 1791552.32 |
| 16 | የአማራ ግብርና ቢሮ | 2963702.34 |
| 17 | የሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብ መምሪያ | 3905525.34 |
| 18 | የአፋር እንስሳትና እርሻ ልማት ቢሮ | 4011120.78 |
| 19 | የጋምቤላ ውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | 4045626.71 |
| 20 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ጤና ቢሮ | 4951246.54 |
| 21 | የሱማሌ ጤና ቢሮ | 8132097.00 |
| 22 | የሱማሌ ትምህርት ቢሮ | 8909372.03 |
| 23 | የአፋር ትምህርት ቢሮ | 9695799.69 |
| 24 | የጋምቤላ ትምህርት ቢሮ | 13530212.00 |
| | ድምር | 66269400.70 |

ከመመሪያው ውጭ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ሀ/ በፌዴራል መንግሥት

| ተራ ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | በማዕከላዊ ስታስቲክስ ባለሥልጣን | 8962.50 |
| 2 | የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 14137.00 |
| 3 | የጋፋት ኢንጂነሪንግ ፋብሪካ | 17488.00 |
| 4 | የድሬዳዋ ግብርና ጽ/ቤት | 21331.92 |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | 22532.17 |
| 6 | 110ኛ ኮር | 32771.20 |
| 7 | ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንጂነሪንግ ፋኩልቲ | 38073.40 |
| 8 | ናዝሬት ጉምሩክ | 46728.00 |
| 9 | የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ | 56058.00 |
| 10 | የድሬዳዋ ጤና ጽ/ቤት | 84718.49 |
| 11 | የውጭ ጉዳይ ማኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን | 138554.19 |
| 12 | 107ኛ ኮር | 167953.53 |
| 13 | ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ | 457297.12 |
| 14 | አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን | 2185331.39 |
| | ድምር | 3291936.91 |

ለ/ በክልል መንግሥት

| ተራ ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት ቢሮ | 5497.33 |
| 2 | የጌዴኦ ዞን ጤና መምሪያ | 5941.70 |
| 3 | የሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ | 6050.64 |
| 4 | የአፋር እንስሳት እርሻ ልማት ቢሮ | 6273.62 |
| 5 | የከምባታና ጠምባሮ ዞን ጤና መምሪያ | 6971.91 |
| 6 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ጤና ቢሮ | 7550.76 |
| 7 | የጋምቤላ ጤና ቢሮ | 9689.45 |
| 8 | የሀዲያ ዞን ግብርና መምሪያ | 9900.50 |
| 9 | የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | 11686.05 |
| 10 | የጋሞጎፋ ዞን ጤና ቢሮ | 12391.90 |
| 11 | የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ የሥራና ከተማ ልማት ትምህርት ቢሮ | 19941.44 |
| 12 | የሰሜን ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ | 33074.85 |
| 13 | የአፋር ትምህርት ቢሮ | 33794.73 |
| 14 | የአፋር ጤና ቢሮ | 35589.08 |

| | | |
|---|---|---|
| 15 | የሐረሪ ትምህርት ቢሮ | 56824.20 |
| | ድምር | 261178.16 |

ደንብን ያልተከተሉ ግዢዎች

ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይቀርብ የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ የብር 21813479.59 ግዥዎች ተፈጽመው ተገኝተዋል፡፡

ይኸውም፣ በክልል መንግሥታት ብር 5622750.56

በፌዴራል መንግሥታት ብር 16190729.03

በድምሩ ብር 21813479.59

ሀ/ በፌዴራል መንግሥት

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| | የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | 6120.00 |
| | የመቀሌ ቢዝነስ ኮሌጅ | 26161.60 |
| | የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን | 34680.00 |
| | የድሬዳዋ ጤና ጽ/ቤት | 39481.65 |
| | የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ | 78189.28 |
| | የድሬዳዋ ግብርና ጽ/ቤት | 109236.01 |
| | የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንጅነሪንግ ፋኩልቲ | 180872.26 |
| | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | 248233.12 |
| | የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 284348.56 |
| | የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት (ኦዲዩቪዥዋል ዕቃ ግዥ) | 554000.00 |
| | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ማሲዮን | 712746.94 |
| | የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት /በጀት/ | 1049193.74 |
| | ማዕከላዊ ስታስቲክስ | 1228391.76 |

| | | |
|---|---|---|
| | የ110ኛ ኮር | 1295558.45 |
| | የ107ኛ ኮር | 3033895.12 |
| | የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 7309620.54 |
| | ድምር | 16190729.03 |

ለ/በክልል መንግሥታት

<u>ደንብና መመሪያን ሳይጠብቅ የተፈፀመ ግዥ</u>

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የጋምቤላ ግብርና ቢሮ | 3558.00 |
| 2 | የአፋር ጤና ቢሮ | 38928.91 |
| 3 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ጤና ቢሮ | 59701.78 |
| 4 | የአፋር ትምህርት ቢሮ | 131446.65 |
| 5 | የአማራ ጤና ቢሮ | 202038.10 |
| 6 | የአፋር እንስሳትና እርሻ ልማት ቢሮ | 226065.07 |
| 7 | የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ | 372299.00 |
| 8 | የሰሜን ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ | 476617.15 |
| 9 | የደቡብ ወሎ ዞን ጤና መምሪያ | 1214332.27 |
| 10 | የሰሜን ጎንደር ዞን ጤና መምሪያ | 2897763.63 |
| | ድምር | 5622750.56 |

የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት

ለተፈጸሙ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃዎች መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው የተፈጸሙ ክፍያዎች፣

በክልል መንግሥታት ብር <u>29354204.83</u>

በፌዴራል መንግሥት ብር 25104965.40፣ $119,922.97፣ BEF31,265.00

በድምሩ ብር <u>54459170.23</u>

ተገኝቷል፡፡

ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | የውጭ ምንዛሪ |
|---|---|---|---|
| 1 | የፍትሕ ማኒስቴር | 6496.80 | |
| 2 | የድሬዳዋ ጤና ጽ/ቤት | 39021.65 | |
| 3 | የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር | 61200.00 | |
| 4 | የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | 109580.54 | |
| 5 | የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት | 124500.05 | |
| 6 | በውጪ ጉዳይ ማኒስቴር የዲፕሎማቲክ ማሲዮን | 229355.05 | |
| 7 | የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን | 1461000.00 | |
| 8 | 110ኛ ኮር | 3285015.17 | |
| 9 | 107ኛ ኮር | 4305972.81 | |
| 10 | የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 4992794.91 | $118462.97 |
| 11 | የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 10490028.47 | |
| 12 | የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን | | $1460.00<br>የቤልጂየም ፍራንክ<br>31265 |
| | ድ ም ር | 25104965.40 | |

ለ/ በክልል መንግሥት

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የጋምቤላ ጤና ቢሮ | 9294.80 |
| 2 | የአፋር እንስሳትና እርሻ ልማት ቢሮ | 9990.00 |
| 3 | ሰሜን ጎንደር ገንዘብ መምሪያ | 12664.70 |
| 4 | የጋምቤላ ትምህርት ቢሮ | 14142.30 |
| 5 | የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ | 85175.45 |
| 6 | የጌዴኦ ዞን ጤና መምሪያ | 217967.35 |
| 7 | የአማራ ዞን ጤና መምሪያ | 354173.20 |
| 8 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ጤና መምሪያ | 429918.00 |
| 9 | የአማራ ግብርና ቢሮ | 472400.06 |
| 10 | የምሥራቅ ጎጃም ዞን ገንዘብ መምሪያ | 589595.56 |
| 11 | የሰሜን ጎንደር ዞን ጤና መምሪያ | 666847.00 |
| 12 | የሐረሪ ትምህርት ቢሮ | 1797497.58 |
| 13 | የሐረሪ ጤና ቢሮ | 3695279.22 |
| 14 | የአፋር ጤና ቢሮ | 5432244.73 |
| 15 | የአፋር ትምህርት ቢሮ | 6769833.23 |
| 16 | የሱማሌ ትምህርት ቢሮ | 8796900.15 |
| | ድ ም ር | 29353923.33 |

**2.11 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ**

የተመዘገቡት ሂሣቦች የበጀት ዓመቱ ወጪዎች መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

በፌዴራል መንግሥት ብር 2,993,803.94

በክልል መንግሥታት ብር 4,646,598.55

በድምሩ ብር 7,640,402.49

የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ ተገኝቷል፡፡

ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ሀ/ በፌዴራል መንግሥት

| ተ/ቁ | መ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የአየር ሐይል ጠቅላይ መምሪያ | 2,774.70 |
| 2 | የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 2,991,029.24 |
| | ድምር | 2,993,803.94 |

ለ/ በክልል መንግሥታት

| ተ/ቁ | መ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የሐዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ | 1,000.00 |
| 2 | የጋምቤላ ጤና ቢሮ | 1,616.83 |
| 3 | የአፋር ጤና ቢሮ | 29,363.24 |
| 4 | የጋሞጎፋ ዞን ትምህረት መምሪያ | 31,315.32 |
| 5 | የጋምቤላ ትምህርት ቢሮ | 60,693.44 |
| 6 | የጋምቤላ ግብርና ልማት ቢሮ | 109,267.89 |
| 7 | የጋምቤላ ውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | 110,088.00 |
| 8 | የአማራ ጤና ቢሮ | 195,858.87 |
| 9 | የአፋር እንሰሳት እርሻ ልማት ቢሮ | 263,040.08 |
| 10 | የአማራ ግብርና ቢሮ | 3,844,054.88 |
| | ድምር | 4,646,298.55 |

## 2.12 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት

የመ/ቤቶች የንብረት አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም የገቢና የወጪ አመዘጋገብና የዕቃዎች ቆጠራ ኦዲት በተደረገበት ወቅት በ19 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 19,160,414.10 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ ይኸውም:-

በፌዴራል መንግሥት ብር 7,759,827.34

በክልል መንግሥታት ብር 11,400,586.76

በድምሩ ብር 19,160,414.10 መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

## 2.13 የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት የተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሣብ ሲነጻጸር፣

ሀ/ ያልተሰራበት በጀት

| | | |
|---|---|---|
| በክልል መንግሥታት | ብር | 101,706,567.66 |
| በፌዴራል መንግሥት | ብር | 106,078,477.20 |
| በድምሩ | ብር | 207,785,044.86 |

ለ/ ከበጀት በላይ የወጣ

| | | |
|---|---|---|
| በክልል መንግሥታት | ብር | 14,068,139.09 |
| በፌዴራል መንግሥት | ብር | 14,472,447.40 |
| በድምሩ | ብር | 28,540,586.49 ተገኝቷል |

ከብር 100,000.00 በላይ ያልተሰራበት በጀት የተገኘባቸውና ከበጀት በላይ ወጪ አድርገው የተገኙ መ/ቤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል።

ሀ/ በፌዴራል መንግሥት ያልተሰራበት በጀት

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የመገናኛ ብዙሐን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት | 131,804.26 |
| 2 | የመንግሥት የልማት ድርጅት ባለአደራ ቦርድ | 303,695.31 |
| 3 | የባህርዳር ዩኒቨርስቲ ኤንጂነሪንግ ፋኩሊቲ | 471,126.79 |
| 4 | የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ድርጅት | 474,828.97 |
| 5 | የድሬደዋ ግብርና ጽ/ቤት | 502,977.94 |
| 6 | የቅርስ ጥናት ጥበቃ ባለሥልጣን | 522,012.82 |
| 7 | የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | 540,118.57 |
| 8 | የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈፃሚ ጽ/ቤት | 663,466.37 |
| 9 | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | 742,656.11 |
| 10 | የኢትዩጵያ ብሔራዊ ቲያትር | 751,550.81 |
| 11 | የመቀሌ ቢዝነስ ኮሌጅ | 1,095,469.27 |
| 12 | የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት | 1,273,414.21 |
| 13 | የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር | 1,391,133.50 |
| 14 | ብሔራዊ ዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ | 1,437,190.09 |
| 15 | የኢትጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ | 1,634,756.77 |
| 16 | ዕድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት | 1,791,643.76 |
| 17 | የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | 1,855,644.22 |
| 18 | የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን | 2,195,192.91 |
| 19 | ፍትሕ ሚኒሰቴር | 2,303,246.48 |
| 20 | የአማኑኤል ሆስፒታል | 2,527,566.36 |
| 21 | ጋፋት ኢንጂነሪነግ ፋብሪካ | 2,637,844.97 |
| 22 | የድሬደዋ ጤና ጽ/ቤት | 2,959,867.77 |

| | | |
|---|---|---|
| 23 | የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ባለስልጣን | 3,053,002.99 |
| 24 | የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | 3,870,820.52 |
| 25 | ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 4,528,898.32 |
| 26 | የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን | 7,195,539.29 |
| 27 | የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት | 17,480,002.41 |
| 28 | የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት | 17,631,616.82 |
| 29 | የገቢዎች ሚኒስቴር | 24,111,388.59 |
| | ድምር | 106,078,477.20 |

ለ/ <u>በክልል መንግሥታት ያልተሰራበት በጀት</u>

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | ሰሜን ሸዋ ግብርና መምሪያ | 122,045.26 |
| 2 | የደቡብ ሕዝብ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | 122,212.09 |
| 3 | የጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ | 229,635.90 |
| 4 | ደቡብ ወሎ ጤና መምሪያ | 275,195.80 |
| 5 | ደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ | 399,417.72 |
| 6 | የጌዴኦ ዞን ጤና መምሪያ | 406,587.12 |
| 7 | ሰሜን ጎንደር ጤና መምሪያ | 612,105.51 |
| 8 | የከምባታና ጠምባሮ ዞን ትምህርት መምሪያ | 694,214.81 |
| 9 | ጋምቤላ ትምህርትና ባህል ቢሮ | 786,579.51 |
| 10 | የሃዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ | 798,083.11 |
| 11 | ጋምቤላ ግብርና ልማት ቢሮ | 1,705,240.72 |
| 12 | ሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብ መምሪያ | 1,803,310.52 |
| 13 | የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መምሪያ | 2,028,836.32 |
| 14 | የአፋር እንስሳትና እርሻ ልማት ቢሮ | 2,153,332.35 |
| 15 | ጋምቤላ ጤና ቢሮ | 2,973,763.26 |
| 16 | ጋምቤላ ውሃ ሃብት ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ | 3,085,566.24 |
| 17 | የአፋር ጤና ቢሮ | 3,980,954.69 |
| 18 | የሐረሪ ትምህርት ቢሮ | 4,110,641.68 |
| 19 | የአማራ ግብርና ቢሮ | 4,658,096.59 |
| 20 | የሶማሌ ትምህርት ቢሮ | 5,368,266.52 |
| 21 | የሶማሌ ጤና ቢሮ | 6,517,320.70 |
| 22 | የአማራ ጤና ቢሮ | 7,986,440.25 |
| 23 | ምስራቅ ጎጃም ገንዘብ መምሪያ | 8,215,251.46 |
| 24 | የሐረሪ ጤና ቢሮ | 9,015,215.53 |
| 25 | የደቡብ ሕዝብ ትምህርት ቢሮ | 10,840,872.74 |
| 26 | የአፋር ትምህርት ቢሮ | 22,784,803.80 |
| | ድምር | 101,673,990.20 |

ሀ/ <u>በፌዴራል መንግሥት ከበጀት በላይ የወጣ</u>

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘብ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር | 138,801.88 |
| 2 | የባህርዳር ዩኒቨርስቲ ኢንጂነሪንግ ፋኩልቲ | 166,557.79 |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | ብሔራዊ ሚትሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት | 175,123.70 |
| 4 | የድሬደዋ ጤና ጽ/ቤት | 193,170.29 |
| 5 | ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 341,231.66 |
| 6 | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | 356,677.12 |
| 7 | ፍትህ ሚኒስቴር | 361,954.37 |
| 8 | እድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት | 417,504.88 |
| 9 | የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ባለሥልጣን | 1,903,715.10 |
| 10 | ብሔሪዊ ዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ ኤጀነሲ | 2,434,498.18 |
| 11 | የኢትየጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን | 7,859,423.76 |
| | ድምር | 14,348,658.73 |

ለ/ በክልል መንግሥታት ከበጀት በላይ የወጣ

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የአፋር እንሰሳትና እርሻ ልማት ቢሮ | 413,244.05 |
| 2 | የአማራ ጤና ቢሮ | 582,186.87 |
| 3 | የአፋር ጤና ቢሮ | 903,425.41 |
| 4 | የሶማሌ ጤና ቢሮ | 1183,069.10 |
| 5 | የአማራ ግብርና ቢሮ | 1,317,339.53 |
| 6 | የአፋር ትምህርት ቢሮ | 2,897,707.50 |
| 7 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ፋይናንስ ቢሮ | 6,569,393.76 |
| | ድምር | 13,866,366.22 |

ሳይሰራበት ስለቀረው በጀት አንዳንድ መ/ቤቶች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ባለሙያዎችን ከገበያ ላይ አግኝቶ ለመቅጠር ባለመቻሉ የታቀዱት ፕሮጀክቶች በተግባር ባለመተርጎማቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከበጀት በላይ ወጪ ስለተደረገው ሂሣብ አጥጋቢ ምክንያት ያልተሰጠ ሲሆን፣ በአግባቡ የበጀት ዝውውር ሳያስፈቅዱ ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይኖረው ከተመላሽ በጀት ላይ ክፍያ የሚፈጽሙ መ/ቤቶች በመኖራቸው እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

## 2.14 <u>ከወጪ ቀሪ ሂሣብ</u>

መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የተገኘውን ሂሣብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም የክልል መ/ቤቶች ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮዎች ፈሰስ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ35 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 96,840,344.63 ፈሰስ ያልተደረገ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

በፌዴራል መንግሥት ብር 40,742,830.36
በክልል መንግሥት ብር <u>56,097,514.27</u>
በድምሩ ብር <u>96,840,344.63</u> መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ከብር 1000,00.00 በላይ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የተገኘውን ፊሰስ ያላደረጉ መ/ቤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል።

ሀ/ በፌዴራል መንግሥት

| ተ/ቁ | የመሥሪያ ቤት ሥም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | 127,450.41 |
| 2 | የድሬደዋ ጤና ጽ/ቤት | 323,902.71 |
| 3 | የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ | 1,763,314.52 |
| 4 | የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ | 1,922,109.98 |
| 5 | የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት | 2,156,549.54 |
| 6 | የድሬደዋ ፋይናንስ ጽ/ቤት | 15,291,458.92 |
| 7 | ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 18,898,191.26 |
| | ድምር | 40,482,977.34 |

ለ/ በክልል መንግሥታት

| ተ/ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | ደቡብ ውሎ ዞን ግብርና መምሪያ | 118,837.58 |
| 2 | የአፋር ትምህርት ቢሮ | 803,438.61 |
| 3 | ሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብ መምሪያ | 2,594,522.74 |
| 4 | የሶማሌ ጤና ቢሮ | 3,046,239.61 |
| 5 | የሶማሌ ትምህርት ቢሮ | 3,767,874.85 |
| 6 | የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | 4,642,173.64 |
| 7 | የአፋር ጤና ቢሮ | 5,162,987.45 |
| 8 | የአፋር እንስሳት እርሻ ልማት ቢሮ | 6,143,541.26 |
| 9 | የአማራ ጤና ቢሮ | 13,039,710.87 |
| 10 | የአማራ ግብርና ቢሮ | 14,737,099.52 |
| 11 | ምስራቅ ጎጃም ገንዘብ መምሪያ | 1,929,909.25 |
| | ድምር | 55,986,335.38 |

ከላይ የተጠቀሰው ሂሣብ በወቅቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና ለፋይናንስ ቢሮዎች ፊሰስ መደረግ የነበረበት ሲሆን በአብዛኛዎቹ ተግባራዊ ሳይሆን የተገኘ ነው።

ስለሆነም መ/ቤቶች በደንቡ መሠረት እንዲሰሩ ጥብቅ ክትትል ያስፈልጋል።

ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የውጭ ምንዛሬ | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|---|
| 1 | የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት /የኦዶቪዢዋል ዕቃ ግዢ/ | ጀርመን ማርክ 10175 | |
| 2 | የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | | 3,606.00 |
| 3 | የአየር ሐይል ጠቅላይ መምሪያ | | 4,167.60 |
| 4 | እድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት | | 15,212.10 |
| 5 | የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈፃሚ ጽ/ቤት | | 93,897.44 |
| 6 | 107ኛ ኮር | | 126,735.64 |
| 7 | የድሬደዋ ጤና ጽ/ቤት | | 142,547.50 |
| 8 | የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ | | 488,306.45 |
| 9 | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ማሲዮን | | 556,165.44 |
| 10 | ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | ካናዳ ዶላር 400.000 | 6,329,022.67 |
| | | | 7,759,660.84 |

ለ/ በክልል መንግሥታት

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | ከምባታና ጠምባሮ ዞን ትምህረት መምሪያ | 12,166.53 |
| 2 | ሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ | 16,782.97 |
| 3 | የሐሪሪ ጤና ቢሮ | 250,272.50 |
| 4 | የጋምቤላ ትምህርትና ባህል ቢሮ | 1,177,642.00 |
| 5 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ትምህርትና ባህል ቢሮ | 3,137,564.76 |
| 6 | የሶማሌ ትምህርት ቢሮ | 6,805,698.00 |
| | ድምር | 11,400,126.76 |

## 2.15 <u>የንብረት አስተዳደር</u>

በዘመኑ ኦዲት በተደረጉ አንዳንድ መ/ቤቶች የንብረት ምዝገባ የሚደረግ በመሆኑ ቆጠራ ተደርጎ የንብረት ጉድለትና ብልጫ የተገኘ ሲሆን፣

ከፌዴራል መንግሥት 7
ከክልል መንግሥታት 23
በድምሩ 30 መ/ቤቶች

- የንብረት መዝገብ ያልተቋቋመ በመሆኑ፣
- ርክክብ በአግባቡ ባለመከናወኑ፣
- የንብረት ምዝገባና የንብረት ኃላፊነት በአንድ ሠራተኛ የሚከናወን በመሆኑ፣

- በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ በማድረግ የንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት
የማይረጋገጥ በመሆኑ፣
- ለቋሚ ዕቃ መለያ ቁጥር ባለመስጠቱ፣
- የንብረት ገቢና ወጪ አመዘጋገብ በተሳሟላ ሁኔታ ባለመከናወኑ
የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል።

የመ/ቤቶቹም ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል።

ሀ/ የፌዴራል መንግሥት

| ተ/ቁ | የመስሪያ ቤቱ ስም |
|---|---|
| 1 | የድሬዳዋ ግብርና ጽ/ቤት |
| 2 | የድሬዳዋ ጤና ጽ/ቤት |
| 3 | የምድር ኃይል 110ኛ ኮር |
| 4 | ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን |
| 5 | የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት |
| 6 | የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈጻሚ ጽ/ቤት |
| 7 | የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ |

ለ/ በክልል መንግሥት

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም |
|---|---|
| 1 | የሐረሪ ትምህርት ቢሮ |
| 2 | የሐረሪ ጤና ቢሮ |
| 3 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ትምህርትና ባህል ቢሮ |
| 4 | የቤንሻንጉል ጉምዝ የውሃ ሀብት ቢሮ |
| 5 | የቤንሻንጉል ጉምዝ ጤና ቢሮ |
| 6 | የደቡብ ሕዝቦች ትምህርት ቢሮ |
| 7 | የጌዲ ኦዞን ጤና መምሪያ |
| 8 | የወላይታ ግብርና መምሪያ |
| 9 | የጌዲኦ ግብርና መምሪያ |
| 10 | የሐዲያ ግብርና መምሪያ |
| 11 | የከምባታና ጠምባሮ ዞን ጤና መምሪያ |
| 12 | የከምባታና ጠምባሮ ዞን ትምህርት መምሪያ |
| 13 | የሐዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ |
| 14 | የጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ |
| 15 | የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መምሪያ |
| 16 | የሶማሌ ጤና ቢሮ |
| 17 | የደቡብ ሕዝቦች ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ |
| 18 | የጋምቤላ ትምህርት ቢሮ |
| 19 | የአፋር እንስሳትና እርሻ ልማት ቢሮ |
| 20 | የአፋር ጤና ቢሮ |

| | |
|---|---|
| 21 | የጋምቤላ ጤና ቢሮ |
| 22 | የሰሜን ጎንደር ጤና መምሪያ |
| 23 | የሰሜን ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ |

## 2.16 ማጠቃለያ

የዋናው ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 68/89 አንቀጽ 7/4 መሠረት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች በሙሉ የኦዲት ሪፖርት ተልኳል፡፡ የገንዘብም ሆነ የአሠራር ጉድለት የተገኘባቸው መ/ቤቶች በአቀረብናቸው የማሻሻያ ሃሣቦች ላይ ያላቸውን አስተያየት እንዲያሳውቁ እንዲሁም የጎደለውን የመንግሥት ገንዘብ ለማስተካከት የወሰዱትን እርምጃ እንዲገልጹ በተላከላቸው ሪፖርት ተጠይቋል፡፡ በዚህ መሠረት አንዳንድ መ/ቤቶች መልስ ቢሰጡም ብዙዎቹ ግን መልስ አልሰጡም፡፡በእኛ አስተያየት በየአመቱ ለመንግሥት የምናቀርበው ሪፖርት እየታየ የተከሰቱትን ጉድለቶች ለማሻሻል የሚቀርቡላቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ በማያደርጉ፣የጎደለውን የመንግሥት ገንዘብ ለማስተካከት ተገቢውን እርምጃ በማይወስዱና በአጠቃላይ በስራቸው ላይ ተገቢውን ቁጥጥር በማያደርጉ ኃላፊዎች ላይ ሊኖር የሚገባው ተጠያቂነት ቢጠናከር የሚታየውን የአሰራር ድክመትም ሆነ የገንዘብና የንብረት ብክነት ለመቀነስ ይቻላል፡፡

በመጨረሻም ኦዲቱን ባካሄድንበት ጊዜ ሥራችን የተቃና እንዲሆን ትብብር ያደረጉልንን ኃላፊዎችንና ሠራተኞች እያመሰገንን ሪፖርቱን ከዚህ ቀጥሎ እናቀርባለን፡፡

## I. የጉምሩክ ባለስልጣን

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት፣ የአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ፣ የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ እና የናዝሬት ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የ1993 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ ውጤቱ ለፌዴራል ገቢዎች ሚኒስቴር፣ ለባለስልጣኑ መ/ቤት እና ለሚመለከታቸው ቅርንጫፎች ተልኮላቸው አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መልስ ሲሰጥ ቀሪዎቹ መልስ ሳይሰጡ ቀርተዋል፡፡

በኦዲቱ ወቅት በአሠራርና በሂሣብ አያያዝ ረገድ ከታዩት ሁኔታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ</u>

1.1 <u>የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ</u>

የዋናው መ/ቤትና የቅርንጫፍ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በአግባቡ መጠበቁን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ብር 14,606.44 ጉድለትና ብር 146.40 ብልጫ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ/ቁ | የመ/ቤቱ ስም | በጉድለት የተገኘ | | በብልጫ የተገኘ | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የባለስልጣኑ መ/ቤት | 10,668 | 38 | | |
| 2 | የአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ | 3,938 | 06 | | |
| 3 | የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ | | | 146 | 40 |
| | ደምር | 14,606 | 44 | 146 | 40 |

በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት በ1991 እና በ1992 በጀት ዓመት የገንዘብ ያዥዎች ርክክብ በመዝገብ ከወጪ ቀሪ መሠረት ባለመፈፀሙ በመዝገብ መሠረት ተመዛዝኖ ለሚታየው ልዩነት ተጠያቂ የሆነውን ገንዘብ ያዥ መለየት አልተቻለም፡፡ ባለፉት ዓመታት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ አስመልክቶ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ተገቢው እርምጃ ባለመወሰዱ አሁንም ችግሩ እንደቀጠለ ተረጋግጧል፡፡
በመሆኑም ተገቢው ማጣራት ተደርጎ በጉድለት የተመለከተው ገንዘብ እንዲተካ፣ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ በብልጫ ለታየው ሂሳብ ደግሞ የገቢ ደረሰኝ እንዲቆረጥለት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 <u>የናዝሬት ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሣጥን ሂሳብ ማመዛዘን አለመቻሉ፣</u>

የጽ/ቤቱን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ :-

- ከ1991 በጀት ዓመት ጀምሮ በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሂሳብ እየተዘጋ ከወጪ ቀሪ እንዲዞር ባለመደረጉ፣

- ከሐምሌ 1993 እስከ ህዳር 1994 ዓ/ም ያለው ሂሳብ ባለመዘጋቱ፣
- ባለፉት አመታት በተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች መሠረት የሂሳብ ማስተካከያዎች ባለመሰራታቸው፣

የሣጥን ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳብ ላይ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ የሂሳብ አያያዙና አሰራሩ መስተካከል እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.3 <u>የሰነድ ሂሳብ</u>

የሰነድ ሂሳብ በወቅቱ መወራረድ እንዳለበት የፋይናንስ አስተደደር ደንብ ቁጥር 17/1989 ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ የሳጥን ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተጠናቀቀ ብር 2,106,841.31 ውዝፍ የሰነድ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የጉምሩክ ባለሥልጣን ዋናው መ/ቤት | 1,198,635 | 69 |
| 2 | የአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ | 768,987 | 85 |
| 3 | የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ | 65,761 | 44 |
| 4 | የናዝሬት ጉምሩክ | 73,456 | 33 |
| | ድምር | 2,106,841 | 31 |

በናዝሬት ጉምሩክ በውዝፍ ከተገኘው ሂሳብ ውስጥ ብር 23,644.67 የተወራረደ ስለመሆኑ በተሰጠው መልስ የተገለፀ ቢሆንም በቀጣዩ ዓመት ኦዲት ወቅት ሰነዱ አለመወራረዱ ተረጋግጧል፡፡

በርካታ የሰነድ ሂሳብ ሊገኝ የቻለው ተገቢው ቁጥጥር በወቅቱ ባለመደረጉ እንደሆነ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ያልተወራረደ ሠነድ ተወራርዷል ብሎ መልስ መስጠት ተገቢ አለመሆኑንና በውዝፍ የተገኘው የሰነድ ሂሳብም በደንቡ መሠረት በአስቸኳይ እንዲወራረድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.4 <u>የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለትና በመዝገብ ያልተመዘገበ ሂሳብ</u>

መ/ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 32/1 እና 36/2 መሠረት ገቢያቸው በደረሰኝ በመሰብሰብ በወቅቱ ምዝገባ ማከናወናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

1.4.1 <u>በናዝሬት ጉምሩክ</u>

- ከጉምሩክ ባለሥልጣን ለጣቢያው የተላከው የበጀት ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ እየተቆረጠለት መመዝገብ ሲገባው ከባንክ ወደ ሳጥን ለገባ ሂሳብ ብቻ የገቢ ደረሰኝ በመቁረጥ በዚሁ መጠን ምዝገባ የሚከናወን መሆኑ፣ ከባንክ ወደ ሣጥን ለገባ የበጀት ሂሳብ ብር 14,842.05 የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት መገኘቱ፣

1.4.2 <u>በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ</u>

ባንክ ገቢ ሆኖ የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሣብ ብር 294,813.37 መገኘቱ፣

በሁለቱም ጣቢያዎች ከላይ የተመለከተው የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሳብ ተገኝቷል::

በመሆኑም የናዝሬት ጉምሩክ ከባለሥልጣኑ መ/ቤት ለሚላክለት የበጀት ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ በመቁረጥ ሂሳቡን እንዲመዘገብና ከባንክ ወደ ሳጥን የሚደረጉ የጥሬ ገንዘብ ዝውውሮች በኮንትራ እንዲመዘገቡ ፣አዲስ አበባ ኤርፖርት ደግሞ በደንቡ መሠረት ገቢውን በደረሰኝ እንዲሰበሰብና ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሳብ እንዲቆረጥለት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

1.5 <u>የባንክ ሂሳብ</u>

በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ የተዘጋጀው የዲፖዚት ሂሳብ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ትክክል መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ባንክ ያልደረሱ ቼኮች ለረዥም ዓመታት በወጪነት በመያዛቸውና ባንክ ገቢ የሆነ ሂሳብ ተጣርቶ የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት በመሆኑ የቀረበው የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ትክክል ሆኖ አልተገኘም ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል::

- ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ ወጪነቱ ያልተረጋገጠ በባንክ በኩል የተቀነሰ ሂሳብ ተብሎ ብር 2,069,249.89 መያዙ ፣
- ከ1985 ዓ.ም ጀመሮ በዲፖዚት የባንክ ሂሳብ ገቢ ሆኖ በመ/ቤቱ ያልተረጋገጠ ገቢ ብር 1,020,619.61 መገኘቱ እና
- ከ1985 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ /93 ባንክ ያልደረሱ ቼኮች ተብሎ ብር 4,016,220.30 መያዙ፣

የሚሉት ናቸው::

በመሆኑም ለችግሩ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቶት ሂሳቡ እንዲታረቅ ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. <u>የገቢ ሂሳብ</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤትና በስሩ የሚገኙት ጣቢያዎች የመንግሥት ገቢ በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና ከዲክላራሲዮን ጋር ማስረጃዎች ተሟልተው መቅረባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1 <u>ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 726,530.57</u>

በዲክላራሲዮን ላይ የተመለከተው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም የመጋዘን ገቢ ትክክለኛነት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ብር 726,530.57 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ተገኝቷል፡፡

| ተራ/ቁ | የ/ቤቱ ሥም | የገንዘብ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ | 13,121 | 56 |
| 2 | በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ | 416,809 | 93 |
| 3 | በናዝሬት ጉምሩክ | 296,599 | 08 |
| | ድምር | 726,530 | 57 |

ይህም በሂሳብና በምንዛሬ ስሌት ስህተት፣መመሪያን ተግባራዊ ባለማድረግ ፣አንድወጥ የሆነ አሰራር ባለመከተልና በታሪፍ አመዳደብ ስህተት ምክንያት ሂሳቡ እንዳልተሰበሰበ ታውቋል፡፡ ስለሆነም ሂሳቡ ከሚመለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች እንዲሰበሰብና ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.2 <u>የተሟላ የገቢ ማስረጃ ያልቀረበለት</u>
<u>ሂሳብ ብር 5,612,960.70</u>

የተሰበሰበው ገቢ ተገቢው ማስረጃ ተሟልቶ የቀረበለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ

<u>በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ</u>:- <u>የውጭ ምንዛሪ</u> <u>ብር</u>

ወደሀገር ውስጥ ለገቡ መድሀኒቶችና
ዕቃዎች ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች
የጥራት ማረጋገጫ ያልቀረበለት ብር 2,761,071.60
ከቅድመ ጭነት ምርመራ ድርጅት

| | | | |
|---|---|---|---|
| የተሟላ የምርመራ ማረጋገጫ ያልቀረበለት | | | 531,949.81 |
| ፎቶ ኮፒ ማስረጃ የቀረበለት | | 422,841.91 | |
| የባንክ ክሬዲት አድቫይስ ያልቀረበለትና | | | |
| የማስጫኛ ሰነድ በባንክ ያልተረጋገጠ | ዩሮ | 6,902,975 | 1,887,514.29 |
| | አሜሪካን ዶላር | 73,083.52 | |
| | ፈረንሣይ ፍራንክ | 24,245.53 | |
| | ዶች ማርክ | 26,565.82 | |
| | የእንግሊዝ ፓውንድ | 15,120.00 | |
| | በጃፓን የን | 280,000.00 | |
| <u>በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ</u>:- | | | |
| - ፎቶ ኮፒ ማስረጃ የቀረበለት | | | 1,198.99 |
| ከቀረጥ ነፃ እንዲወጣ የተፈቀደበት | | | |
| ደብዳቤ ያልቀረበለት | | | <u>8,384.10</u> |

በድምሩ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ብር 5,612,960.70

<u>እና በልዩ ልዩ አገሮች ምንዛሬ የተመለከተው ሂሣብ የተሟላ የገቢ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡</u>

የጥራት ማረጋገጫ ሳይቀርብለት የገባው መድሀኒት በሕብረተሰቡ ጤና ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል መሆኑን

የቅድመ ጭነት ምርመራ የምርመራ ግኝት ማረጋገጫ ሳይቀርብለት የገባው ዕቃ የወጣውን አዋጅና ደንብ ያልተከተለ መሆኑን

አሰመጪዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገባ የተፈቀደለትን ማስረጃ ማቅረብ ካልቻሉ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ እንዲከፍሉ

ፎቶ ኮፒ ማስረጃ የቀረበለት፣የባንክ ዲፖዚት ስሊፕና ቅጾችን በተመለከተ ያልተሟሉት ማስረጃዎች የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የማያስችል በመሆኑ ደንብና መመሪያው በሚያዘው መሠረት ማንኛውም የገቢ ማስረጃ ተሟልቶ መቅረብ እንዳለበት በኦዲት ሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

**2.3** <u>ወደ ሀገር ላልገቡ ዕቃዎች ስለተከፈለው ቀረጥና ታክስ</u>

በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ አንድ አስመጪ ወደሀገር ውስጥ እንዲያስገቡ ከተፈቀደላቸው 1,140 ከረጢት ጥሬ ፕላስቲክ እንዲሁም በናዝሬት ጉምሩክ

አንድ ድርጅት አራት ጥቅል ብለችድ ሐርድ ወልድ ፐልፐ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባታቸው ማስረጃ ሳይቀርብ የአሜሪካን ዶላር 20,865.16 ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ተከፍሎ ዴክላራሲዮን ተበትኖ ተገኝቷል፡፡
በመሆኑም አለአግባብ የባከነው የውጭ ምንዛሪ ተመላሽ እንዲሆንና ለወደፊቱም በአዋጁ መሠረት እንዲሠራ ተገቢው ክትትል መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.4 <u>የማኒፌስት መዝገብ አመዘጋገብን በተመለከተ</u>

የተጫኑ ዕቃዎች ዝርዝር መግለጫ ከጉምሩክ ተቆጣጣሪውና ከመጋዘን ኃላፊው የዕቃ መረከቢያ ሰነዶችን በመረከብ በማኒፌስት መዝገብ በገቢ መመዝገባቸውን፣ ተከታታይ ቁጥር መስጠቱን እና ክፍያ የተፈፀመባቸውን ዴክላራሲዮኖች በወጪ የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በናዝሬት ጉምሩክ የገቢ ምዝገባ የሚከናወነው ከዲክላራሲዮን ላይ መሆኑንና የወጣው ዕቃ ብዛት በወጪ የማይመዘገብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ለወደፊቱ የገቢ ዕቃ ምዝገባ የተጫኑ ዕቃዎችን ዝርዝር መግለጫና የዕቃ መረከቢያ ሰነድን ከጉምሩክ ተቆጣጣሪና ከመጋዘን ኃላፊ በቀጥታ በመረከብ እንዲከናወን፣ ከሰነድ ቁጥጥር ክፍል ዲክላራሲዮን በመረከብ የወጪ ምዝገባ እንዲካሄድ፣ በገቢና ወጪ መካከል ልዩነት ሲኖር ለሰነድ ቁጥጥር ሪፖርት እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.5 <u>የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ምንጭ ሳይጠቀስ</u>
<u>የተስተናገዱ ዲክላራሲዮኖች ብር 3,825.15</u>

በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ በ4 ዲክላራሲዮኖች ለብር 3825.15 የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ምንጭ ሳይጠቀስ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ተሰልቶ የተስተናገዱ የግል መገልገያ ዕቃዎች ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም ለዕቃዎች መከፈል የሚገባው ታክስና ቀረጥ በትክክል መሰራቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ጽ/ቤቱ ቀረጥ ለማስከፈል የተጠቀመበትን ትክክለኛ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ምንጭ እንዲያጣራና ያልተሰበሰበ ሂሳብ ካለ ገቢ እንዲሆን፣ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጸም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.6 <u>በዲፖዚት ዕቃቸውን አውጥተው ሂሳባቸውን</u>

*<u>ያላወራረዱ አስመጪዎች ሂሳብ ብር 5,245,357.09</u>*

በዲፖዚት ዋስትና የተስተናገዱ አስመጪዎች ሂሳብ የተወራረደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ በ268 ዲክላራሲዮኖች ብር 5,245,357.09 ያልተወራረደ የቀረጥ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል:: በመሆኑም በዲፖዚት ዕቃቸውን ያወጡት ግለሰቦችና ድርጅቶች ሂሳባቸውን ባስቸኳይ እንዲያወራርዱ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

2.7 *<u>የጊዜ ገደቡ ባለፈ የኢንሹራንስ ቦንድ ተስተናግደው የተገኙ አስመጪዎች</u>*

ሁለት ድርጅቶች የአገልግሎት መስጫ የጊዜ ገደቡ ባለፈ የብር 830,502.12 ኢንሹራንስ ቦንድ በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ መስተናገዳቸው ታውቋል:: አስመጪዎች ቀረጥና ታክሱን ባይከፍሉ የኢንሹራንስ ድርጅቱን በህግ ለመጠየቅ የማይቻል በመሆኑ አሰራሩ መታረም እዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

2.8 *<u>አባንደንድ ሆነው ወደ ውርስ መጋዘን ያልተላለፉ ዕቃዎች</u>*

በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈልባቸው በህግ ከተወሰነው 90 ቀን በላይ የቆዩ ዕቃዎች ለመንግሥት ውርስ መደረጋቸው ሲጣራ ከገቢ መጋዘን ወደ ውርስ መጋዘን መተላለፍ የነበረባቸው 33 ጥቅል ዕቃዎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ 36 መኪናዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና የመጋዘን ኪራይ ተከፍሎባቸው ከመጋዘን ወጪ መደረጋቸው ተረጋግጧል:: ዕቃዎቹ እንዴት ሊወጡ እንደቻሉ ለማጣራት ቢሞከርም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ የተከፈለባቸው ዲክላራሲዮኖች እና ደጋፊ ሠነዶች ለኦዲት ባለመቅረባቸው ዝርዝር ሁኔታውን ማጣራት ሳይቻል ቀርቷል::

ከባለስልጣኑ በተላለፈው መመሪያ መሠረት በገቢ መጋዘን ከ90ቀን በላይ የቆዩና በተለያዩ አሳማኝ ምክንያቶች ወደ ውርስ መጋዘን ያልተላለፉ ዕቃዎች ባለቤቶቹ ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ዕቃውን አስቀርጠውና ሌሎች የሚፈለጉባቸውን ክፍያዎች ከፍለው ለመወሰድ ለጽ/ቤቱ በጽሁፍ ጥያቄ ሲያቀርቡ እየተፈቀደ የሚስተናገዱ መሆኑ ታውቋል:: ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ላጋር እና በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ የወጡት ዕቃዎች በመመሪያው መሠረት አስፈላጊውን

ፎርማሊቲ አሟልተው የወጡ ባለመሆናቸው ይህን ባደረጉ ሠራተኞች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ፣ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.9 ለኦዲት ሥራ ያልቀረቡ ዲክለራስዮኖች

በአ.አ ኤርፖርት ጉምሩክ 193፣በአ.አ ላጋር ጉምሩክ 257፣በናዝሬት ጉምሩክ 65፣በድምሩ 525 ዲክለራስዮኖች ለኦዲት ባለመቅረባቸው በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ ብር 27,684,246.00፣ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ብር 6,477,226.00 የተሰበሰበውን የቀረጥና ታክስ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በመሆኑም የባለሥልጣኑ መ/ቤት በዲክላሪሲዮኖች አጠባበቅ ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እዳለበት እና ዲክለራስዮኖቹም ተፈልገው በውስጥ ኦዲት በኩል እንዲጣሩ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. ወጪ

የባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤትና በሥሩ የሚገኙት የቀጠና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ለተገቢው አገልግሎት የተከፈለና በአስፈላጊው የወጪ ማስረጃ የተደገፈ መሆኑ እንዲሁም ግዢው በደንቡ መሠረት መፈፀሙንና የተገዛውም ዕቃ ገቢ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

3.1 ደንብን ያልተከተለ ወጪ

3.1.1 በባለስልጣኑ መ/ቤት

- ማስረጃ ያልቀረበለት የውጭ አገር ውሎ አበል:-

| | | |
|---|---|---|
| | የቤልጁም ፍራንክ | 31,265.00 |
| | የአሜሪካን ዶላር | 1,460.00 |
| በብልጫ የተከፈለ የውጭ አገር ውሎ አበል የአሜሪካን ዶላር | | 82.07 |
| ከግለሰቦች የሚፈለግ የስልክ ሂሳብ | | ብር 198.17 |
| ከተፈቀደው በላይ የተደወለ የስልክ ሂሳብ | | ብር 824.57 |

3.1.2 በናዝሬት ጉምሩክ

- ያለአግባብ የተፈፀመ የያዥ አበልና ልዩ ልዩ ወጪዎች ብር 46,728.00
- የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለትና ፈሰስ ያልተደረገ የሥራ ግብር ብር 18,515.80

በድምሩ ብር 66,266.54፣ የአሜሪካን ዶላር 1,542.07 እና የቤልጄም ፍራንክ 31,265.00 ደንብን ሳይከተል ወጪ የተደረገ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብ እና ከግለሰቦች የሚፈለግ የስልክ ሂሳብ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ፣ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ማስረጃው ሊቀርብ ካልቻለ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲሆን፣ደረሰኝ ያልተቆረጠለት የሥራ ግብር እንዲቆረጥለትና ፈሰስ እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ደንብና መመሪያን የተከተለ መሆኑ እንዲረጋገጥ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. <u>ከወጪ ቀሪ</u>

4.1 <u>በዋናው መ/ቤት</u>

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በዋናው መ/ቤትና በሥሩ በሚገኙት ቅርንጫፍ መ/ቤቶች የተጠቃለለ ከወጪ ቀሪ ብር 109,951,651.48 እንደነበረ ታውቋል፡፡

ወደ 1993 በጀት ዓመት የዞረው የዋናው መ/ቤትና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተጠቃለለ ከወጪ ቀሪ በወርኃዊ የሂሳብ ማስታወቂያ ከተመለከተው በብር 6,913,723.39 ብልጫ በማሳየቱ፣የልዩነቱን መንስኤ በማጣራት ማስተካከያ የተደረገ መሆኑ የተገለፀ ቢሆንም ማስተካከያው በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ የተዘጋጀውን የሂሳብ ማስተካከያ መቀበል አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ለማስተካከያው ማስረጃ እንዲያቀርብ ካልሆነ ማስተካከያው በድጋሚ እንዲሰራ ለወደፊቱም የሂሳብ ማስተካከያ በበቂ ማስረጃ መደገፍ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳበናል፡፡

4.2 <u>በናዝሬት ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት</u>

በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ መዝገብና በወርኃዊ የሂሳብ ማስታወቂያ መካከል ከፍተኛ የሂሳብ ልዩነት በመኖሩ እና ተዘጋጅቶ በቀረበው ወርሀዊ የሂሳብ ማሰታወቂያ ላይ በወቅቱ በነበሩት የመ/ቤቱ ኃላፊ ፊርማ ትክክለኛነቱ ባለመረጋገጡ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበረውን ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በመሆኑም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ፣ የመንግሥትን የሂሳብ አያያዝ ስርዓትና መመሪያ ተከትሎ ሂሳቡን በአግባቡ እንዲይዝ ተገቢው ክትትል መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5. <u>ንብረት</u>

በ1992 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት ሊብሬያቸው በባለስልጣኑ የተገኘ 6 ተሽከርካሪዎች የት እንዳሉ እንዲጣራ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ከአዲስ አበባ መስተዳድር መንገድ ትራንስፖርት መገናኛ ቢሮ በተገኘው ማረጋገጫ አንድ ቶዮታ ላንድክሩዘር በኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር ንብረትነት መያዙ፣አንድ ኒሳን ፓትሮል በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ንብረትነት መያዙ፣ አንድ ቶዮታ ላንድክሩዘር ሰይፉና ኢብራሒም አብዱ በተባሉ ግለሰቦች ባለቤትነት መያዙና አንድ ላንድሮቨር ደግሞ በከስተምስ ኤንድ ኤክስይዝ ታክስ አድምንስትሬሽን ንብረትነት መያዙ እና እንዲሁም ሶስቱ ተሽከርካሪዎች የቀድሞው ታርጋቸው የተቀየረ መሆኑ ተገልጿል፡፡

የባለሥልጣኑ የነበሩት ሶስቱ ተሽከርካሪዎች በምን ሁኔታ ወደ ሌላ አካል ንብረት ሊዛወሩ እንደቻሉ እንዲሁም በባለሥልጣኑ ስም ተመዝግቧል የተባለው ተሽከርካሪ የት እንደሚገኝ መጣራት እንዳለበትና በቀሪዎቹ ሁለት ተሽከርካሪዎች ላይ ደግሞ ተገቢው ክትትል ተደርጎ የሚገኙበት ሁኔታ መታወቅ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6. <u>የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ቀሪ ሂሳብ</u>

የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ቀሪ ሂሣብ የሚፈለግባቸው ደንበኞች ገንዘቡን በወቅቱ መክፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

6.1 <u>በአዲስ አበባ ኤርፖርት</u>

<u>ተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 118,162,429.97</u>

- በሠነድ ቁጥጥር ክፍል በሚገኙ 58 ዲክላራሲዮን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ቀሪ ሂሳብ ብር 229,692.91 መኖሩ፣
- በቀድሞ ሂሣብ ኃላፊና በአዲሱ ሂሣብ ኃላፊ መካከል ርክክብ ያልተፈፀመባቸው በሂሣብ ክፍል ከ5 ዓመት በላይ ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወሰድባቸው የተገኙ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ቀሪ ሂሣብ ብር 797,021.49 ዋጋ ያላቸው 133 ዲክላራሲዮኖች መኖራቸው፣
- የጽ/ቤቱ ሂሣብ ሠራተኛ የነበሩት ወ/ሮ ፋሲካ አይነኩሉ በ25/6/93 ከሜድሮክ ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን የተረከቡት ጉምሩክ ክልል መቆጣጠሪያ ክፍል

ሲዛወሩ ርክክብ ያልተፈፀመበት በተረካቢዋ ሠራተኛ ሊቀርቡ ያልቻሉ በ43 ዲክላራሲዮን የሚፈለግ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ብር 29,631,392.05 መኖሩ፣

- አስመጪዎች ዲፖዚት አስይዘው በዋስትና ዕቃው ከወጣ በኋላ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሲሠራ በዲፖዚት ከተያዘው በተጨማሪ የሚፈለግ ሂሣብ ያለባቸው 101 ግለሰቦችና ድርጅቶች ከ1989 እስከ 14/10/94 ያልተሰበሰበ ብር 724,530.11 መገኘቱ፣
- ከበጀታዊ መ/ቤቶችና መንግሥታዊ ድርጅቶች የሚፈለግ ተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 86,779,793.41 መኖሩ፣

በድምሩ ብር 118,162,429.97 ተሰብሳቢ ሂሣብ መኖሩ ታውቋል:: ከላይ ከተገለፁት ቀሪና ያልተሰበሰበ ሂሣብ ውስጥ በተራ ቁጥር &ለ& እና &ሐ& የተመለከቱት በኦዲት አስደራጊዎች በወቅቱ ያልቀረቡና ከሌሎች ሠነዶች ውስጥ በተገኘው መረጃ መሠረት የሚመለከታቸውን ግለሰቦች በመጠየቅ የተደረሰበት ነው::

በሌላ በኩል በተራ ቁጥር ሀ፣መ እና ሠ የተመለከቱት ማስረጃዎችን የተረከበው አካል ቀሪና ውዝፍ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሂሣብ ተከታትሎ እንዲሰበሰብ በጽ/ቤቱ በኩል እርምጃ እንዲወሰድ፣በተራ ቁጥር &ለ& እና &ሐ& የተመለከቱት በጽ/ቤቱ በኩል እስካሁን ሰነዶቹን ተረክቦ ጉዳያቸውን የሚከታተል ክፍል ያለመኖሩ ስለተረጋገጠ የሰነዶቹ ርክክብ በአስቸኳይ ተፈጽሞ የሠነዶቹ ይዘት እየተጣራ የሚፈለገው ቀሪ ውዝፍ ሂሣብ መሰብሰብ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

## 6.2 <u>በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ</u>

<u>ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 251,858,701.27</u>

ሀ/ ቀረጥና ታክስ ከፍለው ከተስተናገዱ በኋላ ዴክላራሲዩን ከመበተኑ በፊት በሰነድ ቁጥጥር ክፍል ሲጣራ ቀሪ ሂሳብ ያለባቸው ድርጅቶች እንዲከፍሉ ተጠይቀው ያልተከፈለ ብር 8,216,051.92

ለ/ አነስተኛ የማስያዣ ሂሣብ አስይዘው በአስቸኳይ ዕቃ መልቀቂያ ቅጽ ከተስተናገዱት አስመጪዎች የሚፈለግ ብር 11,351,430.03፣

ሐ/ በኢንሹራንስና በደብዳቤ ዋስትና ከተስተናገዱት መንግስታዊ መ/ቤቶችና ዓለም  አቀፍ ድርጅቶች የሚፈለግ ቀረጥና ታክስ ብር 18,476,348.02

መ/ ከባለበጀት መ/ቤቶችና ድርጅቶች በገንዘብ ሚ/ር በኩል ተጠይቆ ወደ ቀጥታ ገቢ መዞር ሲገባው ሳይሰበሰብ በገቢ ሂሣብ ክፍል በሌጀር መሠረት የተገኘ ሂሣብ ብር 210,407,375.37፣

ሠ/ ከቀረጥ ነፃ ገብተው ያገለገሉ መኪናዎች በ1993 በጀት ዓመት በሽያጭ ወይም በስጦታ ስም ለማዛወር ቀረጥና ታክስ እንዲከፍሉ ተጠይቆ ሳይከፍሉና ዲክላራሲዮን ሳይበተን የተገኘ ብር 2,723,285.95

ረ/ በሰነድ ቁጥጥር ክፍል ቀሪ ሂሣብ ተጠይቀው ካልከፈሉ አስመጪዎች የሚፈለግ ብር 684,209.98፣

በድምሩ ብር 251,858,701.27 ተሰብሳቢ ሂሣብ መኖሩ ተረጋግጧል።

በአስቸኳይ ዕቃ መልቀቂያ ተስተናግደው ተጨማሪ ሂሣብ የሚፈለግባቸው አስመጪዎች አዲስ ኦፐሬሽን በሚከፍቱበት ጊዜ ቀሪ ሂሣባቸውን እንዲያጠናቅቁ ብርቱ ቁጥጥር የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት እንዳለበት፣በኢንሹራንስ ዋስትና እንዲሁም በደብዳቤ የተስተናገዱ አስመጪዎች የዋስትና ጊዜያቸው ከማለፉ በፊት ተከታትሎ ቀረጥና ታክሱን እንዲከፍሉ ማድረግ እንዲሁም ከባለበጀት መ/ቤቶች ስለሚፈለግ ሂሣብም ሆነ ከቀረጥ ነፃ ገብተው ወደ ሶስተኛ ወገን ከተዛወሩት መኪናዎች የሚፈለገው ቀረጥና ታክስ ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች ጋር ጥብቅ የሆነ የሥራ ግንኙነት በመፍጠር ተሰብሳቢው ሂሣብ በአዋጅ ቁጥር 60/89 መሠረት የጊዜ ገደቡ ከማለፉ በፊት እንዲሰበሰብ ወይም ክስ እንዲመሰረት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

7. <u>ስለተፈቀደው በጀትና ሥራ ላይ ስለዋለው ሂሣብ /የተጠቃለለ በጀት/</u>

ለባለሥልጣኑ በ1993 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀትና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲመዛዘን በዝርዝር የሂሣብ መደቦች ከበጀት በላይ የወጣ ብር 7,859,423.76 ያልተሠራበት በጀት ብር 7,195,539.29 ተገኝቷል።

ከበጀት በላይ ስለወጣው ሂሣብ በተሰጠው መግለጫ ለተሽከርካሪ መኪናዎች መሣሪያዎች መግዣ ክፍያው በ1992 በጀት ዓመት ተፈጽሞ ንብረቱ ገቢ እስኪሆን ድረስ በወጪ ያልተመዘገበ በመሆኑ የታየ ልዩነት መሆኑንና ያልተሠራበት በጀት ሊታይ የቻለው በኰድ ስህተትና የቀጠና ጽ/ቤቶች ደመወዝና አበል ሲመዘገብ በአንድ የሂሣብ መደብ በመያዛቸው መሆኑ ተገልጿል። ሆኖም በባለሥልጣኑ

የተሰጠው መግለጫ ለተወሰኑ የሂሣብ መደቦች ብቻ በመሆኑ እና ቀጠና ጽ/ቤቶች ሰርተዋል የተባለው ስህተት በወቅቱ ታርሞ ትክክለኛ የተጠቃለለ የበጀት ሂሣብ መቅረብ ሲገባው የተሳሳተ መረጃ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዲቀርብ መደረጉ ተገቢ እንዳልሆነና ለወደፊቱም የበጀት ዝግጅት በበቂ ጥናት የተደገፈና ሊተገበር የሚችል መሆን እንዳለበት ፣ ከተፈቀደው በላይ ሥራ ላይ ማዋልም የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብን ያልተከተለ አሰራር በመሆኑ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳበናል፡፡

8. <u>በኦዲት ሪፖርት በተሰጡ አስተያየቶች</u>
   <u>ላይ እርምጃ ሳይወሰድ ስለመገኘቱ</u>

   የጉምሩክ ባለስልጣንና በሥሩ ያሉ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት እርምጃ መወሰዱ ሲጣራ የአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ እና የናዝሬት ጉምሩክ በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ አለመወሰዱ እንዲሁም ለሪፖርታችን በተሰጠው ምላሽ እርምጃ ተወስዷል ተብሎ የተገለፁ ጉዳዮች እርምጃው ሳይወሰድ መገኘቱ ታውቋል፡፡ የኦዲት ሪፖርት ለሥራ አመራሩ አጋዥና ለመ/ቤቱ ገንቢ መሆኑ እየታወቀ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ እርምጃ አለመወሰድ አግባብ አለመሆኑንና ለኦዲት ሪፖርታችን ትክክለኛ መልስ መሠጠት እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

9. <u>በሕግ አገልግሎት በኩል የታዩ ችግሮች</u>

   ለባለሥልጣኑ መ/ቤት የፍርድ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች ባለዕዳዎች በአብዛኛው አድራሻቸው ስለማይታወቅ ገንዘብ ለመሰብሰብ ችግር መኖሩንና፣ነገረ ፈጆች የክስ ፋይል ሳያስረክቡ መ/ቤቱን በመልቀቃቸው በክትትል ማነስ የተዘጉ ፋይሎች መኖራቸውን የባለስልጣኑ የህግ ባለሙያ የገለፁ ሲሆን፣ የህግ ክፍሉ ያለበት የአሠራር ችግሮችና ድክመቶች ታርመው ሥራው በአግባቡ እንዲከናወን ተገቢው ክትትል መደረግ እንዳለት አሳስበናል፡፡

10. <u>ልዩ ልዩ</u>

    በጉምሩክ ዋናው መ/ቤትና በሥሩ ያሉ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት በተደረገበት ወቅት ቀጥሎ የተመለከቱት የሂሳብ አያያዝና የአሠራር ግድፈቶች ተገኝተዋል፡፡

10.1. <u>በዋናው መ/ቤት፣</u>

- በመዝገብ የተመለከተው የወጪ ሂሣብ በወርኃዊ ሂሣብ ማስታወቂያ በወጪ ሂሣብ መደብ 6101፣6102፣6201፣6205 እና 6306 ከተመለከተው ሂሣብ በድምሩ በብር 360,326.24 በማነስ እንዲሁም በ6210 የተመለከተው ደግሞ በብር 319,391.89 በብልጫ የሚያሳይ መሆኑ፣
- በጉምሩክ ባለሥልጣን እየተዘጋጀ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚቀርበው የተጠቃለለ ወርሃዊ የሂሳብ ማስታወቂያ በቀጠናዎች ከሚያዘው የገቢና የወጪ ሂሳብ መዝገብ ጋር የማይመሣከር መሆኑ፣
- በጉምሩክ ባለሥልጣን የኮምፒዩተሮችና የኮምፒዩተር መለዋወጫ ዕቃዎች ገቢና ወጪ ምዝገባ እንዲከናወን ባለፈው ኦዲታችን አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሠራሩ ያልተስተካከለ መሆኑ፣
- በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ዕቃዎች ለረዥም ዓመታት በመጋዘን ውስጥ መከማቸታቸውና በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ አለመወሰድ፣

10.2 <u>በናዝሬት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ፣</u>

- በሞ/265 እና ሞ/266 ገቢና ወጪ የሚሆኑ ዕቃዎች ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣
- ሠራተኞች የፈረሙበት የትርፍ ሰዓት መቆጣጠሪያ ደብተር ባለመቅረቡ ክፍያው ደንብን ተከትሎ መፈፀሙን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- ያገለገሉ የቢሮ ዕቃዎች ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸውና በኃላፊነት የተረከባቸው ሠራተኛ ሣይኖር በተለያዩ ክፍሎች የተቀመጡ መሆኑ፣
- በየዕለቱ የተሰበሰበው ገንዘብ በዕለቱ ወይም በማግስቱ ባንክ ገቢ መሆን እንዳለበት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ የሚያዝ ቢሆንም በጽ/ቤቱ ከ10 ቀን በላይ በካዝና የቆየ ጥሬ ገንዘብ መቆጠሩ፣

ለረዥም ጊዜ መቆየት የማይችሉና ለአጠባበቅ የማያመች ዕቃዎች በዝግ ጨረታ ካልሆነ በስተቀር በግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ የማይወጣ መሆኑ፣

- በአዋሽ መቆጣጠሪያ ጣቢያ በኮንትሮባንድ ለሚያዙና ዕቃ ለሚወረስባቸው መንገደኞች ደረሰኝ ሞ/270 የማይሰጥ መሆኑ፣
- በአዋሽ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ስቶክ ካርድና የሞ/265 መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ፣

- በአዋሽ መቆጣጠሪያ ጣቢያ ርክክብ በመዝገብ (ስቶክ ካርድ) ከወጪ ቀሪ መሠረት መፈፀም ሲገባው በዕለቱ በሚደረገው ቆጠራ መሠረት መሆኑ፣

10.3 <u>በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ፣</u>

ወደ ውርስ መጋዘን ቁጥር 3 የሚተላለፉ ዕቃዎች በሥርዓቱ የማይመዘገቡና ፊሽ ካርድ ያልተቋቋመ መሆኑ፣

በመጋዘን ቁጥር 6 የሚገኙ ዕቃዎች ለጥበቃና ቁጥጥር በማያመች ቦታ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

ከመጋዘን ወጪ ለሚደረግ ዕቃ የወጪ ማስረከቢያ ቅጽ በሥራ ላይ ያልዋሉ መሆኑ፣

10.4 <u>በአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ ፣</u>

- አስፈላጊው ፎርማሊቲ ተሟልቶ ከመጋዘን ወጪ ለሚደረግ ዕቃ የመጋዘን ዕቃ ማስረከቢያ ሰነድ የሌለ መሆኑ፣
- የዕቃ ግ/ቤት ኃላፊነትና የዕቃ ምዝገባ ሥራ በአንድ ሠራተኛ ተደርቦ የሚሠራ መሆኑ፣
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የዕቃ ቆጠራ በማድረግ በመዝገብ ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሣከር መሆኑ፣

ታውቋል::

ከላይ የተመለከቱት የሂሳብና የአሰራር ድክመቶች እንዲታረሙ ተገቢው ክትትል መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

## II <u>የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን</u>

የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ዋናው መ/ቤት እና በሥሩ ያሉት የናዝሬት፣ የድሬዳዋ እና የሰሜን ምዕራብ ቅርንጫፎች፤ እንዲሁም የፌዴራል ግብር ይግባኝ ኮሚሲዮን ጽ/ቤትና የገቢዎች ሚኒስቴር የ1993 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ተደርጓል::

በአሠራርና በሂሣብ አያያዝ ረገድ ከታወቁት ሁኔታዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ቀጥለው ቀርበዋል::

### 1. <u>የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ኦዲት</u>

#### 1.1 <u>በብልጫ ስለታየው ብር 870,888.53</u>

የናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በመዝገብ ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ሂሣብ ጋር ሲመዛዘን ብር 870,888.53 ብልጫ ተገኝቷል:: ብልጫው ሊታይ የቻለው ለአመታት የቆየ የአመዘጋገብ ችግር በመኖሩና ግብር ከፋዮች በቀጥታ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገቢ የሚያደርጉት ሂሣብ እና ጽ/ቤቱ በሚያንቀሳቅሰው የባንክ ሂሣብ ቁጥር 1948 ተለይቶ እንዲመዘገብ ሲደረግ በቀድሞው መዝገብ የተመለከተው ከወጪ ቀሪ በአግባቡ ተጣርቶ መዝገብ ላይ ባለመመዝገቡ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::

በመሆኑም ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ሂሣቡ መስተካከል እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

## 1.2 <u>የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከወጪ ቀሪ</u>

<u>ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ስለአለመቻሉ፣</u>

በጥሬ ገንዘብና በቼክ የተሰበሰበው የግብርና ታክስ ሂሣብ አመዘጋገብና የመዝገብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በዋናው መ/ቤት በሶስት ዋና ገንዘብ ያዥዎች በተለያየ ቀን በአንድ ደረሰኝ በቀጥታ የሚሰበሰበው እና ከዕለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች ለዋና ገንዘብ ያዥዎች ፈሰስ የሚደረገው ጥሬ በገንዘብ በአንድ የሳጥን ሂሣብ መዝገብ /ገ/ሂ/23/ የሚመዘገብ በመሆኑ፣
- ከሐምሌ 1993 ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 1994 ዓ.ም ድረስ ያለው የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ በመዝገብ ላይ በገቢና በወጪ የተመዘገበ ቢሆንም ሂሣቡ

  አለመደመሩና ትክክለኛው ከወጪ ቀሪ ሂሣብ በየወሩ እንዲዞር ባለመደረጉ፣ የተመዘገበው ሂሣብ ትክክለኛ ስለመሆኑ በመ/ቤቱ ኃላፊ፣ በሂሣብ ሹሙና በገንዘብ ያዥ ፊርማ እንዲረጋገጥ ባለመደረጉ፣
- በሰሜን ምዕራብ አብይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ የካቲት 1994 ባለው ጊዜ ውስጥ ተሰብስቦ በባንክ በኩል ወደ ጠቅላይ ግምጃ ቤት ፈሰስ የተደረገው ሂሣብ ባለመመዝገቡና ከወጪ ቀሪው ባለመረጋገጡ ፣
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ግብር ከፋዮች በቀጥታ ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ የባንክ ሂሣብ ገቢ ለሚያደርጉት ሂሳቦች የባንክ ስሊፕ ሣይቀርብለት፣ የገቢው

ትክክለኛነት ሳይረጋገጥና የገቢ ደረሰኝም ሣይቆረጥለት በወሩ መጨረሻ በጥቅሉ ባንክ ገቢ ሆኖ በመዝገብ በገቢ ያልተመዝገበ በማለት የሚመዘገብና በዚሁ መሰረት ወርኃዊ የሂሣብ ማስታወቂያ የሚዘጋጅ ስለሆነ የሂሣቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ባለመቻሉ፣

በሣጥንና በባንክ የተገኘውን ሂሣብ በመዝገብ ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር ማመሳከር ሣይቻል ቀርቷል።

የገቢና የወጪ ሂሣብ በወቅቱ እንዲመዘገብ፣ ሂሣቡ በየወሩ እየተዘጋ በሣጥንና ባንክ ከሚገኘው ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመሣከር፣ ልዩነቶች በወቅቱ ተጣርተው ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና በዋናው መ/ቤትም ሆነ በቅ/ጽ/ቤቶች ውስጥ የተከሰቱትን የአሠራርና የውስጥ ቁጥጥር ግድፈቶች በአፋጣኝ በማረም የጥሬ ገንዘብ መዛግብት ትክክለኛውን ገጽታ እንዲያሳዩ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

**1.3 <u>የባንክ ሂሣብ፣</u>**

- በሰሜን ምዕራብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የባንክ ሂሣብን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በየወሩ የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ የማይዘጋጅ በመሆኑ፣
- የትግራይ ክልል ፋይናንስ ቢሮ የፌዴራል ግብር ከፋዮችን ግብርና ታክስ እንዲሰበስብ የተሰጠውን ውክልና ተግባራዊ ባለማድረጉና ማስረጃዎች ተጠናቅረው ባለመቅረባቸው ለዚሁ ተግባር በተከፈተው የባንክ ሂሣብ ገቢ የሆነውን ሂሣብ ትክክለኛነት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል።

  በመሆኑም ከላይ የተመለከቱት የአሰራር ድክመቶች ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲታረሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

**1.4 <u>የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት እና ያልተመዘገበ ሂሣብ</u>**

**<u>ብር 1,365,890.26</u>**

- በሰሜን ምዕራብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ ወደ ባንክ ገቢ ሆኖ የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለትና ያልተመዘገበ ብር 441960.67፣ በገቢ ደረሰኝ ተሰብስቦ የፊሰስ መቀበያ ደረሰኝ /ሞ/64/ ያልተቆረጠለትና ያልተመዘገበ ብር 855617.75 ተገኝቷል።
- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከሐምሌ ወር 1992 ጀምሮ እስከ ሰኔ 1993 ድረስ ባንክ ገቢ ሆኖ የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለትና በመዝገብም

ያልተመዘገበ ብር 68311.84 ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ሂሣብ ውስጥ ብር 58488.66 ባንክ ገቢ የሆነበት ማስረጃ አልቀረበም፡፡

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 32፣35 እና 36 ላይ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም የመንግሥት ገቢ በሕጋዊ ደረሰኝ ገቢ መደረግና መመዝገብ ያለበት መሆኑን ጠቅሰን ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግና ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሣብም በደንቡ መሠረት ደረሰኝ ተቆርጦለት እንዲመዘገብ ባንክ ገቢ የተደረገበት ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብም ማስረጃ እንዲቀርብለት እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

### 1.5 <u>ውዝፍ የሠነድ ሂሣብ ብር 331,546.37</u>

የደመወዝ የሰነድ ሂሣብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ የዕቃና የአገልግሎት ግዥን የሚመለከተው ደግሞ በ7 የሥራ ቀናት ውስጥ ተጠናቅቆ እንዲወራረድ በመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ደንብ የተደነገገ ቢሆንም የባለሥልጣኑ መ/ቤት የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተጠናቀቀ ብር 331546.37 የሠነድ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

አሰራሩ የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብን ያልተከተለ በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

የመንግሥት ገቢ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

### 2.1 <u>ያልተሰበሰበ ውዝፍ የግብር ሂሣብ</u>
### <u>ብር 284273795.25</u>

በግብር ከፋይ ድርጅቶች ላይ በየታክስ ዘመኑ የተወሰነው ግብር በአግባቡ ገቢ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከ135 ድርጅቶች ብቻ ብር 284273795.25 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ሁኔታውም ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

| ተ.ቁ | የመ/ቤቱ ስም | ያልተሰበሰበው ሂሣብ የሚፈለግባቸው ድርጅቶች ብዛት | ያልተሰበሰበው የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|
| 1 | የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን | 111 | 171243376.59 |
| 2 | ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት | 15 | 106285206.04 |
| 3 | ሰሜን ምዕራብ ቅ/ጽ/ቤት | 2 | 3042004.69 |
| 4 | ናዝሬት ቅ/ጽ/ቤት | 7 | 3703207.93 |
| | ድምር | | 284273795.25 |

በወቅቱ ካልተሰበሰበው ውዝፍ ግብር ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚፈለግ ነው፡፡

ገቢው ለምን እንዳልተሰበሰበ የተለያዩ ምክንያቶች የተሰጡ ቢሆንም ምክንያቶቹ የመንግስትን ገቢ እንዳይሰበሰብ እንቅፋት የሚሆኑ ወይም የህግ እርምጃ ከመውሰድ የሚያግዱ ባለመሆናቸው ሂሣቡን ለመሰብሰብ የባለሥልጣኑ መ/ቤት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2.2 ግብርና ታክስ ያልተወሰነላቸው ድርጅቶች

ከማናቸውም ገቢ ግብር ስለማስከፈል የወጣው የማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 65/1968 አንቀጽ 4 መሠረት የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋይ ድርጅት በወቅቱ መስጠቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

### 2.2.1. ዋናው መ/ቤት

78 ድርጅቶችና ግለሰቦች የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ በወቅቱ ሳይደርሳቸው በመቅረቱ የይርጋ ዘመኑ ያለፈ መሆኑ ፣ እና

የ124 ድርጅቶችና ግለሰቦች ከሁለት ዓመት እስከ አራት ዓመት የግብርና ታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ ያልደረሳቸው መሆኑ፣

### 2.2.2. <u>የናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት</u>

- በ41 ድርጅቶች ከ1ዓመት እስከ 12 ዓመት ግብርና ታክስ ያልተወሰነ መሆኑ፣
- 4 ድርጅቶች ደግሞ ሥራ የጀመሩበትን ጊዜ የሚገልፅ መረጃ ባለመኖሩ ለምን ያህል ጊዜ ግብር ሣይወሰን እንደቆየ ለማወቅ አለመቻሉ፣

### 2.2.3. <u>የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት</u>

- 43 ድርጅቶች ከ1 እስከ 13 ዓመት ግብርና ታክስ ያልተወሰነላቸው መሆኑ ፣

ታውቋል።

ግብርና ታክስ በወቅቱ ክትትል ተደርጎ ካልተወሰነ የይርጋ ዘመኑ ሲያልፍ ግብር ከፋዮች ያሣወቁት ዝቅተኛ ትርፍም ሆነ ኪሣራ የፀና ስለሚሆን የመንግሥትን ገቢ እንዲቀንስ ወይም ጨርሶ ሳይሰበሰብ እንዲቀር ያደርገዋል። ስለዚህ ግብርና ታክስ በወቅቱ አለመወሰኑ አግባብ ባለመሆኑ መ/ቤቱ የይርጋ ዘመን ከመድረሱ በፊት ያለበትን የሰው ኃይል እጥረት አሟልቶ ግብር መወሰን እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 2.3 <u>ግብርና ታክስ በታሳቢ ያልከፈሉና መክፈል ያቆሙ ድርጅቶች</u>

ግብርና ታክስ ከፋዮች ህጉ በሚያዘው መሠረት ሂሣባቸው ኦዲት ተደርጎ ትክክለኛው ገቢ እስኪታወቅ ድረስ ባሳወቁት ገቢ መሠረት ግብር በታሳቢ መክፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኦዲት ከተደረጉ የግብር ከፋዮች ፋይል ውስጥ 13ቱ ከ1 ዓመት እስከ 13 ዓመት፣
- በናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት 12 ግብር ከፋዮች፣
- በሰሜን ምዕራብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት 16 ግብር ከፋዮች፣

  የሚፈለግባቸውን ግብር በታሣቢ አለመክፈላቸውን ለማወቅ ተችሏል። ከነዚህም ውስጥ በአንዳንዶቹ ማህደሮች ከተከፈቱበት ጊዜ ጀምሮ ግብር የተከፈለ ለመሆኑ ምንም ማስረጃ አለመገኘቱ ታውቋል። ስለዚህ ግብር

መክፈል ያቋረጡ ድርጅቶች ሂሣባቸውን እንዲያሣውቁና መክፈል የሚገባቸውን ግብርና ታክስ እንዲከፍሉ ተገቢውን ክትትል በማድረግ በህጉ በተደነገገው መሠረት ግብር ተወስኖ ከነመቀጫው እንዲከፍሉ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 2.4 ገቢ ያልተደረገ ሂሣብ ብር 3224.17

ግብርና ታክስ ከፋዮች በሚያቀርቡት መግለጫ መሠረት የሚፈለግባቸውን ግብርና ታክስ በትክክል ገቢ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሰሜን ምዕራብ ቅርንጫፍ ብር 3224.17 የሥራ ግብር ገቢ አለመደረጉ ታውቋል። የሥራ ግብሩ ገቢ እንዲደረግ በኦዲት ሪፖርት ባሳሰብነው መሠረት ገቢ መደረጉን ቅ/ጽ/ቤቱ በሰጠው መልስ ገልጿል።

## 2.5 በግብርና ታክስ አሰባሰብ እና አሰራር ላይ የታዩ ግድፈቶች

### 2.5.1 የዋናው መ/ቤት

- በባለስልጣኑ ዋና መ/ቤትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የታክስ ኦዲተሮች የኦዲት ሥራ ወረቀቶች፣ በማህደሮች ውስጥ ባለመገኘታቸው የታክስ ኦዲተሮች ሥራ ሕጉንና የኦዲት ሥርዓትን በመከተል መከናወኑን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- ጥቅምት 1993 ዓ.ም ግብርና ቀረጥ የተሰበሰበባቸው የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሥራ ባለመቅረባቸው በፊሰስ መቀበያ ደረሰኝ (ሞ/64) የተጠቃለለውን ገቢ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- የቴምብሮች ገቢና ወጪ መቆጣጠሪያ ምዝገባ መቋረጡ ፣
- ዋጋ ያላቸው ፎርሞች መቆጣጠሪያ መዝገብ አለመቋቋሙ፣
- የሥራ ግብር ከፋይ የሆኑ 35 ድርጅቶችና ግለሰቦች ከ4 እስከ 25 ዓመታት ክፍያ አለመፈፀማቸውና ክፍያ የተቋረጠበትም ምክንያት በማህደራቸው ያለመገኘቱና ተገቢውም እርምጃ በወቅቱ ያለመወሰዱ፣
- ከግብር ከፋዮች የሚፈለግ የግብር መከታተያ መዝገብ /ሌጀር/ ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- በግብር ከፋይነት የተመዘገቡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች የሥራ ግብር ክፍያ የማይፈጽሙ መሆኑ፣

2.5.2 <u>የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት</u>

የበጎ አድራጎት ድርጅት ተቀጣሪ ሠራተኞች መክፈል ያለባቸው የሥራ ግብር ተመርምሮ ባለመወሰኑ መሰብሰብ ያለበትን ትክክለኛ ገቢ ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

- ስለኤክሳይዝ ሽያጭ ታክስ ማስታወቂያ በወጣው አዋጅ ቁጥር 68/85 በክፍል 4 አንቀጽ 14/ለ እና ክፍል 3 አንቀጽ 12/12 በተደነገገው መሠረት 6 ድርጅቶች የኤክሳይዝና ሽያጭ ታክስ ወርኃዊ ገቢ ማስታወቂያ (ሞ/252) ሞልተው ያላቀረቡ እና ታክሱንም ያልከፈሉ መሆኑ፣
- በጥሬ ገንዘብና በቼክ የተሰበሰበ ገቢ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ በሚያዘው መሠረት በዕለቱ ባንክ ገቢ የማይደረግ መሆኑ፣

2.5.3 <u>የሰሜን ምዕራብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት</u>

- ስለ ኤክሳይዝ ሽያጭ ታክስ ማስታወቂያ በወጣው አዋጅ ቁጥር 68/85 ክፍል 4 አንቀጽ 14/ለ እና ክፍል3 አንቀጽ 12/12 በተደነገገው መሠረት 22 ድርጅቶች የሽያጭ እና 1 የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ደርጅት የኤክሳይዝና ሽያጭ ታክስ ወርኃዊ ገቢ ማስታወቂያ (ሞ/252) ሞልተው ያላቀረቡ እና ታክሱንም ያልከፈሉ መሆኑ፣
- ከግብር ከፋዮች የሚፈለግ የግብር መከታተያ መዝገብ /ሌጀር/ ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- 23 ድርጅቶችና ግለሰቦች በግብር ከፋይነት የተመዘገቡ ቢሆንም የንግድ ሥራ የጀመሩበት ጊዜ የማይታወቅ መሆኑ፣
- ስለንግዱ ዓይነት፣ አመሠራረት፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ እና የመሳሰሉትን የተሟላ ማስረጃዎች ያላቀረቡ 4 ድርጅቶች በግብርና ታክስ ከፋይነት ተመዝግበው መገኘታቸው፣
- የሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀትና ሥራ የጀመሩበትን ጊዜ ያላሳወቁ 6 ድርጅቶች በግብር ከፋይነት ተመዝግበው መገኘታቸው፣
- የደመወዝ መክፈያ ሊስት ያላቀረቡ 30 ድርጅቶች የከፈሉት የሥራ ግብር መሰብሰብ በነበረበት ልክ መሆኑን ማረጋገጥ ያለመቻሉ፣

- የግብር ከፋዮችን የገቢ ማሳወቂያ ፎርም (ሞ/48/ሀ) እና የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ ማሳወቂያ ፎርም (ሞ/252/መ) ገቢና ወጪ መቆጣጠሪያ መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- በፍትህ ሚኒስቴር የሚሰጥ የጥብቅና ፈቃድ አሟልተው ያልያዙ 4 ማህደሮች መገኘታቸው፣
- ለረጅም ዓመታት የግብር ክፍያ እንቅስቃሴ የሌላቸው 98 የግብር ከፋይ ማሕደሮች እንቅስቃሴ ያቋረጡበት ሁኔታ በአብዛኛው በማህደራቸው ውስጥ ያልተጠቀሰ መሆኑ፣

  በመሆኑም መ/ቤቶቹ ከላይ የተመለከቱትን የአሰራር ግድፈቶች በማረም የመንግሥት ገቢ በአግባቡ የሚሰበሰብበትንና አስፈላጊው ማስረጃም የሚሟላበትን መንገድ መቀየስ እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሣቦች በማስረጃ የተደገፉ መሆኑን፣ ክፍያዎች መንግሥት ባወጣው የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

### 3.1 <u>የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ ብር 45242.18</u>

በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ የተሟላ ማስረጃ የቀረበለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

| | | |
|---|---|---|
| • በናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | ብር | 733.63 |
| • በዋናው መ/ቤት | | <u>44508.55</u> |
| በድምሩ | ብር | <u>45242.18</u> |

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ያልተሟሉት ማስረጃዎች በናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የስልክ ቢል ያልቀረበለት እና በዋናው መ/ቤት ደግሞ የወጪ ማስመስከሪያ ያልቀረበለት ሂሣብ ሲሆን ምዝገባው ከመከናወኑ በፊት ማስረጃዎች መሟላታቸው መረጋገጥ እንዳለበትና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲቀርብ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

### 3.2 <u>መመሪያ ሳይከተል</u>

**የተፈፀመ ግዢ ብር 34680.00**

በበጀት ዓመቱ የተፈፀመው ግዥ በወጣው የግዥ መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በዋናው መ/ቤት የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ የብር 34680.00 ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

አሰራሩ የግዥ መመሪያን ያልተከተለ በመሆኑ ድርጊቱን በፈፀሙ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3 **የስልጣን ውክልና ሳይኖር የታዘዘና**

**ወጪ የተደረገ ሂሣብ ብር 2185331.39**

ወጪ የሆነው ሂሣብ በተገቢው የበላይ ኃላፊ የፀደቀ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በዋናው መ/ቤት ወጪን ለመፍቀድ ውክልና ባልተሰጠው ሠራተኛ ታዞ ወጪ የተደረገ ሂሣብ ብር 2185331.39 ተገኝቷል፡፡

አሰራሩ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችን ያልተከተለ በመሆኑ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግና ወጪ የሚፈቅዱ የሥራ ኃላፊዎች የሥልጣን ገደብ እንዲወሰን በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 **የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብለት**

**የተከፈለ ሂሣብ ብር 22241285.52**

የገቢዎች ቦርድ ጽ/ቤት የቅድመ ጭነት ምርመራ አገልግሎት ለሚሰጠው ኩባንያ /S.G.S/ የከፈለው ገንዘብ በበቂ ማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኩባንያው የሰጠው አገልግሎት በሌላ ሶስተኛ ወገን ሳይረጋገጥ ከኩባንያው በቀረበ የቅድመ ጭነት ምርመራ ሪፖርት /CRF/ መሠረት ብር 22241285.52 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ለኩባንያው የተከፈለው ሂሳብ በሰጠው አገልግሎት መጠን መሆኑን ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

ኩባንያው ባቀረበው ሪፖርት ላይ ብቻ ተመስርቶ ክፍያ መፈፀም አግባብ አለመሆኑንና ለወደፊቱም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት የሥራ ግንኙነት ካላቸው ድርጅቶች ተገቢውን ማረጋገጫ በማግኘት ከኩባንያው የተላከው ሪፖርት መጣራት እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. **ከወጪ ቀሪ ሂሣብ**

በዋናው መ/ቤት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የመደበኛ በጀት ብር 443465.74 ከወጪ ቀሪ የነበረ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 427268.76 ለተሽከርካሪ መኪና መግዣ በቼክ ለአስመጪ ኩባንያ በቅድሚያ የተከፈለ ሰነድ መሆኑ ታውቋል።

- በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና በአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን መካከል ባለው የአመዘጋገብ ልዩነት ምክንያት ብር 16714394.60 እንዲሁም የናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በምዝገባ ችግር ምክንያት ብር 22484067.12 የገቢ ሂሣብ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ሆኖ ሊታይ እንደቻለ ታውቋል።

ስለሆነም ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ሲያያዝ መጥቶ መፍትሔ ያላገኘው የአመዘጋገብ ልዩነት እንዲስተካከል መደረግ ይኖርበታል።

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የሚታየው ሂሣብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ ያዛል። በመሆኑም ትክክለኛው የሣጥን ከወጪ ቀሪ ተጣርቶ ፈሰስ እንዲደረግና በልዩ ልዩ ምክንያት በተከሰቱት የአመዘጋገብ ልዩነቶችና ስህተቶች ምክንያት ከወጪ ቀሪ ሆኖ የሚታየው ሂሣብም ተገቢውን ማጣራት በማድረግ እንዲስተካከልና የሂሣብ መዝገቦችና ቅጾች ትክክለኛውን መረጃ እንዲያመለክቱ ተደርገው መዘጋጀት እንደሚኖርባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

5. <u>ስለተፈቀደው በጀትና ሥራ ላይ</u>

<u>ስለዋለው ሂሣብ</u>

የተፈቀደው በጀትና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲመዛዘን

| | | |
|---|---|---|
| በአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን . . . . . . . . . . . | ብር | 2195192.91 |
| በገቢዎች ቦርድ ጽ/ቤት . . . . . . . . . . . . . . | ብር | <u>60088803.48</u> |
| በድምሩ | ብር | <u>62283996.39</u> |

ያልተሠራበት በጀት ተገኝቷል።

በመሆኑም ለወደፊቱ የበጀት እቅድ በበቂ ጥናት የተደገፈና በሥራ ላይ ሊውል በሚችል መልክ መዘጋጀት እንደሚኖርበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

6. <u>ንብረት</u>

6.1 <u>በባለሥልጣኑ ዋናው መ/ቤት</u>

- የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች ስርጭትና ቁጥጥር በተገቢው መንገድ ባለመፈፀሙ እና ለገንዘብ ሰብሳቢ ሠራተኞች የተሰራጨውንና ሥራ ላይ የዋለውን የግብርና ቀረጥ መሠብሠቢያ ደረሰኝ መቆጣጠሪያ መዝገብ /ሌጀር/ ባለመቋቋሙ ደረሰኞች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣
- ለአገልግሎት መስጫ የሚውሉ ቋሚ ዕቃዎች ከአላቂ ዕቃዎች ጋር ተቀላቅለው የሚመዘገቡ መሆኑ፣
- ቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያለመሰጠቱና ቁጥር የተሰጣቸውም ቢሆኑ በቁጥራቸው መሠረት አለመመዝገባቸው፣
- ብር 200 ዋጋ ያለው የነዳጅ ኩፖን በጉድለት መገኘቱ፣

6.2 <u>በሰሜን ምዕራብ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- የንብረት መመዝገቢያ ሞ/70 ሀ፣ የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች ሳይዘጉና ከወጪ ቀሪው ሣይረጋገጥ የአላቂ ዕቃዎችና ደረሰኞች ርክክብ የተፈፀመ መሆኑ፣
- ቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልተሠጣቸው መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

በመሆኑም ለቋሚ ንብረት መዝገብ እንዲቋቋምና የተሟላ መለያ ቁጥር እንዲሰጥ፣ የደረሰኞች ስርጭት ለቁጥጥር በሚያመች መንገድ ተመዝግቦ እንዲያዝና የንብረት ርክክብ በአግባቡ እንዲከናወን እንዲሁም በጉድለት የታየው የነዳጅ ኩፖን እንዲተካ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

7. <u>ባለፉት ኦዲት ሪፖርቶች ላይ</u>
<u>እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣</u>

በ1992 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች ላይ በሰጠነው የማሻሻያ ሃሣብ መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑ ሲጣራ፣

7.1 በናዝሬት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣

- ከኑራ ኤራ እርሻ ልማት ሠራተኞች ማህበር የሚፈለግ ብር 17333.71 ለመሰብሰብ እንዲረዳ የፍሬ ግብርና የመቀጫ ሂሣብ ተለይቶ እንዲገለጽ ለምሥራቅ ሸዋ ዞን ፋይናንስ መምሪያ ደብዳቤ ቢፃፍም መልስ አለመገኘቱ፣
- የኑራ ኤራ እርሻ ልማት ድርጅት መክፈል የሚገባውን ብር 4975.98 ገቢ ለምስራቅ ሸዋ ፋይናንስ መምሪያ በመከፈሉ ተመላሽ እንዲሆን በደብዳቤ ቢጠየቅም ገንዘቡ ተመላሽ አለመደረጉ፣
- ድርጅቶች የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ ሲከፍሉ ሞዴል 252"መ" የተሻሻለውን እንዲሞሉ አለመደረጉ፣
- የሥራ ግብር የከፈሉ አብዛኛዎቹ ድርጅቶች ሥራ የጀመሩበት ጊዜ ከማህደራቸው እንዲያያዝ አለመደረጉ፣
- ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በሰው ኃይል በተለይ ደግሞ በቂ የታክስ ኦዲተሮች በመመደብ እንዲጠናከር አለመደረጉ፣

## 7.2 <u>በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት</u>

በቅ/ጽ/ቤቱ ገ/ሂ/29 እና ሞ/16 መካከል የታየው የገቢ አርዕስት ልዩነት አለመስተካከሉ፣

በውዝፍ የሚገኘው የግብር ሂሣብ ብር 17,498,230.82 አሁንም አለመሰብሰቡ፣

የሽያጭና ኤክሣይዝ ታክስ ወርሃዊ ማስታወቂያ ፎርም ሞዴል 252"መ" የተሻሻለውን የሚሞሉ ግብር ከፋዮች ቁጥራቸው አነስተኛ መሆኑ፣

በቅ/ጽ/ቤቱ ሊሰበስብ የሚገባው ቀረጥ በክልሎች ስለሚሠበሰብ እንዲታረም አስተያየት ቢሠጥበትም አሁንም እልባት አለማግኘቱ፣

## 7.3 <u>በሰሜን ምዕራብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት</u>

- ግብር ከፋዩች በታሳቢ የሚከፍሉት ግብርና ታክስ መክፈል ባለባቸው መጠን መሆኑ የማይረጋገጥና ግብርና ታክስ በወቅቱ የማይወሰን መሆኑ፣
- ዋጋ ያላቸው ፎርሞች ሽያጭ መቆጣጠሪያ መዝገብ አለመቋቋሙ፣
- የግብርና ታክስ ከፋዮች ሂሣብ መቆጣጠሪያ መዝገብ /ሌጀር/ አለመቋቋሙ፣

- ግብርና ታክስ መክፈል በአቋረጡ ድርጅቶች ላይ በቂ ክትትል አለመደረጉ፣
- የሥራ ግብር የሚከፍሉ ድርጅቶች የደመወዝ መክፈያ ሊስት አለማቅረባቸው፣
- በቅ/ጽ/ቤቱ ሥም በመቀሌ ከተማ በተከፈተው የሂሣብ ቁጥር 3167 ገቢ የሆነ ሂሣብ በአግባቡ ለመሰብሰቡ ያልተረጋገጠ እና ቅ/ጽ/ቤቱ በዚህ የባንክ ሂሣብ ገቢም ሆነ ፈሰስ ስለሚደረገው ሂሣብ የሚያውቀው ነገር የሌለ መሆኑና የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ቅ/ጽ/ቤቶቹ በየጊዜው የሚሰጡትን የማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ አለማድረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለዚህ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚሰጡትን የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ በማድረግ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ዋናው መ/ቤት ተገቢውን ክትትል እንዲያደርግ በድጋሚ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የኢኮኖሚ አገልግሎት ዘርፍ

## የ1993 በጀት ዓመት ሪፖርት

በፌዴራል መንግሥት በኢኮኖሚ አገልግሎት ዘርፍ በ1993 በጀት ዓመት ኦዲት ሊደረጉ ፕሮግራም ከተያዘላቸው ኦዲቶች ውስጥ፣

- የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈጻሚ ጽ/ቤት ፣
- የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ባለሥልጣን፣
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ፣
- የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣
- የብሔራዊ ዕጽዋት ዘር ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ፣
- የብሔራዊ ሚቴዎሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት፣
- የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣
- የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ፣
- የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ድርጅት፣

በጠቅላላው የዘጠኝ መ/ቤቶች ሂሣቦች ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ተልኳል፡፡

የ1993 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ተደርጎ፣ በሪፖርቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት፣ በኦዲት ውጤቱ ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው አምስት (5) መ/ቤቶች በወቅቱ ሁለት (2) መ/ቤቶች ዘግይተው መልስ የሰጡ ሲሆን 2 መ/ቤቶች ደግሞ መልስ ሳይሰጡ ቀርተዋል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተ/ራ | የመ/ቤቱ ስም | በወቅቱ መልስ የሰጡ (✔) | ዘግይተው መልስ የሰጡ (✔) | መልስ ያልሰጡ (✔) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ባለሥልጣን | | ✔ | |
| 2 | የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈፃሚ ጽ/ቤት | | | ✔ |
| 3 | የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ | ✔ | | |
| 4 | የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ | | | ✔ |
| 5 | የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት | ✔ | | |
| 6 | የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት | ✔ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ድርጅት | | | |
| 7 | የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ✔ | | |
| 8 | ብሔራዊ የዕጽዋት ዘር ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ | ✔ | | |
| 9 | የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር | | ✔ | |

በኦዲቱ ወቅት የታዩት የአሠራርና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲሁም ጉድለቶችና ግድፈቶች እንደሚከተለው ተጠናቅረው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የሰነድ ሂሣብ</u>

1.1. <u>ውዝፍ የሠነድ ሂሣብ</u>

<u>ብር 4023543.66</u>

በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 38/1 መሠረት ለሥራ ማስኬጃ በተለይ ግዥን በተመለከተ በሰነድ የወጣ ሂሣብ በሰባት የሥራ ቀናት፣ የደመወዝ ሰነድ ሂሣብ ደግሞ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ መወራረድ እንዳለበት የታዘዘ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ በዘርፉ ኦዲት ከተደረጉት ዘጠኝ መ/ቤቶች ውስጥ በስምንቱ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተወራረደ ብር 4023543.66 የሰነድ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ሁኔታውም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈጻሚ ጽ/ቤት | 5403 | 73 |
| 2 | የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ባለሥልጣን | 741627 | 99 |
| 3 | የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ | 18715 | 28 |
| 4 | የብሔራዊ ዕጽዋት ዘር ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ | 20435 | 57 |
| 5 | የብሔራዊ ሚቴዎሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት | 77639 | 82 |
| 6 | የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | 67322 | 95 |
| 7 | የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ | 3083546 | 32 |
| 8 | የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ድርጅት | 8852 | 00 |
| | ድምር | 4023543 | 66 |

ውዝፍ የሠነድ ሂሣብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ውስጥ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ ዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ ኤጀንሲና የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ድርጅት በድምሩ የብር 55764.49 ሠነድ ማወራረዳቸውንና ቀሪዎቹንም ለማወራረድ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን በላኩት የመልስ ሪፖርት ገልፀዋል። በመሆኑም ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ መሠረት በአፋጣኝ እንዲወራረድና ለወደፊቱም የሰነድ ሂሣብ በወቅቱ መወራረድ እንደሚኖርበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል።

2. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

2.1. <u>የላቦራቶሪ ምርመራ ገቢ አሰባሰብን በተመለከተ</u>

የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ከላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት የሚሰበሰበው ገቢ በተፈቀደው ተመን መሠረት መሆኑን ለማጣራት ተሞክሮ የሥራ ትዕዛዝ ደብዳቤዎች፣ የገቢ ደረሰኞች፣ የተከናወነው ሥራ በአግባቡ የማይጠቃቀስ በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል።

በመሆኑም አሰራሩ መስተካከል እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

2.2. <u>የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለትና</u>

<u>በገቢ ያልተመዘገበ ሂሣብ ብር 12480.00</u>

በበጀት ዓመቱ ለተሰበሰበው ገቢ በሙሉ የገቢ ደረሰኝ እየተቆረጠለት መመዝገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ድርጅት የተሰበሰበ ብር 12480.00 የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለትና ሳይመዘገብ ተገኝቷል። በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 32/1 እና 36/2 ላይ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም የመንግሥት ገቢ በሕጋዊ ደረሰኝ ገቢ መደረግ እና መመዝገብ ያለበት መሆኑን ጠቅሰን ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግና ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሣብ በደንቡ መሠረት ተቆርጦለት እንዲመዘገብ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል።

2.3. <u>ያልተሰበሰበ የገቢ ሂሣብ ብር 77702.11</u>

የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ድርጅት በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ላከናወነው የጥናት ሥራ የአገልግሎት ክፍያ ብር 77702.11 ከክልሉ መንግሥት

ያለመሰብሰቡ ታውቋል። በመሆኑም ድርጅቱ አገልግሎት የሰጠበት ገንዘብ በወቅቱ ገቢ እንዲሆን ተገቢውን ክትትል እንዲያደርግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 2.4. <u>ከማዕድንና ኢነርጂ ስለሚሰበሰበው ገቢ</u>

### 2.4.1 <u>ስለ ሮያሊቲ ገቢ ሂሣብ</u>

የማዕድን አምራች ድርጅቶች ምርትና የሽያጭ መጠን ባለመመዝገቡ እና ማስረጃዎችም ለኦዲት አመቺ በሆነ መንገድ ባለመቀመጣቸው መሰብሰብ ያለበትን የሮያሊቲ ገቢ ስሌት ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል።

በመሆኑም ለወደፊቱ ማስረጃዎች አመቺ በሆነ መንገድ እንዲቀመጡና ምዝገባውም መስተካከል እንዳለበት በመግለጽ በላክነው ሪፖረት አሳስበናል።

### 2.4.2. <u>ልዩ ልዩ ገቢዎች</u>

ከናሙና መላኪያ ፣ ከፍቃድ ማውጫና ምዝገባ፣ እና ከፍቃድ ማደሻና ከሙያ ብቃት የሚሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተሞክሮ ለኦዲት ሥራ አስፈላጊ የሆነው ማስረጃ በአግባቡ ባለመያዙ የተሰበሰበው ገቢ ተለይቶ የማይመዘገብ በመሆኑ፣ ገቢው በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ አልተቻለም። በመሆኑም ለወደፊቱ ገቢዎች በዓይነታቸው እየተለዩ በመዝገብ እንዲመዘገቡና ደጋፊ ማስረጃዎቻቸውም ለኦዲት ሥራ በሚያመች መንገድ እንዲቀመጡ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 3. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሣቦች በማስረጃ የተደገፉ መሆኑንና ክፍያዎች ሁሉ አግባብ ባለው ባለሥልጣን እየተፈቀዱ መከፈላቸውንና መመዝገባቸውን፣ በክፍያ አፈፃፀም ረገድ የፋይናንስ ሕግ ደንብና መመሪያዎች መከበራቸውንና ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል።

### 3.1 <u>ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ ብር 61200.00</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በሕጋዊ ማስረጃ የተደገፉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ለኮምፒዩተር ግዥ ወጪ የሆነ ብር 61200.00 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የወጪ ማስረጃው ግዥውን በፈፀመው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንደሚገኝ የተገለፀ ቢሆንም ማስረጃው ግዥውን የበጀቱ ተጠቃሚ በሆነው መ/ቤት ውስጥ አለመገኘቱ፣ ሂሳቡ ከአንድ ጊዜ በላይ በወጪ እንዲመዘገብ ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ማስረጃው የሚቀርብበት መንገድ መመቻቸት እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2. <u>ያለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ</u>

<u>ብር 5027.73</u>

ክፍያዎች መንግሥት ባወጣው የፋይናንስ ሕግ ደንብና መመሪያዎች መሠረት መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ :–

| | | |
|---|---|---|
| የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈጻሚ ጽ/ቤት - - - - - | ብር | 324.50 |
| የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ - - - - - - - - - - - | | <u>4703.23</u> |
| ድምር | ብር | <u>5027.73</u> |

ደንብና መመሪያዎችን ያልተከተለ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

አለአግባብ ከተፈፀሙት ክፍያዎች ውስጥ መ/ቤቱን ለለቀቁ ሠራተኛ የተከፈለ ደመወዝ፣ ለግል ሥራ ለተደወለ የስልክ ሂሣብ እና ከመደበኛ በጀት ላይ የተከፈለ የፕሮጀክት ስልክ አገልግሎት ሂሳብ ይገኝበታል፡፡

በመሆኑም ያለአግባብ የተከፈለው ደመወዝና ለግል ሥራ የተደወለው የስልክ ሂሣብ ተመላሽ እንዲደረግና ለወደፊቱም ክፍያዎች ደንብና መመሪያን ተከትለው መፈፀም እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሣስበናል፡፡

3.3. <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት</u>

<u>ሂሣብ ብር 93897.44</u>

መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ የገዟቸው ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦላቸው ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈጻሚ ጽ/ቤት በብር 93897.44 የገዛው ዕቃ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ሳይቆረጥለት ተገኝቷል፡፡ የግዢ ሂሣቦች

በወጪ ከመመዝገባቸው በፊት የተገዙት ዕቃዎች ለንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸው ሊረጋገጥ እንደሚገባና የንብረት ገቢ ደረሰኝም ከወጪ ቫውቸሮች ጋር ተያይዞ መቀመጥ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

4. <u>የበጀት ሂሣብ</u>

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብ እና የበጀት ዓዋጅ መሠረት መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | ከበጀት በላይ የወጣ | | ያልተሠራበት በጀት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አስፈጻሚ ጽ/ቤት | -- | -- | 663466 | 37 |
| 2 | የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ድርጅት | 1903715 | 10 | 3053002 | 99 |
| 3 | የመንግሥት የልማት ድርጅቶች | -- | -- | 303695 | 31 |
| 4 | የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር | 138801 | 88 | 1391133 | 50 |
| 5 | የብሔራዊ ዕጽዋት ዘር ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ | 2434498 | 18 | 1437190 | 09 |
| 6 | የብሔራዊ ሚትዎሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት | 175123 | 70 | 17480002 | 41 |
| 7 | የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | -- | -- | 1855644 | 22 |
| 8 | የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ | -- | -- | 1634756 | 77 |
| 9 | የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ድርጅት | -- | -- | 474828 | 97 |
| | ድምር | 4652138 | 86 | 28293720 | 63 |

4.1. ከላይ እንደተመለከተው በዘርፉ ኦዲት በተደረጉ ዘጠኝ መ/ቤቶች ውስጥ ከበጀት በላይ የወጣ 4652138.86 እና ያልተሠራበት በጀት ብር 28293720.63 ተገኝቷል፡፡ በሥራ ላይ ስላልዋለው በጀት ኦዲት አስደራጊዎች በሰጡት መልስ በክፍት የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኛ ለመቅጠር አለመቻል፣ የሠራተኞች ከሥራ መልቀቅ፣ የግዢ ሂደት መጓተት፣ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሊጠናቀቁ አለመቻላቸው፣ የወጭ ብድርና ዕርዳታ በወቅቱ ሊለቀቅ አለመቻሉ የተፈቀደን በጀት በአግባቡ ለመጠቀም ካላስቻሉት ችግሮች ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

ከበጀት በላይ ስለወጣው ሂሣብ ደግሞ ቀደም ባለው የበጀት ዓመት የታዘዙ የሌተር ኦፍ ክሬዲት (L/C) ግዢዎች ዕቃው በበጀት ዓመቱ በመድረሱና ወጪውም በበጀት ዓመቱ በመመዝገቡ፣ የአገልግሎት ፈቃድ ክፍያ እና ለተሽከርካሪ ጥገና የበጀት ዝውውር ተጠይቆ የዝውውር ሂደቱ በመዘግየቱ ከበጀት በይ በወጪ ለመመዝገብ ያስገደዱ ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች እንደሆኑ ተገልጿል፡፡ ስለዚህ የመ/ቤቶች የበጀት ዝግጅት በበቂ ጥናት ላይ የተመረኮዘ መሆን እንዳለበትና ከበጀት በላይ ወጪ ማድረግ ደግሞ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያን ያልተከተለ አሰራር በመሆኑ መታረም እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

5. <u>ንብረት</u>

የመ/ቤቶች የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡

5.1 <u>ቋሚና አላቂ ዕቃዎች</u>

5.1.1 <u>የመንግሥት ቤቶች ሽያጭ አሰፈጻሚ ጽ/ቤት</u>

- የንብረት ግምጃ ቤት ኃላፊነትና የንብረት ምዝገባ ሥራ በአንድ ሠራተኛ ተደርቦ የሚሠራ መሆኑ፣
- የገንዘብ መሰብሰቢያ የገቢ ደረሰኞች በመዝገብ የማይመዘገቡ መሆኑ፣

5.1.2 <u>የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ</u>

- ለቋሚ ዕቃዎች አል( አል( የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ በመሆኑ የቋሚ ዕቃ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣

5.1.3 <u>የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣</u>

- የቋሚ ዕቃዎች ምዝገባ ያለመከናወኑና መለያ ቁጥር ያለመስጠቱ ፣
- የዕቃ ግምጃ ቤት ለረዥም ጊዜ በመታሸጉ ምክንያት የንብረት ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣

♦ የመ/ቤቱ መጋዘኖች ለዕቃ አቀማመጥ አመቺ ያለመሆናቸውና የዕቃዎች አቀማመጥ የተዘበራረቀ መሆኑ ፣

♦ የኢነርጂ ጥናትና ምርመራ ማዕከል ንብረት በማዕከሉ ግ/ቤት የሚቀመጥ ሲሆን፣

አገልግሎት የሚሰጡ እና የማይሰጡ ዕቃዎች ተለይተው ያለመያዛቸው፣

የንብረት ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣

የማዕከሉ መጋዘኖች ለዕቃዎች አቀማመጥና አጠባበቅ አመቺ ያለመሆን ናቸው ::

5.1.4 <u>የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣</u>

♦ ቋሚና አላቂ ንብረቶች ተለይተው መመዝገብ ሲገባቸው በአንድ መዝገብ ላይ ተመዝግበው መገኘታቸው፣

♦ የቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር አል( አል( ተደጋጋሚ ሆኖ መገኘቱ፣

5.1.5 <u>የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ</u>

5.1.5.1 የድርጅቱ ዋና ላብራቶሪ ንብረት አያያዝና አጠባበቅ፣

- የላብራቶሪው ንብረት ክፍል ኃላፊ የእቃ ምዝገባ ሥራ የሚሠሩ መሆኑ፣

- የላብራቶሪው ዕቃዎች በቢን ካርድ ላይ ከመመዝገብ በስተቀር የንብረት መዝገብ ያልተቋቋመ በመሆኑ እና የቀድሞው የላብራቶሪ ንብረት ክፍል ሠራተኛ ለተተኪው ሲያስረክቡ ያንቀሳቀሱት ንብረት አዲት ያለመደረጉ፣

5.1.5.2. የካርታና የህትመት ውጤቶች አያያዝና አጠባበቅ፣

የቤተመጻህፍት ኃላፊዎች ከንብረት ክፍል የተረከቡት የካርታ ብዛት እና የፊፀሙት ሽያጭ በአግባቡ ተመዝግቦ ባለመያዙ የቤተመጻህፍት

ኃላፊዎች ከተረከቡት ካርታ የተሸጠውንና ያልተሸጠውን ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ለማጣራት አለመቻሉ፣

5.1.5.3. የድርጅቱ የዕቃ ግምጃ ቤቶች ሁኔታ፣

- የድርጅቱ ዕቃ ግ/ቤቶች አሠራር ዕቃዎችን ከዝርፊያ መከላከል ከማይችል ጥንካሬ ከሌላቸው የግንባታ መሳሪያዎች የተሰራ መሆኑና አቀማመጣቸውም ለጥበቃና ለቁጥጥር በማያመች ሁኔታ ተበታትነው የሚገኙ በመሆኑ፣

- በድርጅቱ ጋራዥ ዋና ክፍል ሥር የሚገኘው የነዳጅ ክፍል ከዋናው መ/ቤት የሚረከበው የነዳጅና ቅባት መጠን የማይመዘገብ በመሆኑ ከወጪ ቀሪውን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

- የድርጅቱ የነዳጅና ቅባት ግ/ቤት ኃላፊ የማዕድን ሚኒስቴርን የነዳጅ ገቢና ወጪ የሚመዘግብ፣ የነዳጅ ግዥን እና ነዳጅ ወጪ እንዲሆን የነዳጅና ቅባት መጠየቂያ ቅጽ ላይ የሚፈርም በመሆኑ የነዳጅ ሂሣብ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አስተማማኝ ሆኖ አለመገኘቱ፣

- ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑና ዕቃዎች በዓይነታቸው ተለይተው ያለመመዝገባቸው፣ በኦዲት ከተደረሰባቸው ድክመቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲታረሙና ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ያለበት መሆኑን ለየመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 5.2 ተሽከርካሪ መኪናዎች፣

### 5.2.1 የብሔራዊ ሜቲዎሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት፣

- 6 ተሽከርካሪ መኪናዎች የባለቤትነት መታወቂያ /ሊብሬ/ ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ መሆኑ፣

- የሠሌዳ ቁጥር 4-20796 የሆነ ተሽከርካሪ መኪና በ1993 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ወቅት በነበረው የፀጥታ አለመረጋጋት ምክንያት ለሥራ ጉዳይ መስክ እንደወጣ የጠፋ ሲሆን ሊብሬው ብቻ የተገኘ መሆኑ፣

5.2.2 <u>የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣</u>

አስራ ስምንት ተሽከራካሪዎች በትውስት ለሌላ መ/ቤት በመስጠታቸው ያሉበትን ሁኔታ በኦዲቱ ወቅት ማጣራት ያልተቻለ ሲሆን አንድ ተሽከርካሪ ደግሞ የሠሌዳ ቁጥሩ የጠፋ መሆኑ ፣

5.2.3 <u>የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ</u>

42 ተሽከርካሪዎች በከፍተኛ ብልሽት፣ በመለዋወጫ እጥረት፣ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት በመስጠትና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ምክንያት ከአንድ እስከ ስድስት ዓመት ያለአገልግሎት የቆሙ መሆናቸው፣

የድርጅቱ ተሽከርካሪዎች ኪሎ ሜትር ቆጣሪ የማይሠራ በመሆኑ ለእያንዳንዱ መኪና የታደለው ነዳጅ በተጓዘው ኪሎ ሜትር ልክ መሆኑን ለማረጋገጥ የማይቻል መሆኑ፣

የድርጅቱን ተሽከርካሪዎች ሁኔታ የሚገልጽ የተሟላ የተሽከራካሪዎች ማህደር ያልተቋቋመ መሆኑ፣

6 ተሽከርካሪዎች ለሌላ መ/ቤት በትውስት የተሰጡ ሲሆን እስከ ኦዲቱ መጨረሻ ያልተመለሱ መሆኑ፣

በተሽከርካሪ መኪናዎች አያያዝና አጠባበቅ የታዩ ጎላ ጎላ የሉ ችግሮች ናቸው::

በመሆኑም አገልግሎት ሣይሰጡ የቆዩት ተሽከርካሪዎች ሁኔታቸው ተጣርቶ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉት እንዲጠገኑ ሊጠገኑ የማይችሉት ደንብና መመሪያ በሚያዘው መሠረት እንዲወገዱ፣ የነዳጅ አጠቃቀምን በተገቢው መንገድ ለመቆጣጠር እንዲቻል የተሽከርካሪዎች ኪሎ ሜትር ቆጣሪዎች እንዲሠሩ

ማስጠገን እንደሚገባ፣ የተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ ማህደር ተፈላጊ መረጃዎችን አሟልቶ እንዲይዝ መረጃዎችን ማሰባሰብ እንደሚያስፈልግ፣ በትውስት ተሰጥተው ያልተመለሱ ተሽከርካሪዎች ለማስመለስ ተገቢውን ክትትል ማድረግ እንደሚገባ፣ የሰሌዳ ቁጥሩ የጠፋ እና ሊብሬ የሌላቸው ተሽከርካሪዎች ጉዳይ ተጣርቶ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6. <u>ልዩ ልዩ</u>

<u>የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ድርጅት፣</u>

<u>የካርታ ሽያጭ ገቢን ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ</u>

ለሽያጭ የቀረበ የካርታ ስኬልና የዋጋ ተመን በዝርዝር ባለመገለፁ ከካርታ ሽያጭ የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን ለወደፊቱ አሰራሩ እንዲስተካከል በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

6.1. <u>የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ፣</u>

- ቦርዱ የውስጥ ኦዲት ክፍል ያላቋቋመ መሆኑ፣

- የልዩ ፈንድ ዓመታዊ መግለጫ (Financial Statement) የዓመቱን ወጪ ብቻ የሚያሳይ እንጂ የዓመቱን ገቢና ከወጪ ቀሪ የማያካትት መሆኑ፣

የተሰበሰበው ገቢ እና የተከፈለው ገንዘብ በየዕለቱ የማይመዘገብ መሆኑ፣

የደመወዝ ክፍያ ሊስት ማዘጋጀትና ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ በሂሣብና በጀት ክፍል ኃላፊው ብቻ የሚሠራ መሆኑ፣

በወጪ ማስመስከሪያ (ሞ/6) ላይ የተከፈለበት ቀን የማይሞላና የሂሣብ መደቡም ያለቦታው በእርሳስ የሚጻፍ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ የተመለከቱት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚስተካከሉበት መንገድ እንዲፈለግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.2. <u>የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር</u>

- የስልክ አገልግሎት ፍጆታ አገልግሎት ገደብ የሌለ መሆኑ፣
- የመ/ቤቱ የውስጥ ኦዲት አገልግሎት በ1992 በጀት ዓመት የሂሳብም ሆነ የንብረት ኦዲት አለማድረጉ ታውቋል፡፡

  በመሆኑም ከላይ የተመለከቱት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲታረሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.3. <u>የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ</u>

ከድርጅቱ የሕግ አገልግሎት በተገኘው መረጃ መሠረት ከሌሎች ድርጅቶችና ከድርጅቱ ሠራተኞች በዕዳ የሚፈለግ ብር 2126128.54 መኖሩ ታውቋል፡፡ ከዚህ ውስጥ የድርጅቱ ንብረት የሆነ የሠ.ቁ.3-111 ተሽከርካሪ መኪና በደረሰበት ግጭት ምክንያት ብር 3,763.00 ከድርጅቱ ወጪ ተደርጎ የተጠገነበት ገንዘብ ከአሽከርካሪው እንዲተካ በፍርድ ቤት በተወሰነው መሠረት ገንዘቡ ለድርጅቱ አለመተካቱ ታውቋል፡፡ በመሆኑም የድርጅቱ የሕግ አገልግሎትና የበላይ ኃላፊዎች ጉዳዩን በጥብቅ በመከታተል ገንዘቡን ገቢ ለማስደረግ አስፈላጊውን ጥረት እንዲያደርጉ በተላከው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
## የማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ
## የ1993 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

በፌዴራል መንግሥት በማህበራዊ አገልግሎት ዘርፍ ከሚገኙ መ/ቤቶች ውስጥ ፣

- የአምቦ እርሻ ኮሌጅ፣
- የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን መደበኛ በጀት
- የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንጂነሪንግ ፋኩልቲ፣
- የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ፣
- የአማኑኤል ሆስፒታል፣
- የመቀሌ ቢዝነስ ኮሌጅ
- የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ
- እድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት
- የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን
- የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን የ1992 በጀት ዓመት የጡረታ ፈንድ ሂሣብ

በአጠቃላይ የ10 መ/ቤቶች ሂሣቦች ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ለኦዲት ተደራጊዎች በየአድራሻቸው ተልኳል፡፡

መ/ቤቶች በሪፖርቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት፣ በኦዲት ውጤቱ ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው 7 መ/ቤቶች ዘግይተው መልስ የሰጡ ሲሆን 3 መ/ቤቶች ደግሞ መልስ ሳይሰጡ ቀርተዋል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተ/ራ/ቁ | የመ/ቤቱ ስም | በወቅቱ መልስ የሰጡ (✔) | ዘግይተው መልስ የሰጡ (✔) | መልስ ያልሰጡ (✔) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንጂነሪንግ ፋክልቲ | | ✔ | |
| 2 | የአማኑኤል ሆስፒታል | | | ✔ |
| 3 | የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ | | ✔ | |
| 4 | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | | | ✔ |
| 5 | የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ | | ✔ | |
| 6 | የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን (መደበኛ በጀት) | | ✔ | |
| 7 | የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን የ1992 በጀት ዓመት የጡረታ ፈንድ ሂሣብ | | ✔ | |
| 8 | የመቀሌ ቢዝነስ ኮሌጅ | | ✔ | |
| 9 | እድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት | | | ✔ |
| 10 | የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | | ✔ | |

በኦዲት ወቅት የታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች፣ የአሠራር ጉድለቶች እና የሂሣብ አያያዝ ስህተቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል::

1. <u>ጥሬ ገንዘብና የሠነድ ሂሣብ፣</u>

1.1 <u>የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 9747.04</u>

ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በአራቱ ብር 9747.04 ጉድለት ተገኝቷል:: ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል::

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንጂነሪንግ ፋክልቲ | 6647 | 58 |
| 2 | የአማኑኤል ሆስፒታል | 799 | 57 |
| 3 | እድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት | 928 | 21 |
| 4 | የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | 1371 | 68 |
| | ድምር | 9747 | 04 |

ለጉድለቱ ዋናው መንስኤ በጥሬ ገንዘብ ላይ በየጊዜው ቁጥጥር ባለመደረጉ መሆኑ ታውቋል:: በመሆኑም የጎደለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ላይ እንዲተካና ተመሣሣይ ጉድለት እንዳይደርስ ደግሞ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን ማጠናከር እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

1.2 <u>በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ ጥሬ ገንዘብ ብር 51,913.01</u>

የመ/ቤቶቹ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በሚገባ መጠበቁንና በመመሪያ ከተፈቀደው ብር 5000.00 በላይ በካዝና ውስጥ የማይቀመጥ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

በባህርዳር ዩኒቨርስቲ ኢንጂነሪንግ ፋክሊቲ ብር 19,033.01

በአማኑኤል ሆስፒታል ብር 32,880.00

በድምሩ ብር 51,913.01

በካዝና እንዲቀመጥ ከተፈቀደው በላይ ተገኝቶ ተቆጥሯል።

በመመሪያው መሠረት ከብር 5000.00 በላይ በካዝና እንዳይቀመጥና ለወደፊቱም ተገቢው ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 1.3 ውዝፍ የሠነድ ሂሣብ ብር 373,271,742.12

1.3.1 ኦዲት ከተደረጉት 10 መ/ቤቶች ውስጥ በሰባቱ ብር 373,271,742.12 ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ተገኝቷል። ውዝፍ የሠነድ ሂሣብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | 333,365 | 96 |
| 2 | የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንጂነሪንግ ፋክልቲ | 47,658 | 85 |
| 3 | የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ | 12,255 | 70 |
| 4 | የአማኑኤል ሆስፒታል | 11,757 | 21 |
| 5 | እድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት | 134,734 | 15 |
| 6 | የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | 45,735 | 05 |
| 7 | ማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን የ1992 በጀት ዓመት የጡረታ ፈንድ ሂሳብ | 372,686,235 | 20 |
| | ድምር | 373,271,742 | 12 |

በውዝፍ ከተመለከተው ሂሳብ ውሰጥ ብር 372,686,235.20 የማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን በበጀት ዓመቱ ለአበልና ለአስተዳደር አገልግሎት ክፍያ እንዲውል ለተለያዩ የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት፣ የፋይናንስ ጽ/ቤቶች እና ለባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በየወሩ የተላከና ከ1 ወር እስከ 8 ወር ለሚደርስ ጊዜ ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ ታውቋል።

ይሁን እንጂ የሰነድ ሂሣብ በወቅቱ መወራረድ እንዳለበት በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/89 የተደነገገ በመሆኑ መ/ቤቶቹ ውዝፉን የሰነድ ሂሣብ በአስቸኳይ እንዲያወራርዱና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና መመዝገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1 <u>ህጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ የተሰበሰበ ገቢ ብር 90,384.62</u>

የመንግሥት ገቢ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/89 አንቀፅ 6 ከንዑስ አንቀፅ 1 እስከ 3 እና ደንብ ቁጥር 17/89 አንቀፅ 32/1 መሠረት መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በአምቦ እርሻ ኮሌጅ :-

| | | |
|---|---|---|
| . በነጭ ወረቀት የተሰበሰበ የአደራ ገቢ.... | ብር | 5,000.00 |
| . በኮሌጁ የመዝናኛ ክበብ ደረሰኝ የተሰበሰበ የጨረታ ማስከበሪያ ገቢ... | ብር | <u>85,384.62</u> |
| በድምሩ | ብር | <u>90,384.62</u> |

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በማያውቀውና ህጋዊ ባልሆነ የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ተሰብስቦ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም አሰራሩ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ ከሚያዘው ውጪ በመሆኑ እንዲታረም እና ለገቢው ሕጋዊ ደረሰኝ እንዲቆረጥለት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.2 <u>ደረሰኝ ሳይቆረጥለት የተሰበሰበ ገቢ ብር 26,636.00</u>

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ለአየር ቲኬት መግዣ ከተከፈለው ውስጥ ተራፊው ብር 26,636.00 የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት በገቢ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ለሂሳቡ ተገቢው ደረሰኝ እንዲቆረጥለት እና ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.3 <u>ያልተሰበሰበ ሂሣብ ብር 573,882,.58 እና የአሜሪካን ዶላር 14,646.50</u>

የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ

እድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት ከክልሎች በበጀት ዓመቱ ገቢ ማድረግ የሚገባውን ብር 573,882.58 ክልሎች የሚፈለግባቸውን ሂሳብ በወቅቱ ገቢ ባለማድረጋቸው ምክንያት ያለመሰብሰቡ በኦዲት አስደራጊዎች የተገለፀ ሲሆን የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ደግሞ ከአሸነፉ አትሌቶች መሰብሰብ የሚገባውን 14,646.50 የአሜሪካን ዶላር አለመሰብሰቡ ተረጋግጧል።

ስለሆነም ለወደፊቱ ተሰብሳቢ ሂሣብ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰብ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 2.4 <u>የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት የገቢ ሂሣብ ብር 34,705,074.95</u>

በገቢ የተመዘገበው ሂሳብ ሊሰበሰብ በሚገባው ልክ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን የ1992 በጀት ዓመት የጡረታ ፈንድ ሂሣብ ለብር 34,705,074.95 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብለት በገቢ ተመዝግቦ ተገኝቷል። ይኸውም ገንዘቡ ባንክ ገቢ የተደረገበት ደረሰኝ፣ የደመወዝ መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ /ገ/በወ/11/1 እና ቅጽ ጡ/17 ያልቀረበ በመሆኑ የተመዘገበው ገቢ በተሰበሰበው ልክ መሆኑን ማጣራት አልተቻለም። ለወደፊቱ ማስረጃዎች ተሟልተው እንዲያዙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 2.5 <u>ከመኪና ኪራይ የተሰበሰበ ገቢ ብር 25,200.00</u>

የአምቦ እርሻ ኮሌጅ የሰበሰበው ገቢ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/89 አንቀጽ 6 እና 14 ላይ በተደነገገው መሠረት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የኮሌጁን አነስተኛ አውቶቡስ ለአምቦ ማዕድን ፋብሪካ በማከራየት በውስጥ ገቢ ደረሰኝ የተሰበሰበ ብር 25,200.00 ተገኝቷል።

የአገልግሎት ዋጋው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ያልፀደቀና መኪና በማከራየት ገቢ መሰብሰብ እንደሚችል በመንግስት ያልተፈቀደለት በመሆኑ አሰራሩ ተገቢ ስላልሆነ በዚህ መልክ ገቢ ለመሰብሰብ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ፈቃድ መገኘት እንዳለበት፣እንዲሁም፣ ማንኛውም በመንግሥት ስም የሚሰበሰብ ገቢ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያውቀው ደረሰኝ ተሰብስቦ ወደተጠቃለለው ፈንድ ገቢ መደረግ እንዳለበት በፋይናንስ አዋጅና ደንብ ላይ የተደነገገ በመሆኑ የተሰበሰበው ብር 25,200.00 ወደ ተጠቃለለው ፈንድ ገቢ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 2.6 <u>ከተለያዩ መ/ቤቶችና ግለሰቦች የሚፈለግ ዕዳ ብር 2,416,884.44</u>

በማሕበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ከ1967 ዓ.ም በፊት የመላው አፍሪካ ሥጋ ደዌ መከላከያ ድርጅት ሠራተ→ች በኢትዮጵያ መድን ድርጅት የተጠራቀመ የፕሮቪደንት ፈንድ ሂሣብ ብር 285,533.02፣ እንዲሁም ደመወዝና የጡረታ አበል አጣምረው ሲወስዱ ከነበሩ ግለሰቦች ተመላሽ የሚደረግ ብር 131,351.42 የጡረታ ፈንድ ሂሣብ፣ በሲቪል አውቶኖመስ ኢንቨስትመንት ከሚታየው ሂሣብ ውስጥ ለኢትዮጵያ አየር ሀይል ጠቅላይ መምሪያ እስከ ግንቦት /87 ከነወለዱ ተከፍሎ እንዲጠናቀቅ በብድር የተሰጠ ብር 2,000,000 በድምሩ ብር 2,414,884.42 ለባለሥልጣኑ ገቢ መደረግ ያለበት ሂሣብ መኖሩ ታውቋል:: በመሆኑም የሚመለከታቸው ግለሰቦችና መ/ቤቶች ገንዘቡን ለባለሥልጣኑ ገቢ እንዲያደርጉ ጠንካራ ክትትል መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ መ/ቤቱ በላከው መልስ ብር 2,000,000 ከነወለዱ ተመላሽ የተደረገ መሆኑ ተገልጿል::

2.7 <u>ተሰብሳቢ ሂሣብ</u>

- የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ ብር 1,126,814.31 ተሰብሳቢ ሂሣብ እንዳለው የታወቀ ቢሆንም ዝርዝር የሂሳብ ቋት ያልተዘጋጀ በመሆኑ ሂሣቡን ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉና
- የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን የ1992 በጀት ዓመት የጡረታ ፈንድ ሂሳብ በሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ከሲቪልና ከድርጅት መሰብሰብ ካለበት የፈንድ ሂሣብ ብር 10,487,573.64 ውስጥ ብር 7,294,988.88 ያለአግባብ በተሰብሳቢነት መመዝገቡ ታውቋል::
- የአ.አ ንግድ ሥራ ኮሌጅ ለተሰብሳቢ ሂሳብ ተገቢው የሂሳብ ቋት በማዘጋጀት ምዝገባ እንዲከናወንና ለማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ደግሞ ከፈንድ ለፈንድ መዛወር የሚገባው በመሆኑ በፈንዱ አይነት ተለይቶ መመዝገብ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

3. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በማስረጃ የተደገፉ መሆናቸውን፣ ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት መፈፀማቸውንና፣ ጉልህ ግድፈቶች አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል::

3.1 <u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ብር 22,625,808.41</u>

ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በአምስቱ የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ ብር 22,625,808.41 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | 1,406,006 | 80 |
| 2 | የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን | 19,251,170 | 00 |
| 3 | የአማኑኤል ሆስፒታል | 853,929 | 21 |
| 4 | እድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት | 1,081,620 | 60 |
| 5 | የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | 33,081 | 80 |
| | ድምር | 22,625,808 | 41 |

ከተጠቀሰው ሂሣብ ውስጥ የጨረታ ሰነድ ያልቀረበለት፣ የደመወዝ ተመላሽና ከመንግሥት ሠራተኞች መቀጫ እንዲሁም የሥራ ግብር ተሰብስቦ በባንክ በኩል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተላከ ቢሆንም ገንዘቡ ለመድረሱ ሞ/64 ያልቀረበለት፣ በተቋራጭ ስም የታተመ ደረሰኝ መቅረብ ሲገባው በወጪ ማስመስከሪያ ሞ/6 ብቻ የተከፈለ እና የጡረታ ክፍያ መጠየቂያ ያልቀረበለት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡ ስለሆነም ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ማሰረጃዎች የተሟሉ መሆናቸው መረጋገጥ እንዳለበትና ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡

3.2 <u>በብልጫ የተከፈለ ሂሣብ ብር 2,504.20</u>

በአትሌቲክስ ፌዴሬሽን አትሌቶች ወደ ሀንጋሪ ሲሄዱ ለቲኬት መግዣና ለምግብ አገልግሎት ብር 2,504.20 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ገንዘቡ ከሚመለከተው ክፍል እንዲመለስና ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት የቀረበው ማስረጃ መጣራት እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3 <u>ያለአግባብ የተከፈለ ሂሣብ ብር 80,491.07</u>

በበጀት ዓመቱ ክፍያዎች ደንብና መመሪያን ጠብቀው የተፈፀሙ መሆናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ያለአግባብ የተከፈለ ብር 80,491.07 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአማኑኤል ሆስፒታል | 235 | 50 |
| 2 | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | 22,532 | 17 |
| 3 | የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ | 19,650 | 00 |
| 4 | ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ኢንጂነሪንግ ፋክሊቲ | 38,073 | 40 |
| | ድምር | 80,491 | 07 |

ከዚህ ውስጥ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣ ሣይቀነስ የቀረ የሥራ ግብር፣ ያለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል የሚሉት ይገኙበታል፡፡
አሠራሩ ደንብና መመሪያን ያልተከተለ በመሆኑ እንዲታረምና ያለአግባብ የተከፈለውም ሂሣብ ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3.4 <u>የግዥ መመሪያን ሳይጠብቅ የተፈፀመ ግዢ ብር 539,576.26</u>

በበጀት ዓመቱ የተፈፀሙትን ግዢዎች የዕቃና አገልግሎት ግዢ መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከመመሪያ ውጭ የብር 539,576.26 ግዢ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገነዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንጂነሪንግ ፋኩልቲ | 180,872 | 26 |
| 2 | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | 248,233 | 12 |
| 3 | የመቀሌ ቢዝነስ ኮሌጅ | 26,161 | 60 |
| 4 | የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ | 78,189 | 28 |
| 5 | የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | 6120 | 00 |
| | ድምር | 539,576 | 26 |

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡና በጨረታ አሸናፊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተፈፀመ ፣ የጨረታ ማስታወቂያ መውጣት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ ብቻ የተፈፀመ እና የጨረታ ማስታወቂያም ሆነ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይቀርብ የተፈፀመ ግዥ ይገኙበታል:: ለወደፊቱ አሰራሩ እንዲታረምና ድርጊቱን በፈፀሙ ሠተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል::

3.5 <u>የአፈፃፀም መመሪያና ደንብ ሣይኖርው</u>

<u>የተፈፀመ ክፍያ ብር 36,408.00</u>

በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የውስጥ ገቢ አጠቃቀምን በተመለከተ ወጪን ሰለመፍቀድና ክፍያን ስለመፈፀም የወጣ ደንብ ወይም ዝርዝር የአሠራር መመሪያ ሣይኖረው የጥናትና ምርምር ሥራ ላከናወኑ የኮሌጁ ሠራተኞች የተከፈለ ብር 36,408.00 ተገኝቷል :: ከተከፈለው ገንዘብ ላይም በሕግ በተደነገገው መሠረት የሥራ ግብር ገቢ አለመሰብሰቡ ታውቋል:: በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ አጠቃቀምን በተመለከተ መመሪያ ሊኖረው እንደሚገባና ያልተቀነሰው ሥራ ግብር ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተቀንሶ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሣሥበናል::

3.6 <u>ለባለጥቅሞቹ ለመድረሱ ማስረጃ ያልቀረበለት ብር 109,579.54</u>

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ለአትሌቲክስ ባለሙያዎችና ተሳታፊዎች ለምግብና ለኪስ ገንዘብ የተከፈለ ብር 10,176.60 እና ለክልል ስፖርት ም/ቤቶች በባንክ በኩል የተላከ ብር 99,402.94 ለባለሙያዎቹ ለመድረሱ ወይም አገልግሎት ለማግኘታቸው ሳይረጋገጥ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል::

አሰራሩ ትክክል ስላልሆነ ተፈላጊ ማስረጃዎች እንዲቀርቡና ከወጪ ማስመስከሪያ ጋር እንዲያያዙ ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል::

3.7 <u>ተከፋይ ሂሣብ ብር 226,230.21</u>

በአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ በተለያዩ የሂሣብ አርዕስቶች በተከፋይነት የተያዘ ብር 226,230.21 ለማን እንደሚከፈል የሚገልጽ ዝርዝር ንዑስ የሂሣብ ቋት ባለመዘጋጀቱ ምክንያት ሂሣቡን ኦዲት ለማድረግ ሳይቻል ቀርቷል:: ለወደፊቱም ለተከፋይ ሂሣብ ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳዩ ንዑስ የሂሳብ ቋት

እንዲዘጋጁና ከሂሣብ መግለጫዎች ጋር ተያይዘው መቀመጥ እንደሚገባቸው በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

3.8 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት</u>

<u>ሂሣብ ብር 507,124.55</u>

የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ በብር 2,417.45 ለገዛው የሞባይል ስልክ እና ከውጭ አገር በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የተገዙ ብር 485,889 የሚያወጡ ዕቃዎች፣

እድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት ለተማሪዎች አገልግሎት በብር 15,212.10 የተገዛ መድሀኒት ፣

- የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በብር 3,606 የተገዙ ልዩ ልዩ ዕቃዎች፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸውና በንብረትነት ሳይመዘገቡ ተገኝተዋል፡፡ ስለሆነም ለዕቃዎቹ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲቆረጥና በንብረት መዝገብ እንዲመዘገቡ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. <u>የንብረት ሂሳብ፣</u>

<u>በአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮለጅ</u>

ለአገልግሎት መስጫ በየጊዜው ወጪ የተደረጉት ዕቃዎች በደንቡ መሠረት መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸውና ዕቃዎቹን ለመቆጣጠር የሚያስችል መዘክር ያልተቋቋመ መሆኑ፣

ለሥራ አገልግሎት ለየክፍሉ የተሰጡት ቋሚ ዕቃዋች ወጪ የሚሆኑት በትውስት ፎርም አማካኝነት መሆን ሲገባው በንብረት ወጪ ደረሰኝ መሆኑ፣

<u>በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣</u>

ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ፣

<u>ዕድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት</u>

አላቂ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ አለመቋቋሙ

በወጪ ያልተመዘገበ 168 ጥንድ አንሶላና 60 ብርድልብስ መኖሩ፣

የተማሪዎችን ቀለብ ተረካቢና መዝጋቢ አንድ ሠራተኛ መሆኑ፣ታውቋል፡፡

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት የአሰራር ድክመቶች እንዲታረሙ በላክነው ሪፖርት አሳሰበናል፡፡

<u>በአትሌቲክስ ፌዴሬሽን</u> የንብረት ወጪ ማዘዣ ያልቀረበለት ብር 2,750.86 የሚያወጡ ሰባት (7) ዓይነት ዕቃዎች ወጪ ያደረገው ሠራተኛ ለመቀበሉ ሳይፈርምና የንብረት ወጪ ማዘዣ ሳይቀርብ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ወጪ ተደርጎ

ተገኝቷል፡፡ የንብረቱ ወጪነት ተጣርቶ በሚመለከታቸው ሠራተኞች እንዲፈረም ማዘዣውም እንዲያያዝ በላክነው በሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የተሽከርካሪ ሁኔታ</u>

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንጂነሪንግ ፋክልቲ ካሉት 24 ተሽከርካሪዎች ውስጥ 15 በተለያየ ብልሽት ምክንያት የቆሙና አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡ የሰሌዳ ቁጥር 4-00237 ፔጆ መኪና የካቲት 1983 ዓ/ም የጠፋና የደረሰበት የማይታወቅ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በብልሽት ምክንያት የቆሙት ተጠግነው በሥራ ላይ የሚውሉበት መንገድ እንዲፈለግ እና ከጥቅም ውጭ የሆኑት ደግሞ አግባብ ባለው የመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ፣ የጠፋው ተሽከርካሪ ሁኔታም ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ አሰፈላጊው ሁሉ እንዲፈፀም በተላከው ሪፖርት አሣስበናል፡፡

5 <u>የበጀት አጠቃቀም፣</u>

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ያዋሉ፣ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ ወጪ አለመደረጉን እንዲሁም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የሚገኘውን ሂሣብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | ያልተሠራበት በጀት | | ከበጀት በላይ የወጣ | | ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአምቦ እርሻ ኮሌጅ | 742,656 | 11 | 356,677 | 12 | 127,450 | 41 |
| 2 | የባህርዳር ዩኒቨርስቲ ኤንጂነሪንግ ፋኩልቲ | 471,126 | 79 | 166,557 | 79 | 96,793 | 30 |
| 3 | እድገት የጎልማሶች አዳሪ ት/ቤት | 1,791,643 | 76 | 417,504 | 88 | - | - |
| 4 | የኢትዩጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን | 3,870,820 | 52 | - | - | - | - |
| 5 | የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ | - | - | - | - | 1,922,109 | 98 |
| 6 | የአማኑኤል ሆስፒታል | 2,527,566 | 36 | | | 8,065 | 25 |
| 7 | የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ | | | | | 1,763,314 | 52 |
| 8 | የመቀሌ ቢዝነስ ኮሌጅ | 1,095,469 | 27 | 55,391 | 54 | - | - |
| | ድምር | 10,499,282 | 81 | 996,131 | 33 | 3,917,733 | 46 |

ከላይ እንደተመለከተው ያልተሰራበት በጀት ብር 10,499,282.81 ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገ ብር 996,131.33 ደግሞ በወቅቱ ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ ብር 3,917,733.46 ተገኝቷል።

የመ/ቤቶች የበጀት ዝግጅት በበቂ ጥናት የተደገፈና ሊተገበር የሚችል መሆን እንዳለበት፣ በበጀት ዓዋጁ ከተፈቀደው በላይ መጠቀም ደግሞ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብን ያልተከተለ አሰራር መሆኑንና ፈሰስ ያልተደረገውም ከወጪ ቀሪ በአስቸኳይ ፈሰስ እንዲሆን በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል።

6. <u>ልዩ ልዩ</u>

<u>የአምቦ እርሻ ኮሌጅ፣ የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ</u>

<u>ኮሌጅ እና የባህርዳር ዩኒቨርስቲ ኢንጂነሪንግ ፋክልቲ</u>

የውስጥ ገቢ በየኮሌጆቹ ስም በታተመ የገቢ ደረሰኝ የሚሰበሰብ መሆኑ እና ኮሌጆቹ በከፊል የድርብ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን የሚጠቀሙ ቢሆንም የሂሳብ አያያዝ ማኑዋል የሌላቸው መሆኑ ታውቋል። ኮሌጆች የሚሰበስቡት የውስጥ ገቢ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ተገቢውን ፈቃድ ማግኘት እንዳለባቸውና የሂሳብ አያያዝ ስርዓታቸውንም የሚገልፅ ማኑዋል ሊኖራቸው እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

<u>አማኑኤል ሆስፒታል</u>

የዕርዳታ ሂሣብ ወርኃዊ ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የማይቀርብ መሆኑ፣

የተራድኦ ሂሣብ የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ የማይዘጋጅ መሆኑ፣

<u>የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን</u>

አለም አቀፍ ውድድር ከተካሄደባቸው ሀገሮች ወደ ሀገር ቤት ለሚደወሉ የስልክ ጥሪዎች አግባብ ባለው ሠራተኛ ለሥራ ጉዳይ የተደወለ ለመሆኑ ማረጋገጫ ሳይቀርብ ሂሣቡ የሚወራረድ መሆኑ፣

ከኮሚሽኑ የስፖርት ትጥቅ ግ/ቤት ለሚመጡ ልዩ ልዩ የስፖርት ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደሰኝ የማይቆረጥ ሲሆን ለተጠቃሚዎች ሲታደልም የንብረት ወጪ ደረሰኝ የማይቆርጥ መሆኑ

ብር 31,118 የሚያወጡ 6 ዕቃዎች በብልጫ 653.50 የሚያወጡ ዕቃዎች በማነስ መታየታቸው፣

ዕድገት የኀልማሶች አዳሪ ት/ቤት

ት/ቤቱ የራሱ የሆነ መተዳደሪያ ደንብ ወይም መቋቋሚያ አዋጅ የሌለው መሆኑ፣

ታውቋል::

የማህበራዊ ዋስና ባለሥልጣን የመደበኛ በጀት

የ1992 በጀት ዓመት የጡረታ ፈንድ

በ1992 በጀት ዓመት እንዲስተካከሉ በኦዲት ሪፖርት አስተያየት የተሰጠባቸው ግኝቶች በ1993 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት ሳይስተካከሉ መገኘታቸው፣

የጡረታ ፈንዶችን በአዲስ መልክ ለማቋቋም የሚያስችል የአክችዋሪ ጥናት ያልፀደቀ በመሆኑ የወደፊት የጡረታ ባለመብቶች ተከፋይ ዕዳ እንዲሁም የመጠባበቂያ ሂሣብ በተዘጋጀው የሂሣብ መግለጫ ላይ ያልተካተተ መሆኑ

የሂሣብ እንቅስቃሴ የሌለው የባንክ ሂሣብ በመመሪያ መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ወይም እንዲዘጋ ያልተደረገ መሆኑ

መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 38/88 በአዲስ መልክ ተቋቁሞ የጡረታ መዋጮ የመሰብሰብና አበል የመክፈል ኃላፊነት ማከናወን ሲጀምር ቀደም ሲል በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ጠቅላላ የተሰበሰበ የጡረታ ገቢና ለጡረተኞች የተከፈለ አበል ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ተጣርቶ ርክክብ በመፈፀም ሥራ መጀመር ሲገባው ፈንዱን ለማቋቋም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተገኘ ገንዘብ መነሻነት ሥራውን የጀመረ መሆኑና ትክክለኛው ከወጭ ቀሪ አለመታወቁ፣

ለሲቪል አውቶኖመስ የጡረታ ፈንድ ሂሣብ እራሱን የቻለ የሂሣብ መግለጫ መቅረብ ሲኖርበት ከሲቪል ጡረታ ፈንድ ሂሣብ ጋር ተጠቃሎ የቀረበ መሆኑ፣

በመንግሥት ፈንድ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ለቋሚ ዕቃ መግዣ የወጣ ሂሳብ ዕቃው በተገዛበት በጀት ዓመት በሙሉ በወጪ መመዝገብ ያለበት ቢሆንም ብር 134,172.59 የእርጅና ቅናሽ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ ፣

ከላይ  የተጠቀሱት የአሰራር ድክመቶች እንዲታረሙና ችግሮቹን ለማስወገድ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

**<u>የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ</u>**

**<u>የአስተዳደር አገልግሎት ዘርፍ</u>**

# የ1993 በጀት ዓመት ሪፖርት

በፌዴራል መንግሥት በአስተዳደር አገልግሎት ዘርፍ ሥር በሚገኙ አገልግሎቶች በ1993 በጀት ዓመት ኦዲት ሊደረጉ ፕሮግራም ከተያዘላቸው ኦዲቶች ውስጥ፣

- የመከላከያ ሚኒስቴር ፋይናንስ መምሪያ፣
- የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ፣
- የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት
- የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ም/ቤቶች የኦድዮቪዥዋል ዕቃዎች ግዥ
- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት
- የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት
- የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያ
  - የዋና ገንዘብ ያዥ የሣጥን ሂሣብ
  - የ110ኛ ኮር
  - የ107ኛ ኮር
- የፍትህ ሚኒስቴር አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት
- ጋፋት ኢንጂነሪንግ ፋብሪካ

በአጠቃላይ 9 ሂሣቦች ኦዲት ተደርገው ሪፖርቱ ለኦዲት ተደራጊዎች በየአድራሻቸው ተልኳል፡፡

የ1993 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ተደርጎ፣ በሪፖርቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት፣ በኦዲት ውጤቱ ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው ሁለት (2) መ/ቤቶች በወቅቱ ሁለት (2) መ/ቤቶች ዘግይተው መልስ የሰጡ ሲሆን አምስት (5) መ/ቤቶች ደግሞ መልስ ሳይሰጡ ቀርተዋል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| | | በወቅቱ | ዘግይተ | መልስ |
|---|---|---|---|---|

| ተ/ራ | የመ/ቤቱ ስም | መልስ የሰጡ (✓) | ው መልስ የሰጡ (✓) | ያልሰ ጡ (✓) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የመከላከያ ሚኒስቴር ፋይናንስ መምሪያ | | ✓ | |
| 2 | የዓየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | ✓ | | |
| 3 | የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት | | ✓ | |
| 4 | የሕዝብ ተወካዬችና የፌዴሬሽን ም/ቤቶች የኦዲዮቪዥዋል ዕቃዎች ግዥ | | | ✓ |
| 5 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | | | ✓ |
| 6 | የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት | | | ✓ |
| 7 | የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያ<br>የዋና ገንዘብ ያዥ የሜጥን ሂሣብ<br>የ110ኛ ኮር<br>የ107ኛ ኮር | | | ✓ |
| 8 | የፍትሕ ሚኒስቴር አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | ✓ | | |
| 9 | ጋፋት ኢንጂነሪነግ ፋብሪካ | | | ✓ |

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የሰነድ ሂሣብ</u>

1.1 <u>የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 30625.22</u>

በዘርፉ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች በ3ቱ መ/ቤቶች ብር 3062522 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 2810 | 04 |
| 2 | የጋፋት ኢንጂነሪንግ ፋብሪካ | 10314 | 44 |
| 3 | የፍትህ ሚኒስቴር | 17500 | 74 |
| | ድምር | 30625 | 22 |

ከጉድለቱ መንስኤዎች መካከል ዋናው በጥሬ ገንዘብ መዝገብ ላይ በየጊዜው ቁጥጥር አለመደረጉ ነው፡፡ በመሆኑም የጎደለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ላይ እንዲተካና ተመሳሳይ ጉድለት እንዳይደርስ ደግሞ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን ማጠናከር እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 <u>በካዝና ውስጥ ተገኝቶ ስለተቆጠረው የጥሬ ገንዘብ</u>

ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ6ቱ ብር 531237.98 በካዝና ተገኝቶ ተቆጥሯል። ዝርዝሩ ቀጥሎ ተመልክቷል።

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ ብር | |
|---|---|---|---|
| 1 | የ107ኛ ኮር | 12675 | 12 |
| 2 | ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 12588 | 00 |
| 3 | ፍትህ ሚኒስቴር | 177447 | 10 |
| 4 | የጋፋት ኢንጂነሪንግ ፋብሪካ | 9132 | 80 |
| 5 | የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት | 8682 | 32 |
| 6 | የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 310762 | 64 |
| | ድምር | 531287 | 98 |

በመመሪያው መሠረት ማንኛውም መ/ቤት ከብር 5000.00 በላይ ጥሬ ገንዘብ በሣጥን ማሳደር እንደሌለበትና የተሰበሰበው ገቢ ወዲያውኑ ወይም በማግሥቱ ባንክ ገቢ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

1.4 <u>ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ብር 163407676.29</u>

ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች በስምንቱ ብር 163407676.29 ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ተገኝቷል።

ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው።

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የ110ኛ ኮር | 35043741 | 88 |
| 2 | የ107ኛ ኮር | 59654324 | 73 |
| 3 | የመከላከያ ሚኒስቴር ፋይናንስ መምሪያ | 4775 | 02 |
| 4 | አየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 49906484 | 91 |
| 5 | ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 17848121 | 81 |
| 6 | ፍትህ ሚኒስቴር | 305225 | 18 |
| 7 | ጋፋት ኢንጂነሪንግ ፋብሪካ | 644510 | 76 |
| 8 | የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት | 492 | 00 |
| | ድምር | 163407676 | 29 |

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 38/1 መሠረት ለሥራ ማስኬጃ በሠነድ የወጣ ሂሣብ በሰባት የሥራ ቀናት፣ የደመወዝ ሰነድ ሂሣብ ደግሞ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ መወራረድ እንዳለበት የታዘዘ ቢሆንም ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ከላይ የተመለከተው ውዝፍ ሂሣብ ሊገኝ ችሏል። ስለሆነም

መ/ቤቶቹ ውዝፉን የሰነድ ሂሣብ በአስቸኳይ እንዲያወራርዱ ለወደፊቱም በደንቡ መሠረት እንዲሰራ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

2. <u>የወጪ ሂሣብ</u> :–

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በማስረጃ የተደገፉ መሆኑን፣ ክፍያዎች ደንቦችና መመሪያዎች ተጠብቀው መከፈላቸውንና መመዝባቸውን እንዲሁም ስህተቶችና ግድፈቶች አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል።

2.1 <u>የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ እና የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይቀርብ የተፈፀመ ግዥ</u>

ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ6ቱ የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ የብር 12845583.03 እና የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይቀርብ የብር 681,033.38 ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል። የመ/ቤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ተመልክቷል።

| ተ/ራ | የመ/ቤቱ ስም | የጨረታ ማስታወቂያ ያልወጣለት | | የዋጋ ማወዳደሪያ ያልቀረበለት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የ110ኛ ኮር | 1153636 | 20 | 141922 | 25 |
| 2 | የ107ኛ ኮር | 2797709 | 43 | 236185 | 69 |
| 3 | የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 59248 | 21 | 225100 | 35 |
| 4 | የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 7290585 | 54 | 19035 | 00 |
| 5 | የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት | 990403 | 65 | 58790 | 09 |
| 6 | የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ም/ቤቶች ጽ/ቤት (የኦዲዮ ቪዥዋል ዕቃ ግዥ) | 554000 | 00 | - | - |
| | ድምር | 12845583 | 03 | 681033 | 38 |

አሠራሩ ስለግዥ አፈፃፀም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያወጣውን መመሪያ ያልተከተለ በመሆኑ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና ለወደፊቱ መመሪያው ተጠብቆ እንዲሠራ በተላከው ሪፖርት አሣስበናል።

## 2.2. የተሟላ የወጪ ማስረጃ

**ያልቀረበለት ብር 1,080,314.70**

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገቡት ሂሣቦች የተሟላ የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ የተመዘገበ ሂሣብ ብር 1,080,314.70 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | 110ኛ ኮር | 489,151 | 90 |
| 2 | 107ኛ ኮር | 73,056 | 45 |
| 3 | የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት | 264,854 | 10 |
| 4 | የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት | 92,194 | 21 |
| 5 | የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 26,235 | 62 |
| 6 | ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 133,961 | 00 |
| 7 | ጋፋት ኢንጅነሪንግ ፋብሪካ | 861 | 42 |
| | ድምር | 1,080,314 | 70 |

ተሟልተው ያልቀረቡት ማስረጃዎች አይነት በርካታ ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ የጥገና ጥያቄ ያልቀረበለት፣ ያለወጪ ማዘዣ የተከፈለ፣ የዕቃው ብዛት በንብረት ገቢ ደረሰኝ ላይ ያልተገለፀ፣ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ስምምነት ያልቀረበለት የደመወዝ ክፍያ ፣የውክልና ደብዳቤ ያልቀረበለትና የግዢ ወይንም የአገልግሎት ውል ያልቀረበለት የሚሉት ይገኙበታል፡፡ መ/ቤቶች ሂሳባቸውን ከመመዝገባቸው በፊት ማስረጃዎች ተሟልተው መቅረባቸው መረጋገጥ እንዳለበት እና ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሣስበናል፡፡

## 2.3. የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ ብር 23204808.16 እና የአሜሪካ ዶላር 118462.97

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ተገቢው ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ኦዲት ሲደረግ በስድስት መ/ቤቶች የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት የተመዘገበ ሂሣብ ብር 23204808.16 እና 118462.97 የአሜሪካ ዶላር ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ ብር | | የአሜሪ ካዶላር | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 10490028 | 47 | - | - |
| 2 | የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 4992794 | 91 | 118462 | 97 |
| 3 | የ107ኛ ኮር | 4305972 | 81 | - | - |
| 4 | የ110ኛ ኮር | 3285015 | 17 | - | - |
| 5 | የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት | 124500 | 00 | - | - |
| 6 | የፍትህ ሚኒስቴር | 6496 | 80 | - | - |
| | ድምር | 23204808 | 16 | 118462 | 97 |

የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ የተመዘገቡ ሂሣቦች አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች እንዲቀርቡላቸው፣ ካልሆነ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊው ክትትል መደረግ እንዳለበትና ለወደፊቱም የወጪ ማስረጃ መቅረቡ ሳይረጋገጥ ምዝገባ እንዳይከናወን በላክነው ሪፖርት አሣስበናል፡፡

2.4 <u>ፈሰስ ያልተደረገ የሥራ ግብር</u>

<u>ሂሣብ ብር 21119.59</u>

ከመንግሥት ሠራተኞች የተሰበሰበው የሥራ ግብር ሂሣብ በወቅቱ ለሚመለከተው ክፍል ፈሰስ መደረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በሶስት መ/ቤቶች የተሰበሰበው የሥራ ግብር ብር 21119.59 ፈሰስ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተ/ራ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 593 | 95 |
| 2 | አየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 17991 | 22 |
| 3 | ጋፋት ኢንጂነሪንግ ፋብሪካ | 2534 | 42 |
| | ድምር | 21119 | 59 |

ስለሆነም የተሰበሰበው ገቢ ለሚመለከተው ክፍል በአስቸኳይ ፈሰስ እንዲሆንና ለወደፊቱም አሰራሩ እንዲታረም በላክነው ሪፖርት አሣስበናል፡፡

2.5 <u>የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ</u>

<u>የወጪ ሂሣብ ብር 2993803.94</u>

በወጪ የተመዘገበው ሂሣብ በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሁለት መ/ቤቶች ባለፉት ዓመታት ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ ብር 2993803.94 በዘመኑ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ብር 2991029.24

- የአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ........ብር 2774.70

ድምር ብር 2993803.94

አሰራሩ የበጀት አዋጁን፣ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብን ያልተከተለ መሆኑን በመግለጽ፣ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.6. <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት</u>

የመ/ቤቶች የግዥ አፈፃፀም መንግሥት ባወጣው ደንብና መመሪያዎች መሠረት መከናወኑን፣ የተገዙትም ዕቃዎች በንብረት ደረሰኝ ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በብር 6,460,051.81፣እንዲሁም 400,000.00 የካናዳ ዶላር እና 10,175.00 የጀርመን ማርክ የተገዙ ዕቃዎች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ለመሆናቸው ማረጋገጫ የንብረት ገቢ ደረሰኝ አልቀረበም፡፡ ዝርዝር ሁኔታውም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘብ ልክ |
|---|---|---|

| | | ብር | | የካናዳ ዶላር | | DM | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 107ኛ ኮር | 126,735 | 64 | --- | | - | - |
| 2 | አየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 4,167 | 60 | --- | | - | - |
| 3 | ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 6,329,022 | 67 | 400,000 | 00 | - | - |
| 4 | ፍትህ ሚኒስቴር | 126 | 50 | --- | | - | - |
| 5 | የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ም/ቤቶች ጽ/ቤት (የኦዲዮቪዝዋል ዕቃ ግዥ) | | | | | 10,175 | 00 |
| | ድምር | 6,460,052 | 41 | 400,000 | 00 | 10,175 | 00 |

የግዥ ሂሳቦች ከመመዝገባቸው በፊት የተገዙት ዕቃዎች ለንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸው ሊረጋገጥ እንደሚገባና የንብረት ገቢ ደረሰኝም ከወጪ ቫውቸር ጋር ተያይዞ መቀመጥ እንዳለበት ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2.7. አለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች ብር 694,264.15

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ክፍያዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሰባት መ/ቤቶች ውስጥ አለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 694,264.15 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ሁኔታውም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | 110ኛ ኮር | 32,771 | 20 |
| 2 | 107ኛ ኮር | 167,953 | 53 |
| 3 | የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት | 1,549 | 73 |
| 4 | ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 457,297 | 12 |
| 5 | አየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ | 14,137 | 00 |
| 6 | የጋፋት ኢንጅነሪንግ ፋብሪካ | 17,488 | 00 |
| 7 | የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት | 3,067 | 57 |
| | ድምር | 694,264 | 15 |

አለአግባብ የተፈፀሙት ክፍያዎች በርካታ ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ በብልጫ የተከፈለ የውሎ አበልና ደመወዝ፣ በባለሥልጣን ከተፈቀደው በላይ የተከፈለ፣ መ/ቤቱ ላልተጠቀመበት ቤት የተከፈለ የቤት ኪራይ፣ ከደመወዝ ላይ ሣይቀነስ የቀረ የሥራ ግብር፣ መ/ቤቱ የተጠቀመበት አገልግሎት መሆኑ

ሳይረጋገጥ የተከፈለ የስልክ ሂሣብ፣ የመ/ቤቱ ንብረት ላልሆነ የመብራት ቆጣሪ የተከፈለ የመብራት ሂሣብ፣ ለሣጥን መጠበቂያ ተብሎ የተፈፀመ ክፍያ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ደንብና መመሪያዎችን ሣይጠብቁ የተፈፀሙ ክፍያዎች ናቸው::

በመሆኑም ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ክፍያዎች፣ በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ እና መ/ቤቱ ላልተጠቀመበት አገልግሎት የተፈፀሙ ክፍያዎች ተመላሽ እንዲደረጉ ያልተቀነሰው የሥራ ግብር ተቀንሶ ፈሰስ እንዲሆን በመግለፅ ለወደፊቱ ክፍያዎች መመሪያና ደንብን ተከትለው እንዲፈፀሙ በላክነው ሪፖርት አሣስበናል::

3. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ የተጠቀሙበት መሆኑንና በበጀት ዓመቱ መጨረሻም ከወጪ ከቀሪያቸውን ለሚመለከተው ክፍል በወቅቱ ፈሰስ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት ቀጥሎ የተመከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል::

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ስም | ያልተሠራበት በጀት | | ከበጀት በላይ የወጣ | | ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ ሂሣብ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት | 4,528,898 | 32 | 341,231 | 66 | 18,898,191 | 26 |
| 2 | ፍትህ ሚኒስቴር | 2,303,246 | 48 | 361,954 | 37 | - | - |
| 3 | ጋፋት ኢንጂነሪንግ ፋብሪካ | 2,637,844 | 97 | - | - | - | - |
| 4 | የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት | 1,273,414 | 21 | - | - | 2,156,549 | 54 |
| 5 | የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት | 17,631,616 | 82 | 6,533 | 84 | - | - |
| 6 | የ107ኛ ኮር | - | - | - | - | 16,810 | 64 |
| | ድምር | 28,375,020 | 80 | 709,719 | 87 | 21,071,551 | 44 |

ከላይ እንደተመለከተው ያልተሠራበት በጀት ብር 28,375,020.80፣ ከበጀት በላይ የወጣ ብር 709,719.87 የተገኘ ሲሆን ብር 21,071,551.44 ደግሞ በወቅቱ ፈሰስ ያልተደረገ ሂሣብ ነው:: በመሆኑም የመ/ቤቶች የበጀት እቅድ አዘገጃጀት በበቂ ጥናት የተደገፈና ሊተገበር የሚችል መሆን እንዳለበትና በበጀት ዓዋጅ ከተፈቀደው በላይ ሥራ ላይ ማዋልም ሆነ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተመለከተውን ከወጪ ቀሪ በወቅቱ ፈሰስ አለማድረግ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብን ያልተከተለ አሰራር መሆኑን በመግለፅ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እዳይፈፀም ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል::

4. <u>ንብረት</u>

4.1 የ110ኛ ኮር፣

የቀለብ ገቢና ወጪ በአግባቡ ያልተመዘገበ መሆኑ፣

የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት ያልተመዘገበ በርካታ ስንቅና ቀለብ መገኘቱ፣

የነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት አመዘጋገብ ሥርዓትን ያልተከተለ መሆኑ ፣

የቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ የሌለና ለዕቃዎች የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፣

በርካታ ዕቃዎች ለብልሽት የተዳረጉ መሆኑ፣

የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰ→ች መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ፣

ለጭነት ማጓጓዣነት የሚያገለግሉ እንስሳት በምን ሁኔታላይ እንዳሉ የማይታወቅ መሆኑ፣

4.2 የ107ኛ ኮር ፣

የንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ፣

ለቋሚ ዕቃዎችና ንብረቶች የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፣

የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰ→ች መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ፣

በርካታ ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት የቆሙ መሆናቸውንና ሊብሬ(የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር) የሌላቸው መሆኑ፣

4.3. <u>የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ም/ቤቶች</u>

<u>ጽ/ቤት የኦዲዮቪዥዋል ዕቃዎች ግዥ</u>

ከአራተኛው የኦዲዮቪዥዋል ዕቃ ግዥ፣ ከመንግሥት መመሪያ ውጭ 60% የግዢ ቅድሚያ ክፍያ ብር 99,766.80 በሰነድ መሰጠቱ፣

የዕቃ ሻጭ ድርጅት ብር 166,278.00 የሚያወጣ ዕቃ ለማቅረብ በገባው ግዴታ መሠረት በወቅቱ ያላቀረበ ቢሆንም በውለታው መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

በአምስተኛው የኦዲዮቪዥዋል ዕቃ ግዢ ፕላዝማ እስክሪን ለመግዛት የወጣው ጨረታ ያለበቂ ምክንያት ተሰርዞ በአራተኛው የኦዲዮቪዥዋል ዕቃ ግዥ

ወቅት ካሽነፊ ተጫራች ግዥ መፈፀሙና ሌሎች ተጓዳኝ ዕቃዎች ደግሞ የግዥ ውል ሳይደረግ የተገዙ መሆኑ ፣

- ከመንግሥት መመሪያ ውጭ 65% የግዥ ቅድሚያ ክፍያ ብር 287,118.00 በሰነድ የተሰጠ መሆኑ፣

ከላይ በዝርዝር የተመለከቱት የአሠራር ግድፈቶች በኦዲት ወቅት የተረጋገጡ በመሆኑ ጽ/ቤቱ ለወደፊቱ በዕቃ ግዥ ሂደት ላይ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

5. <u>ልዩ ልዩ</u>

5.1. <u>በኦዲዮቪዥዋል ዕቃ ግዥ ወቅት የታየ የቁጥጥር ሥርዓት ድክመት</u>

የኦዲዮቪዥዋል ዕቃዎች ግዥ በእስፔስፊኬሽኑ መሠረት ለመሆናቸው በባለሙያ ለመረጋገጡ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

የኦዲዮቪዥዋል ግዥ በአንድ ጊዜ መፈፀም ሲገባው በተለያዩ ጊዜያት ተከፋፍሎ የተከናወነ መሆኑ፣

5.2. <u>በሌሎች ኦዲት በተደረጉ 8 መ/ቤቶች የታዩ የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች</u>

ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣

ስለመንግሥት ተሽከርካሪዎች አገልግሎት በወጣው መመሪያ መሠረት የተዘጋጁት ቅጾች ሥራ ላይ አለመዋላቸው እና

የዕቃዎችና የንብረት ቆጠራ በየዓመቱ የማይደረግ መሆኑ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ከላይ የተመለከቱትና ሌሎችም በርካታ የቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በመገኘታቸው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

5.3. <u>በጥቅም ላይ ያልዋለ ቃል የተገባ የእርዳታ ገቢ ብር 596,000</u>

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የእምባ ጠባቂና ሰብአዊ መብት ኮሚሽንን ለማቋቋም ከካናዳ መንግሥት ቃል ከተገባለት 2,096,000.00 ብር ውስጥ ብር 1,500,000 ብቻ በሥራ ላይ የዋለ ሲሆን ቀሪው ብር 596,000.00 ተጠይቆ

አለመምጣቱን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው በምክር ቤቱና በእርዳታ ሰጪው የካናዳ ኤምባሲ መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት የገንዘብ አጠቃቀም ሪፖርትና የኦዲት ሪፖርት ለእርዳታ ሰጪው አካል በወቅቱ ባለመላኩ እና ቀሪው ገንዘብም እንዲለቀቅ ባለመጠየቁ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተገልጿል፡፡ ስለዚህ ለወደፊቱ ከእርዳታ የሚገኝ ገቢን ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ለማዋል ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግና ቃል የተገባውም የዕርዳታ ሂሣብ ጥቅም ላይ እንዲውል ተገቢው ሪፖርት ተሟልቶ መቅረብ እንዳለበት  በላክነው ሪፖርት አሣስበናል፡፡

**1.2. <u>ከተለያዩ ግለሰቦች የሚፈለግ ዕዳ ብር 118884.65</u>**

የ110ኛ ኮር አባላት የሆኑ አስር ሰዎች ብር 118884.65 ይዘው መሠወራቸው ተገልጿል፡፡ ከዚህ ውስጥ ብር 39729.53 ባጠፉት ግለሰብ ላይ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ መወሰዱ የተገለፀ ሲሆን፣ በቀሪዎቹ ላይ  አስፈላጊው እርምጃ ተወስዶ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አስገንዘበናል፡፡

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ

## የ1993 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት

በፌዴራል መንግሥት በ1993 በጀት ዓመት ኦዲት ለማድረግ ፕሮግራም ከተያዘላቸው በጠቅለላ አገልግሎት ዘርፍ ከሚገኙ መ/ቤቶች ውስጥ፣

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር፣
- የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት፣
- የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን፣
- የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን፣
- የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣
- በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን፣ ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ ውጤቱ ለኦዲት ተደራጊዎች በየአድራሻቸው ተልኳል።

የ1993 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ተደርጎ በሪፖርቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት እና በሪፖርቱ መሠረት የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው ሁለት (2) መ/ቤቶች በወቅቱ፣ አንድ (1) መ/ቤት ዘግይቶ መልስ የሰጡ ሲሆን 3 መ/ቤቶች መልስ ሳይሰጡ ቀርተዋል። ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል።

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | በወቅቱ መልስ የሰጡ (✓) | ዘግይተው መልስ የሰጡ (✓) | መልስ ያልሰጡ (✓) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር | | ✓ | |
| 2 | የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት | | | ✓ |
| 3 | የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን | ✓ | | |
| 4 | የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን፣ | | | ✓ |
| 5 | የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | ✓ | | |
| 6 | በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ሂሳብ | | | ✓ |

በኦዲቱ ወቅት በአሠራርና በሂሣብ አያያዝ ረገድ የተገኙት ውጤቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 1. የጥሬ ገንዘብና የሠነድ ሂሣብ፣

### 1.1. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት

ኦዲት ከተደረጉት ስድስት መ/ቤቶች ውስጥ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 9528.27 የጥሬ ገንዘብ ብልጫ ብር 2427.53 እና በጉድለት የተመለከተ የቪዛ ገቢ ብር 2934.10 ተገኝቷል፡፡ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተ/ራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ጉድለት | | ብልጫ | |
| 1 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር | 32 | 03 | - | - |
| 2 | የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት | 1,274 | 99 | - | - |
| 3 | የማዕከላዊ ስታቲክስ ባለሥልጣን፣ በ3 ቅርንጫፍ ጽ/ ቤቶች | 7934 | 92 | 2316 | 36 |
| 4 | የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | 286 | 33 | - | - |
| 5 | የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን | - | - | 111 | 17 |
| 6 | በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማትክ ሚሲዮን ሂሣብ (የቪዛ ሂሳብ) | 2934 | 10 | - | - |
| | ድምር | 12,462 | 37 | 2,427 | 53 |

ጉድለቱና የሣጥን ብልጫ ሊደርስ የቻለው በጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ላይ ተገቢው ወቅታዊ ቁጥጥርና ክትትል ባለመደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም ለወደፊቱ ተመሣሣይ ስህተት እንዳይከሰት ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባና የጎደለው ገንዘብ እንዲተካ፣ እንዲሁም በብልጫ ለተገኘው ሂሣብ የገቢ ደረሰኝ እንዲቆረጥለት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 1.2 ማመዛዘን ያልተቻለ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ

የማዕላዊ ስታትስቲክስ የባለሥልጣኑ የዋና ገ/ያዥ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከወጪ ቀሪ ኦዲት ለማድረግ ተሞክሮ፣

- ከ1992 ለ1993 በጀት ዓመት መዞር ያለበት የመደበኛ በጀት ከወጪ ቀሪ ሂሣብ ብር 1,077,656.08 በመዝገብ ያልተመዘገበ በመሆኑ፣

በጥሬ ገንዘብ ሂሣብ መዝገብ እና በወርሃዊ የሂሣብ ማስታወቂያ መካከል ልዩነት በመኖሩ፣

የ1993 በጀት ዓመት የየወሩ የገቢና ወጪ ሂሣብ ድምር በእርሳስ የተጻፈ (ያልቀለመ) እና በኃላፊዎች ተረጋግጦ ያልተፈረመበት በመሆኑ፣

የሂሣብ መዝገብ ተዘግቶ የገቢና የወጪ ሂሣብ ከተናበበ በኋላ የተሠረዘና አዲስ የተጨመሩ ሂሣቦች በመኖራቸው እና አዲስ የመዝገብ ከወጪ ቀሪ ተመዝግቦ በመገኘቱ፣

በሰኔ 30/1992 የሥነ ሕዝብና የጤና ጥናት የዕርዳታ ሂሣብ መዝገብ በሣጥን ዓምድ የተመለከተው ወጪ በብር 79,437.65 ከገቢ በልጦ በመገኘቱ፣

ከበጀት ሂሣብ ላይ ወጪ ተደርጎ በሥነሕዝብና ጤና ጥናት የዕርዳታ ሂሣብ መዝገብ ላይ በወጪ የተመዘገበው ሂሣብ፣ በሥነሕዝብና ጤና ጥናት የዕርዳታ ሂሣብ መዝገብ በገቢ የማይያዝ በመሆኑ፣

የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ሳይመዛዘን ቀርቷል።

በ1990 በጀት ዓመት ሂሣብ አዲት ወቅትም ተመሣሣይ ድክመቶች በመታየታቸው ሊታረም እንደሚገባ ማሳሰቢያ ቢሰጥም አለመሻሻሉ ታውቋል። በመሆኑም መ/ቤቱ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ አያያዝ ድክመቶችን ለማስወገድ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

1.3. <u>በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ</u>
<u>ጥሬ ገንዘብ ብር 189,189.19</u>

በዘርፉ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በአራቱ በካዝና ውስጥ ብር 189,189.19 ተገኝቶ የቆጥሯል። ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል።

| ተ/ራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት | 14,015 | 12 |
| 2 | የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን | 10,889 | 40 |
| 3 | የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን | 156,111 | 87 |
| 4 | የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | 8,172 | 80 |
| | ድምር | 189,189 | 19 |

በጥሬ ገንዘብ ላይ ጉድለትና ጥፋት ከመፈፀሙ በፊት ገንዘብ ያዥዎች የሚሰበስቡት የዕለት ገቢ ከብር 5,000.00 በላይ ከሆነ በዕለቱ ወይንም በተከታዩ ቀን ባንክ ገቢ እንዲደረግ፣ የመ/ቤት ኃላፊዎችም ይህንኑ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ መመሪያው የሚያዝ ሆኖ ሳለ ተግባራዊ ካለመደረጉ የተከሰተ መሆኑን በመግለጽ አሠራሩን እንዲያስተካክሉ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

1.4. <u>ውዝፍ የሠነድ ሂሣብ ብር 20,163,501.25፣</u>

በዘርፉ ኦዲት በተደረጉት ስድስት መ/ቤቶች ውስጥ ብር 20,163,501.25 ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር | 46,138 | 12 |
| 2 | የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት | 27,027 | 02 |
| 3 | የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን | 2,964 | 50 |
| 4 | ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን | 19,987,847 | 63 |
| 5 | የፌዴራል ሲቪልሰርቪስ ኮሚሽን | 67346 | 37 |
| 6 | በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ሂሣብ | 32177 | 61 |
| | ድምር | 20,163,501 | 25 |

ከላይ ከተመለከተው ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ውስጥ ብር 11,182,951.53 በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ለውሎ አበል ተብሎ የተከፈለና በወቅቱ ያልተወራረደ ሲሆን በአጠቃላይ ሰነዱ ሊከማች የቻለው በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ መሠረት ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ባለመደረጉ እንደሆነ ታውቋል፡፡ በመሆኑም ለወደፊቱ በደንቡ መሠረት ተገቢው ቁጥጥር እንዲደረግና ውዝፉም ሂሳብ በአስቸኳይ እንዲወራረድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.5 <u>በቪዛ ገቢ ማጠቃለያ መዝገብ እና በባንክ ሂሣብ ማስታወቂያ መካከል የተገኘ የሂሳብ ልዩነት ብር 459,397.89</u>

በናይሮቢ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ከቪዛ የተሰበሰበው እና በባንክ ሂሣብ ማስታወቂያ የተመለከተው ሂሳብ በቪዛ ገቢ ማጠቃለያ መዝገብ በተመለከተው ልክ መሆኑ ሲጣራ፣ በባንክ ሂሣብ ማስታወቂያ የተመለከተው ብር 459397.89 አንሶ ተገኝቷል፡፡ ልዩነቱ የተከሰተው ከቪዛ ገቢ ላይ ክፍያ ተፈፅሞ በወጪ

ለመመዝገብ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ በሰነድ የተመዘገበ ሂሣብ በመኖሩ መሆኑን ኦዲት አስደራጊዎች የገለፁ ቢሆንም በወቅቱ የተዘጋጀ የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ ባለመቅረቡ፣ የሰነድ ሂሣብ ለመሆኑ ገንዘቡን የወሰደው ሰው ስም፣ የገንዘቡ ልክ፣ የወጪው ምክንያትና ቀኑን የሚገልፅ ማስረጃ ባለመቅረቡና እንዲሆን የሚታዘዘው በዋናው መ/ቤት በመሆኑ ከዋናው መ/ቤት የተፃፈ ደብዳቤ ባለመቅረቡ የተሰጠው ምክንያት አሳማኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የልዩነቱ መንስኤ በዋናው መ/ቤት በኩል ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. <u>የገቢ ሂሣብ፣</u>

የመንግሥት ገቢ በሕጉ መሠረት መሰብሰቡንና ለተሰበሰበው ገቢም የገቢ ደረሰኝ እየተቆረጠለት መመዝገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1. <u>የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሣብ</u>

<u>ብር 715,631.99፣</u>

ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን ብር 585490.46፣ በዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ሂሣብ ዋና ክፍል ብር 130141.53 በድምሩ ብር 715631.99 የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለትን ሂሣብ ለመጥቀስ ያህል ከሠራተኛ ደመወዝ የተቀነሰ የግል የስልክ ጥሪ፣ ሠራተኞች ላልሠሩበት ጊዜ የተቀነሰ ደመወዝ ተመላሽ፣ በብልጫ ተከፍሎ ተመላሽ የተደረገ፣ ለዕቃ ግዥ ገቢ የተደረገ እና ከቪዛ ሂሣብ ወደ በጀት የተዛወረ ሂሣብ የሚሉት ናቸው፡፡ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 32/1 እና 36/2 ላይ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም የመንግስት ገቢ በሕጋዊ ደረሰኝ ገቢ መደረግ እና መመዝገብ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.2. <u>ያልተሰበሰበ የገቢ</u>

**ግብር ብር1,100.00**

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ለግብርና ናሙና የፖስተር ዝግጅት ውድድር ላሸነፉ ግለሰቦች ከተሰጠው ሽልማት ላይ መሰብሰብ ያለበት ግብር ብር 1,100.00 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት

እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ፣ አሁንም ቢሆን ያልተሰበሰበው ሂሣብ ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ተመላሽ እንዲሆን በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

2.3 <u>ከታሪፍ በታች የተሰበሰበ የቪዛ ገቢ</u>

<u>ሂሣብ ብር 3,230.42፣</u>

የቪዛ ገቢ በወጣው ታሪፍ መሠረት የተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ሂሳብ ዋና ክፍል ከታሪፍ በታች የተሰበሰበ ብር 3,230.42 ተገኝቷል። ለወደፊቱ ማናቸውም ገቢ በታሪፉ መሠረት እንዲሰበሰብ ብርቱ ጥንቃቄና ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ እና ሳይሰበሰብ የቀረው ገንዘብም ገቢ ተደርጎ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

3. <u>የወጪ ሂሣብ፣</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በማስረጃ የተደገፉ መሆኑን ፣ ክፍያዎች በወጣው የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎች መሠረት መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል።

3.1. <u>የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ</u>

<u>ብር 1,690,355.05</u>

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ለታሪካዊ ቅርሶች ጥገናና እንክብካቤ ለክልሎች የተላከ ሂሣብ ብር 1,461,000.00፣ የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ለተለያዩ አገልግሎቶችና ግዢዎች ወጪ የሆነ ብር 229,355.05 በድምሩ ብር 1,690,355.05 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል። በመሆኑም ገንዘቡ ለታቀደለት አላማ ለመዋሉ ማስረጃው ቀረቦ በውስጥ ኦዲት በኩል እንዲጣራ ለወደፊቱ ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት የተሟላ ማስረጃ የቀረበ ለመሆኑ ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል።

3.2. <u>የወጪውን ትክክለኛነት</u>

<u>ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ብር 119,544.24</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ትክክለኛ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ :–

በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን - - - - ብር 118621.56

በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን - - - - - -    562.68

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ሂሳብ    360.00

በድምሩ    119544.24

የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን ብር 118544.24 የያዙ አራት የወጪ ቫውቸሮች ባለመቅረባቸው እና የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ደግሞ ለስልክ አገልግሎት የተከፈለ ሂሣብ ለመንግሥት ሥራ ወይም ለግል ጉዳይ የዋለ መሆኑን ለማጣራት አልተቻለም፡፡

በመሆኑም ያልቀረቡት ቫውቸሮች ተፈልገው ትክክለኛነታቸው በውስጥ ኦዲት ክፍል እንዲጣራ እና ለስልክ አገልግሎት የተከፈለው ደግሞ ሁኔታው ተጣርቶ ለግል ሥራ የዋለ ከሆነ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡

3.3 <u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት</u>

<u>ሂሣብ ብር 10113480.92</u>

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ሂሣብ ዋና ክፍል የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ ብር 10113480.92 ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በቀረበው ሂሣብ ላይ ያልተሟላውን ማስረጃ ለመጥቀስ ያህል የወጪ ቫውቸር ያልተዘጋጀለት፣ የውል ስምምነት ያልቀረበለት፣ የዕቃው ብዛትና ዓይነት በንብረት ገቢ ላይ ያልተገለፀ፣ የገንዘብ ያዥ ፊርማ የሌለውና ማስረጃው ፎቶ ኮፒ የሆነ የሚሉት ናቸው፡፡

በመሆኑም ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ማስረጃዎች መሟላታቸው መረጋገጥ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

3.4 <u>ያለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ</u>

<u>ብር 147516.69፣</u>

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን .......... ብር 8962.50

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ

ሚሲዮን ሂሣብ ዋና ክፍል ......................... ብር <u>138554.19</u>

በድምሩ    ብር <u>147516.69</u>

ያለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ ተገኝቷል፡፡

ያለአግባብ ከተፈፀሙት ክፍያዎች ውስጥ የተፈቀደበት መመሪያ ሳይኖር የተከፈለ የወተት አበል፣ የመጠለያ አበል፣ በብልጫ የተከፈለ፣በድጋሚ ተከፍሎ የተገኘ፣ በባለሥልጣን ሳይፈቀድ የተፈፀመ ክፍያ፣የመኪና ሾፌር ለፈፀመው ጥፋት ከመንግሥት ካዝና የተከፈለ፣ከደንብና መመሪያ ውጭ የተፈፀመ ክፍያ፣ በዲፕሎማቲክ ስም ለተያዘ ተሽከርካሪ ጥገና የተከፈለ፣ለትርፍ ሰዓት ሥራ የተከፈለ ሂሣብ ይገኝበታል ፡፡

በመሆኑም አሠራሩ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብን ያልተከተለ በመሆኑ እንዲታረምና ያለአግባብ በተፈፀመውም ክፍያ ላይ ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

**3.5 <u>ደንብና መመሪያን ሣይከተል የተፈፀመ የግዥ</u>**

**<u>ሂሣብ ብር 1941138.70፣</u>**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተፈፀሙት ግዥዎች ደንብና መመሪያን ተከትለው የተፈፀሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ............. ብር 1228391.76

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ

ሚሲዮን ሂሣብ ዋና ክፍል ......................... ብር <u>712746.94</u>

በድምሩ <u>1941138.70</u>

ደንብና መመሪያን ሣይከተል የተፈፀመ ግዥ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ በጋራዡች በኩል የተፈፀመ፣ ያለጨረታ ውድድር የተፈፀሙ፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ያልቀረበላቸው ግዥዎች የሚሉት ናቸው ፡፡ አሰራሩ መንግሥት ያወጣውን የዕቃ ግዥ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ በመሆኑ ድርጊቱን በፈፀሙት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላይ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ ለወደፊቱ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ግዥው ደንብና መመሪያዎችን ተከትሎ መፈፀሙ መረጋገጥ እንዳበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

**3.6 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት</u>**

**<u>ሂሣብ ብር 556165.44፣</u>**

በበጀት ዓመቱ የተገዙት ዕቃዎች በሙሉ ለንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ሂሣብ

በብር 556.165.44 የተገዙ ዕቃዎች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ አልቀረበም፡፡

በመሆኑም ሂሣቡ ከመወራረዱ በፊት ንብረቶቹ ገቢ መደረጋቸውን ማረጋገጥ እንደሚገባ በመግለጽ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደረጉና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለትም ዕቃ ገቢ መደረጉ ተረጋግጦ ደረሰኝ እንዲቆረጥለት በላክነው ሪፖርት አሣስበናል፡፡

4. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን፣ ከበጀት በላይ ወጪ አለማድረጋቸውንና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የሚገኘውን ሂሣብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካ ፈሰስ ያደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በአራቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

| ተ/ራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | ያልተሠራበት በጀት | | ከበጀት በላይ የወጣ | | ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ ሂሣብ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር | 751550 | 81 | – | – | 6279 | 84 |
| 2 | የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት | 131804 | 26 | 61863 | 29 | 100 | 05 |
| 3 | የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን | 522012 | 82 | – | | – | |
| 4 | የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | 540118 | 57 | – | | 94487 | 37 |
| | ድምር | 1945486 | 46 | 61863 | 29 | 100867 | 26 |

ከላይ እንደተመለከተው በአራት መ/ቤቶች ያልተሠራበት በጀት ብር 1945486.46፣ ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገ ብር 61863.29 እና በወቅቱ ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ ብር 100867.26 መኖሩ ታውቋል፡፡

የበጀት ዝግጅት በበቂ ጥናት የተደገፈና ሊተገበር የሚችል መሆን እንዳለበት፣ በበጀት ዓዋጅ ከተፈቀደው በላይ ሥራ ላይ ማዋልም ሆነ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተመለከተውን ከወጪ ቀሪ በወቅቱ ፈሰስ አለማድረግ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብን ያልተከተለ አሰራር መሆኑን በመግለጽ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

5. <u>ልዩ ልዩ</u>

5.1. <u>የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን</u>

በብሔራዊ ሙዝየም ንብረት ክፍል የሚገኙ ፖስት ካርዶች፣ የመግቢያ ቲኬቶች እና መጽሔቶች ገቢና ወጪ መከታተያ መዝገብ ባለመቋቋሙ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣

5.2. <u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን</u>

የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ምዝገባ ባለመከናወኑ የንብረት ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ እና በዕርዳታ የተገኘ ብር 626493.04 በመደበኛ በጀት ሂሣብ ላይ ተመዝግቦ መገኘቱ፣

5.3. <u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር</u>

ቲያትር ቤቱ ገቢ የሰበሰበባቸውን ጉርድ ቲኬቶች በበጀት ዓመቱ ለይቶ ባለመያዙ እና በቲኬት ላይ ቀን የማይጻፍ በመሆኑ ትያትር ቤቱ የሰበሰበውን ገቢ ኦዲት ማድረግ አለመቻሉ፣

5.4 <u>በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ሂሣብ፣</u>

የቪዛ ሂሣብ ባንክ ገቢ የተደረገበት ዲፖዚት ስሊፕ ከባንክ ስቴትመንት ጋር የማይላክ መሆኑ፣

የዕቃ ግዥ እና የዕቃ ግ/ቤት ሥራ በአንድ ሠራተኛ ተደርቦ የሚከናወን መሆኑ፣

የሂሣብ ሪፖርቶች ሥርዝ ድልዝ የሚበዛባቸው ሆኖ መገኘቱ፣

በየዕለቱ የሚሰበሰበው ገንዘብ በዕለቱ ባንክ ገቢ የማይደረግ መሆኑ፣

የኤምባሲዎችን ሂሣብ በተመለከተ የዴስክ ኃላፊዎች አጣርተው በሚያቀርቡት ሪፖርት መሠረት እርምጃ የማይወስድ መሆኑ፣

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከኤምባሴዎች የበጀት፣ ቪዛ እና ከዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ሂሳብ ዋና ክፍል በርካታ ከወጪ ቀሪ እንደነበረና ይህም ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የተደረገ መሆኑ የተገለፀ ቢሆንም ፈሰስ የተደረገበት ማስረጃ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ከላይ የተገለፁት የአሰራር ስህተቶች እንዲታረሙና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢው ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የድሬደዋ አስተዳደር ካውንስል

## የ1993 በጀት ዓመት የድጋፍና ድጎማ

## ሂሣብ ኦዲት

በ1993 በጀት ዓመት ከፌዴራል መንግሥት ለአስተዳደር ካውንስሉ የተመደበውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ልዩ ድጎማዎች በአዋጅ ቁጥር 68/1989 አንቀጽ 7/2 መሠረት ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ በሶስት መ/ቤቶች ሂሣብ ላይ ኦዲቱን አከናውኗል፡፡ መ/ቤቶቹም :-

- የጤና ጽ/ቤት
- የግብርና ጽ/ቤት
- የፋይናንስ ጽ/ቤት

ሲሆኑ፤ ኦዲት የተደረገው ሂሣብ ውጤትና አስተያየት በየአድራሻቸው የተላከ ቢሆንም በሪፖርቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት እና በኦዲት ውጤቱ ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው የድሬደዋ አስተዳደር ካውንስል ፋይናንስ ጽ/ቤት ከሶስት ወር በኋላ መልስ የሰጠ ሲሆን ሁለቱ መ/ቤቶች መልስ ሣይሰጡ ቀርተዋል፡፡ በአጠቃላይ በአሠራርና በፋይናንስ ረገድ በኦዲቱ ከታወቁት ሁኔታዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 1. የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ

#### 1.1 የሣጥን ጉድለት

የየመ/ቤቶቹ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ በመዝገብ የተመለከተውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ ሲመዛዘን ብር 7,422.31 ጉድለት ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

| ተራ/ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የጤና ጽ/ቤት | 861 | 40 |
| 2 | የግብርና ጽ/ቤት | 2283 | 61 |
| 3 | የፋይናንስ ጽ/ቤት | 4277 | 30 |
| | ድምር | 7422 | 31 |

የተገኘው ጉድለት ያልተተካ ሲሆን ገንዘቡን ለማስተካት መ/ቤቶቹ እርምጃ እንዲወስዱ በማሣሰብ ለወደፊቱ በሣጥን ሂሣብ ላይ በየጊዜው ቁጥጥር እንዲያደርጉ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 <u>የሣጥን ብልጫ</u>

በፋይናንስ ጽ/ቤት ብር 512.10 የሣጥን ብልጫ ተገኝቷል፡፡ በብልጫ የታየው ሂሣብ የገቢ ደረሰኝ እንዲቆረጥለትና ለወደፊቱ ሂሣብ ክፍሉ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲያደርግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.3 <u>በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ ብር 99,020.24</u>

በአስተዳደር ካውንስሉ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች በድምሩ ብር 99,020.24 በካዝና ተገኝቶ ተቆጥሯል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | ግብርና ጽ/ቤት | 5,843 | 00 |
| 2 | ጤና ጽ/ቤት | 47,459. | 04 |
| 3 | ፋይናንስ ጽ/ቤት | 45,718. | 20 |
| | ድምር | 99,020 | 24 |

የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ ለብክነት እንዳይጋለጥ ከብር 5000.00 በላይ በካዝና ማደር እንደሌለበት መመሪያ የሚያዝ በመሆኑ መ/ቤቶች ጥንቃቄና ቁጥጥር እንዲያደርጉ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.4 <u>ያልተወራረደ የሠነድ ሂሣብ ብር 1,274,027.62</u>

በበጀት ዓመቱ ኦዲት በተደረጉት ሶስት መ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,274,027.62 ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | ጤና ጽ/ቤት | 343,842 | 13 |
| 2 | ግብርና ጽ/ቤት | 236,895 | 78 |
| 3 | ፋይናንስ ጽ/ቤት | 693,289 | 71 |
| | ድምር | 1,274,027 | 62 |

ለሥራ ማስኬጃ በሰነድ የወጣ ሂሣብ በተለይ ግዢን የሚመለከተው በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ፣ የደመወዝ የሰነድ ሂሣብ ደግሞ የወሩ ደመወዝ

በሚከፈልበት ጊዜ መወራረድ እንዳለበት በፋይናንስ አስተደደር ደንብ ቁጥር 17/1989 የተደነገገ ቢሆንም በሶስቱ መ/ቤቶች ከላይ የተመለከተው ያልተወራረደ ሂሣብ ሊገኝ ችሏል፡፡ ስለሆነም ውዝፉን የሰነድ ሂሣብ በአስቸኳይ እንዲያወራርዱ፣ ለወደፊቱም በሰነድ ሂሣብ ላይ አስፈላጊው ቁጥጥር እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

የተመዘገቡት ሂሳቦች በማስረጃ የተደገፉ መሆኑን፣ የፋይናንስ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች ተጠብቀው ክፍያዎች መፈፀማቸውን፣ እንዲሁም ስህተቶችና ግድፈቶች አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1 <u>ደንብና መመሪያ ሳይከተል</u>
<u>የተፈፀመ ግዥ ብር 148,717.66</u>

መ/ቤቶች የፈፀሟቸው ግዢዎች ደንብንና መመሪያን የተከተሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣

| ተ/ቁ | | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | ጤና ጽ/ቤት | 39,481 | 65 |
| 2 | ግብርና ጽ/ቤት | 109,236 | 01 |
| | በድምሩ | 148,717 | 66 |

በግዥ ሥራ ላይ ባልተመደበ ሠራተኛ የተፈፀመ ግዥና በመመሪያው መሠረት የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይቀርብ የተፈፀመ ግዥ መሆኑ ታውቋል፡፡ አሠራሩ መንግሥት ያወጣውን የፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ ያልተከተለ በመሆኑ ለወደፊቱ መታረም እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡

2.2 <u>ያለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 106,050.41</u>

ኦዲት በተደረገባት ሁለት መ/ቤቶች የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የጤና ጽ/ቤት.. | 84,718 | 49 |
| 2 | የግብርና ጽ/ቤት.. | 21,331 | 92 |
| | በድምሩ ብር | 106,050 | 41 |

አለአግባብ ከተፈፀመው ክፍያ ውስጥ በብልጫ የተከፈለ የውሎ አበል፣ ማይቀነስ የቀረ ለህንፃ ግንባታ በቀረበ ዋጋ ላይ የተሠጠ ቅናሽ፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣ በድጋሚ የተከፈለ የውሎ አበል፣ ለግጭቱ መንስዔው ማይጣራ ለመኪና ጥገና የተከፈለ ወጪ ይገኝበታል፡፡ አሠራሩ ከደንብና መመሪያ ውጪ በመሆኑ አለአግባብ የተፈፀመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግና ለወደፊቱም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ደንብና መመሪያዎች መገናዘብ እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2.3 <u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት</u>
<u>ሂሣብ ብር 149,702.08</u>

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ ብር 149,702.08 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የጤና ጽ/ቤት | 116,251 | 28 |
| 2 | የግብርና ጽ/ቤት | 33,450 | 80 |
| | በድምሩ | 149,702 | 08 |

ያልተሟሉት ማስረጃዎችን ዓይነት ለመጥቀስ ያህል ደረሰኝ ያልቀረበለት፣ የውል ስምምነት የሌለው የነዳጅ ክፍያ፣ በባለጥቅሙ ያልተፈረመ የውሎ አበል፣ በሥራና ከተማ ልማት ጽ/ቤት ያልተረጋገጠ የግንባታ ሥራ ክፍያ፣ የጥገና ማዘዣ ያልቀረበለት የሚሉ ይገኝባቸዋል ፡፡ ስለሆነም መ/ቤቶቹ ወጪ ከመመዝገባቸው በፊት የማስረጃ መሟላቱን ማረጋገጥ እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

2.4 <u>የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ብር 39,021.65</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሣቦች ደጋፊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጤና ጽ/ቤት የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ የተመዘገበ ሂሣብ ብር 39,021.65 ተገኝቷል፡፡ ለወደፊቱ ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ እንዳለበትና ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ እንዲቀርብለት ካልሆነም ገንዘቡ ተመላሽ እንዲሆን በላክነው ሪፖርት አሣስበናል፡፡

2.5 <u>የሂሣብ መደቡን ያልጠበቀ ወጪ ብር 46,765.73</u>

የሂሣብ መደቡ ተጠብቆ ምዝገባ መከናወኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | ጤና ጽ/ቤት | ብር 8,850 | 29 |
| 2 | ግብርና ጽ/ቤት | ብር 37,915 | 44 |
| | በድምሩ | ብር 46,765 | 73 |

የሂሣብ መደቡን ሣይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ አሠራሩ የሚዘጋጀውን የሂሣብ መግለጫዎች የተዛባ መልዕክት እንዲያስተላልፉ የሚያደርግና ለበጀት ክትትልና ቁጥጥር አመቺ አለመሆኑን በመግለፅ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እዳለበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

2.6 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ብር 142,547.50</u>

መ/ቤቶች ለሚገዙዋቸው ዕቃዎች ሁሉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እየቆረጡ በትክክል የሚመዘግቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጤና ጽ/ቤት ብር 142,547.50 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብላቸው ሂሣቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ የተሰጠው ምክንያት በመጋዘን እጥረት ምክንያት ማስቀመጫ ባለመኖሩ ግዥ ከተፈፀመባቸው ድርጅቶች መጋዘኖች ለማንሳት ባለመቻሉ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ለወደፊቱ የዕቃዎች ግዥ ከተፈፀመ

በኋላ እና ሂሣቡ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ንብረቱ ገቢ መደረጉን ማረጋገጥ የሚገባ መሆኑን በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

2.7 <u>በድጋሚ በወጪ የተመዘገበ</u>

<u>ሂሣብ ብር 102,352.00</u>

ሂሣቦች በትክክል የሚመዘገቡ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በጤና ጽ/ቤት ብር 102,352.00 በድጋሚ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በድጋሚ የተመዘገበው ሂሣብ ከወጪ ቀሪ ሂሣብን የሚያዛባ በመሆኑ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሠራለትና ለወደፊቱም በምዝገባ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.8 <u>ልዩ ልዩ</u>

2.8.1 <u>ያልተወገዱ የተለወጡ ዋጋ ያላቸው ፎርሞችና</u>

<u>ቴምብሮች ሂሣብ ብር 3,689.25</u>

በድሬደዋ አስተዳደር ካውንስል ፋይናንስ ጽ/ቤት ሊወገዱ የሚገባ ብር 3,689.25 ዋጋ ያላቸው ቴምብሮችና ፎርሞች ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም ጽ/ቤቱ እነዚህ ቴምብሮችና ፎርሞች በመመሪያው መሠረት እንዲወገዱ በላክነው ሪፖርት አሣስበናል፡፡

2.8.2 <u>በድጋሚ የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት ብር 24,979.00</u>

በጤና ጽ/ቤት ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለልዩ ልዩ ስልጠናዎች ማስፈፀሚያ ለጽ/ቤቱ የተላከ ብር 24,979.00 በድጋሚ የገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት ተገኝቷል፡፡ የጽ/ቤቱን ከወጪ ቀሪ የሚያዛባ በመሆኑ ማስተካከያ እንዲሠራለትና ለወደፊቱም ተመሣሣይ ሁኔታ እንዳይከሠት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

2.8.3 <u>ወጪ ሣይደረግ በወርሃዊ የሂሣብ ማስታወቂያ</u>

<u>ላይ ሪፖርት የተደረገ ሂሣብ ብር 960.37</u>

በወርሃዊ ሂሣብ ማስታወቂያ ላይ የተመለከተው ሂሣብ በትክክል ከመዝገብ ላይ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጤና ጽ/ቤት ብር 960.37 በመዝገብ ላይ በወጪ ያልተመለከተ ሂሣብ በወርሃዊ ሂሣብ ማስታወቂያ ላይ ሪፖርት ተደርጎ ተገኝቷል፡፡ ስህተቱ የበጀት ዓመቱን ከወጪ ቀሪ የሚያዛባና የሂሣብ መግለጫዎች ትክክለኛ መረጃ እንዳያስተላልፉ የሚያደርግ በመሆኑ

ለወደፊቱ ተመሣሣይ ስህተት እንዳይደገም ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውንና ከበጀት በላይ ወጪ አለማድረጋቸውን፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የተገኘውን ሂሣብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

| ተራ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | ያልተሠራበት በጀት | | ከበጀት በላይ የወጣ | | ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ ሂሣብ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጤና ጽ/ቤት | 2,959,867 | 77 | 193,170 | 29 | 323,902 | 71 |
| 2 | የግብርና ጽ/ቤት | 502,977 | 94 | - | - | - | - |
| | በድምሩ | 3,462,845 | 71 | 193,170 | 29 | 323,902 | 71 |

ከላይ እንደተመለከተው ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ያልተሰራበት በጀት ብር 3,462,845.71፣ ከበጀት በላይ የወጣ ብር 193,170.29 እና ብር 323,902.71 ደግሞ በወቅቱ ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ ሂሣብ የተገኘ ሲሆን የመ/ቤቶች የበጀት አጠቃቀም፣የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንቡን ያልተከተለ መሆኑን በመግለጽ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

## <u>በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ</u>
## <u>የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የ1993 በጀት</u>
## <u>ዓመት የድጋፍና ድጎማ ሂሣብ ኦዲት</u>

በ1993 በጀት ዓመት ከፌዴራል መንግሥት ለክልሉ መንግሥት የተመደበውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ልዩ ድጎማዎችን በአዋጅ ቁጥር 68/1989 አንቀጽ 7/2 መሠረት ኦዲት ለማድረግ አቅዶ በሶስት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲቱን አከናውኗል ::

መ/ቤቶቹም:-

ጤና ቢሮ ፣

ትምህርት ቢሮ፣

የእንሰሳትና እርሻ ልማት ቢሮ ሲሆኑ፣ ኦዲት ተደርገው ሪፖርቱ ለኦዲት ተደራጊዎች በየአድራሻቸው የተላከ ቢሆንም በሪፖርቱ ላይ ያላቸውን አስተያየትና በኦዲት ውጤቱ ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው ሁሉም መ/ቤቶች መልስ ሳይሰጡ ቀርተዋል፡፡ በአጠቃላይ በአሠራርና በፋይናንስ ረገድ ከታወቁት ድክመቶች ውሰጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

<u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ</u>

1.1 <u>የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 940.38</u>

በክልሉ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በትምህርት ቢሮ ብር 940.38 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተገኘ ሲሆን፣ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ጉድለት እንዳይደርስ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱን እንዲያጠናክርና የጎደለውም ገንዘብ እንዲተካ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 <u>ውዝፍ የሰነድ ሂሳብ ብር 7,347929.83</u>

ኦዲት በተደረጉት ሶስት መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ የሰነድ ሂሳብ ብር 7,347,929.83 ተገኝቷል፡፡ ውዝፍ የሰነድ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ጤና ቢሮ - - - - - - - ብር 4, 355,810.47

ትምህርት ቢሮ - - - - - - - ብር 769,183.28

የእንሰሳትና እርሻ ልማት ቢሮ ብር 2,222,936.08

ድምር 7,347,929.83

ለሥራ ማስኬጃ በሠነድ የወጣ ሂሳብ በተለይ ግዢን የተመለከተው በሰባት የሥራ ቀናት፣ የደመወዝ ሠነድ ደግሞ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ መወራረድ እንዳለበት በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ የተደነገገ ስለሆነ በዚህ መሠረት ሳይወራረድ የተገኘው ውዝፍ የሰነድ ሂሳብ በአስቸኳይ እንዲወራረድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

<u>የገቢ ሂሳብ</u>

2.1 <u>የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለትና ያልተመዘገበ ብር 2,806,430.73</u>

በበጀት ዓመቱ ለተሰበሰበው ገቢ በሙሉ የገቢ ደረሰኝ እየተቆረጠለት መመዝገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በክልሉ ጤና ቢሮ የተሰበሰበ ብር 2,806,430.73 የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለትና ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 32፣35 እና 36 ላይ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም የመንግሥት ገቢ በሕጋዊ ደረሰኝ ገቢ መደረግ እና መመዝገብ ያለበት መሆኑን ጠቅሰን ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግና ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሳብ በደንቡ መሠረት ተቆርጦለት እንዲመዘገብ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

<u>የወጪ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በማስረጃ የተደገፉ መሆኑንና ክፍያዎች ሁሉ አግባብ ባለው ባለስልጣን እየተፈቀዱ መከፈላቸውንና መመዝገባቸውን፣ደንብና መመሪያዎች መከበራቸውንና ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

3.1 <u>የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ብር 12,212,067.96</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በሕጋዊ ማስረጃ የተደገፉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ኦዲት በተደረጉት በሶስቱም መ/ቤቶች ብር 12,212,067.96 ሕጋዊ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

መ/ቤቶቹም:-

| | | |
|---|---|---|
| ጤና ቢሮ | - - - - - - - ብር | 5,432,244.73 |
| ትምህርት ቢሮ | - - - - - - - ብር | 6,769,833.23 |
| እንሰሳትና እርሻ ልማት ቢሮ | ብር | 9,990.00 |
| ድምር | | 12,212,067.96 |

ለወደፊቱ የወጪ ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ህጋዊ የወጪ ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ እንዳለበትና ማስረጃ ያልቀረበለትም ሂሳብ እንዲቀርብለት፣ ካልሆነም ገንዘቡ ለሣጥን ተመላሽ እንዲደረግ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2 <u>ያለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 75,657.43</u>

ክፍያዎች መንግሥት ባወጣቸው ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መከናወናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ያለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ ሂሳብ ብር 75,657.43 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ጤና ቢሮ | - - - - - - - ብር | 35,589.08 |
| ትምህርት ቢሮ | - - - - - - -ብር | 33,794.73 |
| እንሰሳትና እርሻ ልማት ቢሮ | ብር | 6,273.62 |
| ድምር | | 75,657.43 |

ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ ከተፈፀመው ሂሳብ ውስጥ ለግል ሥራ ለተደወለ የስልክ ሂሣብ ከመንግሥት ካዝና የተከፈለ፣ ያለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል፣ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ የደንብ ልብስ ሂሳብ፣ በኮንትራት ለተቀጠረ የጥበቃ ሰራተኛ የተከፈለ ሂሳብ እና በብልጫ የተከፈለ ይገኙበታል፡፡ ስለሆነም ያለአግባብ በተከፈለው ሂሳብ ላይ ተገቢው እርምጃ

ተወስዶ ገንዘቡ እንዲተካና የደንብ ልብስን በተመለከተ መመሪያው በሚያዘው መሠረት በጥሬ ገንዘብ ሳይሆን ጨርቁ እንዲሰጥ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል

3.3 <u>የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ</u>

**<u>ብር 292,403.32</u>**

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በሙሉ የበጀት ዓመቱ ወጪዎች መሆናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ :-

| | | |
|---|---|---|
| ጤና ቢሮ | - - - - - - - ብር | 29,363.24 |
| እንስሳትና እርሻ ልማት ቢሮ | ብር | <u>263,040.08</u> |
| በድምሩ | ብር | <u>292,403.32</u> |

የ1992 በጀት ዓመት ወጪ ሆኖ ሳለ በ1993 በጀት ዓመት ተመዝግቦ ተገኝቷል።

ማንኛውም ክፍያ ወጪ በተደረገበት የበጀት ዓመት እንዲመዘገብና ለበጀት ዓመቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት እንዲሰራ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል።

3.4 <u>ከካፒታል በጀት ለመደበኛ በጀት ወጪ የሆነ ብር 29,363.24</u>

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንቡ በሚፈቅደው መሠረት መጠቀማቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የክልሉ ጤና ቢሮ ከተፈቀደለት የካፒታል በጀት ላይ ብር 29,363.24 በመደበኛ በጀት ሊሸፈን የሚገባው የመብራትና የስልክ አገልግሎት ክፍያ ወጪ ሆኖ መከፈሉ ታውቋል።

ለካፒታል ፕሮጀክት የተፈቀደን በጀት ለመደበኛ በጀት መጠቀም እንደማይቻል በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/89 አንቀጽ 17 ላይ የተደነገገ በመሆኑ አሰራሩ መታረም እንዳለበትና ለወደፊቱም ቢሮው የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ በመከተል እንዲሰራ አሳስበናል።

3.5 <u>የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ የተገኘ</u>

**<u>ብር 23,271.78</u>**

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በትክክለኛ የወጪ ሂሳብ መደብ ተለይተው መመዝገባቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ :-

በጤና ቢሮ - - - - - - - ብር 1,664.13

በትምህርት ቢሮ - - - - - - -ብር 21,607.65

በድምሩ 23,271.78

የሂሣብ መደብ ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ አሠራሩ የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች የተዛባ መልዕክት እንዲያስተላልፉ የሚያደርግና ለበጀት ቁጥጥርም አስቸጋሪ መሆኑን በመግለፅ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.6 <u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት</u>

<u>ብር 13,706,920.47</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች የተሟላ የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ :-

በትምህርት ቢሮ - - - - - - - - - - ብር 9,695,799.69

በእንሰሳትና እርሻ ልማት ቢሮ - - - - - - -ብር 4,011,120.78

በድምሩ ብር 13,706,920.47

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ከተመዘገበው ሂሳብ ውስጥ ገንዘቡ ለተላከለት አካል ለመድረሱ ማስረጃ ያልቀረበለት፣ የግዥ ቃለ ጉባኤ ያልቀረበለት፣ የወጪ ሂሳብ መደብና የቫውቸር ቁጥሩ ሳይሟላ የተመዘገበ፣ የተቀባይ ፊርማ የሌለው እና የጨረታ ሰነድ ውል ያልቀረበለት የሚሉ ይገኙበታል፡፡ ስለሆነም ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ተገቢው ማጣራት እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

3.7 <u>መመሪያ ሳይከተል የተፈፀመ ግዥ</u>

<u>ብር 626,732.63</u>

በበጀት ዓመቱ የተፈፀመው ግዢ ስለ ዕቃና አገልግሎት ግዢ አፈፃፀም የወጣውን መመሪያ የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ ብር 230,292.00፣ የግዢ መጠየቂያና የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይቀርብ ብር 396,440.63 በድምሩ ብር 626,732.63 መመሪያን ያልተከተለ ግዢ ተፈፅሞ ተገኝቷል::

ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል::

| የመ/ቤቱ ሥም | የግዢ መጠየቂያና ፕሮፎርማ ያልቀረበለት | የጨረታ ማስታወቂያ ያልወጣለት |
|---|---|---|
| ጤና በሮ | 38,928.91 | - |
| ትምህርት ቢሮ | 131,446.65 | 230,292.00 |
| የእንስሳትና እርሻ ልማት ቢሮ | 226,065.07 | - |
| ድምር | 396,440.63 | 230,292.00 |

በመሆኑም ከብር 3000.00 እስከ 30,000.00 የዋጋ ማወዳደሪያ በማቅረብ፣ ከብር 30,000.00 በላይ ደግሞ የጨረታ ማስታወቂያ እየወጣ ግዥ መፈጸም እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል ::

## 3.8 <u>የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ብር 258,016.24</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በሙሉ መ/ቤቶች ለተጠቀሙበት አገልግሎት መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሁለት ቢሮዎች በወጪ የተመዘገበውን ሂሣብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የልተቻለ ብር 258,016.24 ተገኝቷል:

ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል::

- ትምህርት ቢሮ ...................... ብር 2,880.00
- የእንስሳትና እርሻ ልማት ........... ብር <u>255,136.24</u>

ድምር ብር <u>258,016.24</u>

የወጪውን ትክክለኛነት ለማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ፣ ለመስክ ስራ ከተላኩበት መ/ቤት የውሎ አበል ላለመከፈሉ ሳይረጋገጥ የተከፈለ፣ በፋክቱር ላይና በቫውቸር ላይ የተለያዩ ስም የቀረበለትና የሰዓት ፊርማ ባለመቅረቡ ማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ ተገኝቷል:: ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተቶች እንዳይደገሙ ተገቢው ቁጥጥር እንዲደረግና ከላይ

የተመለከተውም ሂሳብ በውስጥ ኦዲት በኩል ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## የበጀት አጠቃቀም

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውንና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የሚገኘውን ሂሣብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | ያልተሠራበት በጀት | | ከበጀት በላይ የወጣ | | ፈሰስ ያልደተረገ ከወጪ ቀሪ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የክልሉ ጤና ቢሮ | 3,980,954 | 69 | 903,425 | 41 | 5,162,987 | 45 |
| 2 | የክልሉ ትምህርት ቢሮ | 22,784,803 | 80 | 2,897,707 | 50 | 803,438 | 61 |
| 3 | የእንሰሳትና እርሻ ልማት ቢሮ | 2,153,332 | 35 | 413,244 | 05 | 6,143,541 | 26 |
| | ጠቅላላ ድምር | 28,919.090 | 84 | 4,214,376 | 96 | 12,109,967 | 32 |

ከላይ እንደተመለከተው በሶስቱም መ/ቤቶች ያልተሠራበት በጀት ብር 28,919,090.84 ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገ ብር 4,214,376.96 በወቅቱ ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ብር 12,109,967.32 ተገኝቷል፡፡ የበጀት ዝግጅት በበቂ ጥናት የተደገፈና ሊተገበር የሚችል መሆን እንዳለበት እና በበጀት ዓዋጅ ከተፈቀደው በላይ ሥራ ላይ ማዋልም ሆነ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተመለከተውን ከወጪ ቀሪ በወቅቱ ፈሰስ አለማድረግ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብን ያልተከተለ አሠራር መሆኑን በመግለፅ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሥህተት እንዳይፈፀም ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

## ልዩ ልዩ

በእንሰሳትና እርሻ ልማት ቢሮ በብልጫ የተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ብር 15368.00 እና በማነስ የተመዘገበ የወጪ ሂሣብ ብር 2000.20 ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም ከላይ የተመለከቱት የምዝገባ ስህተቶች እንዲታረሙና ለወደፊቱ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## ንብረት

- በሶስቱም ቢሮዎች የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ ባለመቋቋሙ እና
- የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ ደንብና መመሪያ በሚያዘው መሠረት ባለመሆኑ፣

የአላቂና ቋሚ ንብረት ሂሣብ ኦዲት ማድረግ አልተቻለም። ስለሆነም አስፈላጊው መዝገብ ተቋቁሞ ሥራ ላይ እንዲውል በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል።

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
## የ1993 በጀት ዓመት የድጋፍና ድጎማ
## ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

በ1993 በጀት ዓመት ከፌዴራል መንግሥት ለክልሉ መንግሥት የተመደበውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማ በአዋጅ ቁጥር 68/1989 አንቀጽ 7/2 መሠረት ኦዲት ለማድረግ አቅዶ በስምንት መ/ቤቶች የሂሣብ ኦዲቱን አከናውኗል መ/ቤቶቹም :-

- የግብርና ቢሮ፣
- የጤና ቢሮ፣
- የሰሜን ሸዋ ግብርና መምሪያ፣
- የደቡብ ወሎ ግብርና መምሪያ፣
- የደቡብ ወሎ ጤና መምሪያ፣
- የሰሜን ጎንደር ጤና መምሪያ፣
- የሰሜን ጎንደር ገንዘብ መምሪያ፣

የምሥራቅ ጎጃም ገንዘብ መምሪያ፣ ሲሆኑ የኦዲት ሪፖርቱ ለኦዲት ተደራጊዎች በየአድራሻቸው ተልኳል፡፡

መ/ቤቶች በሪፖርቱ ላይ ያላቸው አስተያየት እና በኦዲት ውጤቱ ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው ሁሉም መልስ ሣይሰጡ ቀርተዋል፡፡

በኦዲቱ ወቅት የታዩት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች፣ የአሠራር ጉድለቶችና ግድፈቶች፣ እንዲሁም የሂሣብ አያያዝ ስህተቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ፣</u>

**1.1 ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ብር 27569131.99**

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/89 መሠረት ለሥራ ማስኬጃ በተለይ ግዥን በተመለከተ በሰነድ የወጣ ሂሣብ በሰባት የሥራ ቀናት፣ የደመወዝ ሰነድ ሂሣብ ደግሞ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ መወራረድ እንዳለበት የታዘዘ ሲሆን፣ ኦዲት በተደረጉት ስምንት መ/ቤቶች ያልተወራረደ ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ብር 27569131.99 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የሰሜን ጎንደር ጤና መምሪያ | 138179 | 55 |
| 2 | የሰሜን ጎንደር ገንዘብ መምሪያ | 25840 | 04 |
| 3 | የምሥራቅ ጎጃም ገንዘብ መምሪያ | 18632 | 40 |
| 4 | የግብርና ቢሮ | 13680520 | 16 |
| 5 | የጤና ቢሮ | 13586996 | 02 |
| 6 | የሰሜን ሸዋ ግብርና መምሪያ | 14171 | 00 |
| 7 | የደቡብ ወሎ ግብርና መምሪያ | 99792 | 70 |
| 8 | የደቡብ ወሎ ጤና መምሪያ | 5000 | 12 |
| | ድምር | 27569131 | 99 |

በመሆኑም ለወደፊቱ የፋይናንስ አስተዳደር ደንቡ በሚያዘው መሠረት የሰነድ ሂሣብ በወቅቱ መወራረድ ያለበት መሆኑንና ያልተወራረደውም ሂሣብ በአፋጣኝ እንዲወራረድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 1.2. ሞ/86 ያልተዘጋጀለትና በሰነድነት የተገኘ የአደራ ሂሣብ ብር 5382.90

የሰሜን ጎንደር ገንዘብ መምሪያ ብር 5382.90 ገንዘቡን ያስያዙት ግለሰቦች /ድርጅቶች/ ሞ/85 አቅርበው በሞ/86 ወጪ ከማድረጋቸው በፊት ገንዘቡ ወጪ ተደርጎ የሂሣብ ሠነዶቹ በካዝና ውስጥ ተገኝቷል፡፡

ሞ/85 ከመቅረቡ በፊት ገንዘቡ ወጪ መደረግ እንዳልነበረበት ገልፀን ሞ/85 ቀርቦ ሂሣቡ እንዲወራረድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 1.3. በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ ጥሬ ገንዘብ ብር 15235.68

በመመሪያ ከተፈቀደው ብር 5000.00 በላይ በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ ብር 15235.68 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| | |
|---|---|
| የሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብ መምሪያ | ብር 10087.33 |
| የምሥራቅ ጎጃም ገንዘብ መምሪያ | 5148.35 |
| ድምር | 15235.68 |

በመመሪያ ከተፈቀደው መጠን በላይ የሆነ ጥሬ ገንዘብ በካዝና ማስቀመጥ አግባብ አለመሆኑንና ለወደፊቱም በጥሬ ገንዘብ አጠባበቅ ላይ ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

የመንግሥት ገቢ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

### 2.1. <u>የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሣብ ብር 3949.40</u>

በበጀት ዓመቱ ለተሰበሰበው ገቢ በሙሉ የገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብ መምሪያ የተሰበሰበ ብር 3949.40 የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት ተገኝቷል፡፡ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/89 አንቀጽ 32፣35 እና 36 ላይ በተደነገገው መሠረት የመንግሥት ገቢ በህጋዊ ደረሰኝ ገቢ መደረግ ያለበት መሆኑን ጠቅሰን ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግና ደረሰኝ ያልተቆረጠለትም በደንቡ መሠረት እንዲቆረጥለት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 2.2. <u>ከሥራ ተቋራጮች ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሣ ብር 35328.85</u>

የሥራ ተቋራጮች በገቡት የውል ስምምነት መሠረት መፈፀሙን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፣

| | | |
|---|---|---|
| የጤና ቢሮ - - - - - - - - - - - - - | ብር | 25959.00 |
| የሰሜን ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ - - - - - | ብር | 9369.85 |
| በድምሩ | | 35328.85 |

በመሆኑም ከሥራ ተቋራጮች ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሣ መኖሩ ታውቋል፡፡ ስለሆነም ሂሣቡ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ተሰብስቦ ለመንግሥት ገቢ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በሕጋዊ ማስረጃ የተደገፉ መሆኑ፣ ደንብና መመሪያዎች ተጠብቀው ክፍያዎች መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

## 3.1. <u>የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት</u>

ሂሣብ ብር 2180957.47

ኦዲት በተደረጉ 7 መ/ቤቶች የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ብር 2180957.47 ተገኝቷል። ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል።

| ተራ ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የሰሜን ጎንደር ዞን ጤና መምሪያ | 666847 | 00 |
| 2 | የምሥራቅ ጎጃም ገንዘብ መምሪያ | 589595 | 56 |
| 3 | ግብርና ቢሮ | 472400 | 06 |
| 4 | ጤና ቢሮ | 354173 | 20 |
| 5 | የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ | 85175 | 45 |
| 6 | የሰሜን ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ | 101 | 50 |
| 7 | ሰሜን ጎንደር ገንዘብ መምሪያ | 12664 | 70 |
| | ድምር | 2180957 | 47 |

ያልቀረቡትን ማስረጃዎች ለመጥቀስ ያህል የመጓጓዣ ደረሰኝ ያልቀረበለት፣ ፎቶ ኮፒ ማስረጃ የቀረበለት እና በባንክ በኩል የተላከ ሂሳብ ለመድረሱ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ የሚሉት ይገኙበታል ፣

ለወደፊቱ የሂሳብ ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ህጋዊ የወጪ ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ እንዳለበትና ማስረጃ ያልቀረበለትም ሂሣብ እንዲቀርብለት፣ ካልሆነም ገንዘቡ ለሣጥን ተመላሽ እንዲደረግ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡

## 3.2. <u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት</u>
<u>ሂሣብ ብር 7954494.93</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች የተሟላ የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በስድስት መ/ቤቶች የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ብር 7954494.93 ተገኝቷል። ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል።

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የሰሜን ጎንደር ዞን ጤና መምሪያ | 149932 | 07 |
| 2 | የሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብ መምሪያ | 3905525 | 34 |
| 3 | የግብርና ቢሮ | 2963702 | 34 |
| 4 | የጤና ቢሮ | 485902 | 60 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | የሰሜን ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ | 408043 | 70 |
| 6 | የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ | 41388 | 88 |
| | ድምር | 7954494 | 93 |

ተሟልተው ያልቀረቡት ማስረጃዎች ዓይነት በርካታ ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ የግዥ መጠየቂያ ያልቀረበለት፣ የሥራ ትዕዛዝ ደብዳቤ ያልቀረበለት፣ ፋክቱር ባቀረቡ ሠራተኞች ያልተፈረመ፣ የሥራ ሰዓት መቆጣጠሪያ ያልቀረበለት፣ የተላከው ሂሣብ ለመድረሱ ማረጋገጫ ሞ/64 ያልቀረበለት፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት፣ የመኪና ሰሌዳ ቁጥር ያልተጻፈበት የነዳጅ ደረሰኝ፣ የጨረታ ተሳታፊዎች የሥራ ፈቃድ ግብር ለመክፈላቸው ማስረጃ ያልቀረበለት፣ የውል ስምምነት የሌለው፣ ቀን፣ዓ.ም፣ እና የተቀባይ ፊርማ የሌለው እና ሕጋዊ ደረሰኝ መቅረብ ሲገባው ነጭ ወረቀት በማስረጃነት የቀረበለት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። መ/ቤቶች ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ማስረጃዎች ተሟልተው መቅረባቸውን መረጋገጥ እንዳለበትና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢው ቁጥጥር እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

### 3.3. <u>ደንብና መመሪያን ያልተከተለ የግዥ ሂሣብ ብር 5,163,050.50</u>

በበጀት ዓመቱ የተከናወነው ግዥ በወጡት ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈፀሙን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:–

- ሰሜን ጎንደር ዞን ጤና መምሪያ ------- ብር 2897763.63
- ሰሜን ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ ------- 476617.15
- የጤና ቢሮ --------------- 202038.10
- የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ------- 372299.00
- የደቡብ ወሎ ዞን ጤና መምሪያ -------- <u>1214332.27</u>

ድምር ብር <u>5163050.50</u>

የግዥ ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ከተፈፀሙት ግዥዎች መካከል ዕውቅና ካልተሰጣቸው አቅራቢዎች የተፈፀመ ፣ ለጨረታ ኮሚቴ ሳይቀርብ በቀጥታ የተፈፀመ፣

በጨረታ ኮሚቴ በተሰበሰበ ፕሮፎርማ የተፈፀመ፣ግዥ ከተፈፀመ በኋላ የግዥ መጠየቂያ የቀረበለት፣ የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ የተፈፀመ ግዥ እና የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ ኮንትራት የተሰጠ ግንባታ የሚሉት ናቸው። አሰራሩ የፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያን ያልተከተለ በመሆኑ ድርጊቱን በፈፀሙ ሠራተኞች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ እና ለወደፊቱም በዕቃና በአገልግሎት ግዥ ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

3.4. <u>ያለ አግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች ብር 40322.38</u>

ክፍያዎች በወጡት ደንብና መመሪያዎች መሠረት በአግባቡ መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአምስት መ/ቤቶች ውስጥ ያለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 40322.38 ተገኝቷል። ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል።

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የሰሜን ጎንደር ዞን ጤና መምሪያ | 485 | 20 |
| 2 | የጤና ቢሮ | 2775 | 00 |
| 3 | የሰሜን ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ | 33074 | 85 |
| 4 | የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ | 3572 | 03 |
| 5 | የደቡብ ወሎ ጤና መምሪያ | 415 | 30 |
| | ድምር | 40322 | 38 |

ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች በርካታ ቢሆኑም ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል ኃላፊዎች ሳያውቁት ያለአግባብ የተከፈለ አበል፣ ያለገዞ መስመር የመጓጓዣ ደረሰኝ የቀረበለት፣ የሥራ ግብር ሣይቀንስ ለአሠልጣኞች የተከፈለ፣ ለዕቃ ግዥ በብልጫ የተከፈለ እና የስልጣን ውክልና ባልተሰጠው ሠራተኛ ፊርማ የተፈፀመ ክፍያ የሚሉት ይገኙበታል። በመሆኑም ክፍያዎች ደንብና መመሪያን ተከትለው እንዲፈጸሙ እና ያለአግባብ የተከፈለውም ሂሣብ ጉዳዩ ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

3.5. <u>ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ብር 87864.47</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሣቦች ትክክለኛ ማስረጃ ቀርቦላቸው መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፦

- የሰሜን ጎንደር ጤና መምሪያ - - - -   ብር 9323.47
- የሰሜን ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ - - - - -   & 73273.00
- የደቡብ ወሎ ዞን ጤና መምሪያ   & 5268.00

በድምሩ   ብር **87864.47**

የያዘ የወጪ ማስረጃ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል።

ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሣብ ውስጥ ከመጡበት መ/ቤት የውሎ አበል ያልተከፈለ ለመሆኑ ማረጋገጫ ያልቀረበለት፣ ለመ/ቤቱ አገልግሎት ለመስጠቱ ማረጋገጫ ያልቀረበለት እና የሰልጣኞች ዝርዝር ያልቀረበለት የውሎ አበልና የመጓጓዣ ሂሣብ ይገኝበታል።

በመሆኑም የክፍያው ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድና ለወደፊቱም በክፍያ ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

### 3.7. የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሣብ ብር 4039913.75

የተመዘገቡት ሂሳቦች በበጀት ዓመት መ/ቤቶች ሥራ ላይ ያዋሉት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ :–

| | | |
|---|---|---|
| የግብርና ቢሮ - - - - - - - | ብር | 3844054.88 |
| የጤና ቢሮ - - - - - - - - | & | 195858.87 |
| በድምሩ | ብር | 4039913.75 |

ያለፉት በጀት ዓመታት ወጪ ሆኖ ሳለ በ1993 በጀት ዓመት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል።

በመሆኑም አሰራሩ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና የበጀት አዋጁን ያልተከተለ ስለሆነ እንዲታረም በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

### 3.8. ለገንዘብ ቢሮዎችና መምሪያዎች ወርኃዊ ሪፖርት ሳያቀርቡ ስለተገኙት መ/ቤቶች

መ/ቤቶች በቻናል1 ወጭ በሌሎች ቻናሎች የሚያገኙትን ገቢ ለሚመለከተው የገንዘብ ቢሮዎችና መምሪያዎች የሚያሳውቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ እና የክልሉ ጤና ቢሮ

በእርዳታ ያገኙትን ሂሳብ ለሚመለከታቸው የገንዘብ ቢሮ እና መምሪያ በወርኃዊ ሪፖርት እንዳላሳወቁ ተረጋግጧል፡፡

መ/ቤቶች በልዩ ልዩ ቻናሎች ያገኙትን ዕርዳታ በወቅቱ ካላሳወቁ በበጀት ዓመቱ ክልሉ ያገኘውን ገቢና ሥራ ላይ ያዋለውን ሂሣብ ለማወቅ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ተዘጋጅቶ የሚቀርበው የክልሉ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ የተሟላ መረጃ ስለማይሰጥ አሠራሩ መታረም እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ የተጠቀሙበት መሆኑንና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የሚገኘውን ሂሣብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

| ተራ ቁ | የመ/ቤቱ ስም | ያልተሠራበት በጀት | | ከበጀት በላይ የወጣ | | ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ ሂሣብ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግብርና ቢሮ | **4658096** | **59** | **1317339** | **53** | **14737099** | **52** |
| 2 | ጤና ቢሮ | **7986440** | **25** | **582186** | **87** | **13039710** | **87** |
| 3 | የሰሜን ሸዋ ግብርና መምሪያ | **122045** | **26** | — | — | | |
| 4 | የምሥራቅ ጎጃም ዞን ገንዘብ መምሪያ | **8215251** | **46** | — | — | **1929909** | **25** |
| 5 | የሰሜን ጎንደር ጤና መምሪያ | **612105** | **51** | — | — | **18530** | **36** |
| 6 | የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ጤና መምሪያ | **275195** | **80** | — | — | — | — |
| 7 | የሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብ መምሪያ | **1803310** | **52** | — | — | **2594522** | **74** |
| 8 | የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ | **399417** | **72** | — | — | **118837** | **58** |
| ድምር | | **24071863** | **11** | **1899526** | **40** | **32438610** | **32** |

ከላይ እንደተመለከተው ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ያልተሠራበት በጀት ብር 24071863.11፣ ከበጀት በላይ የወጣ ብር 1899526.40፣ በወቅቱ ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ ሂሣብ ብር 32438610.32 መኖሩ ታውቋል።

የበጀት ዝግጅት በበቂ ጥናት የተደገፈና ሊተገበር የሚችል መሆን እንዳለበት እና በበጀት ዓዋጁ ከተፈቀደው በላይ ሥራ ላይ ማዋልም ሆነ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተመለከተውን ከወጪ ቀሪ በወቅቱ ፈሰስ አለማድረግ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብን ያልተከተለ አሰራር መሆኑን በመግለጽ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል።

5. <u>ንብረት</u>

የመ/ቤቶች የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ደንብና መመሪያ የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል።

5.1. የሰሜን ጎንደር ጤና መምሪያ፣

- የንብረት ገቢና ወጪ መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- የቋሚ ዕቃ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣

5.2. የሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብ መምሪያ፣

የመንግሥት የንብረት አስተዳደር ደንብና መመሪያ ሳይጠቅብ ይኸውም :-

| | |
|---|---|
| • በባለሥልጣን ሣይፈቀድ ወጪ የተደረጉ ዕቃዎች | ብር 416.30 |
| ከተጠየቀው በላይ ወጪ የተደረጉ ዕቃዎች | ብር 199.43 |
| በዕቃ መጠየቂያ ብዛትና መስፈሪያ ሣይጠቀስ | |
| በሞ/22 ወጪየተደረጉ ዕቃዎች | ብር <u>1522.13</u> |
| በድምሩ | ብር <u>2137.86</u> |

ዋጋ ያላቸው ንብረቶች ወጪ የተደረገ መሆኑ፣

- የቋሚና አላቂ ዕቃ ቆጠራ የማይከናወንና ለቋሚ ዕቃ መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፣
- አገልግሎት ሊሰጡ በማይችሉ ቋሚ ዕቃዎች ላይ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣

የአላቂና የቋሚ ዕቃ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣

5.3. የግብርና ቢሮ፣

- ቢሮው ካሉት 87 ተሽከርካሪ መኪናዎች ውስጥ መድን /ኢንሹራንስ/ የተገባው ለ6 መኪናዎች ብቻ መሆኑ፣
- አገልግሎት ሊሰጡ በማይችሉ ቋሚ ዕቃዎች ላይ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣
- የአላቂና የቋሚ ዕቃ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣

5.4. የጤና ቢሮ፣

- ዕቃ ግ/ቤት ኃላፊነት እና የዕቃ የምዝገባ ሥራ በአንድ ሠራተኛ የሚከናወን መሆኑ፣
- ገንዘብ ያዥዎችና የዕቃ ግ/ቤት ሠራተኞች ተያዥ የሌላቸው መሆኑ፣
- የዕቃ ግ/ቤት ሠራተኞች ሲቀያየሩ የመዝገብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ እና ርክክቡ በመዝገብ መሠረት አለመሆኑ ፣

የመድሐኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ላይ የተሟላ የገቢና ወጪ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣

አገልግሎት ሊሰጡ በማይችሉ ቋሚ ዕቃዎች ላይ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣

- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ የማይከናወንና ለቋሚ ዕቃዎች የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፣

5.5. የደቡብ ወሎ ዞን ግብርና መምሪያ

- የቋሚና አላቂ ዕቃ ቆጠራ የማይከናወን መሆኑ፣
- ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፣
- የቋሚና የአላቂ ዕቃ ምዝገባ የማይከናወን ሆኖ መገኘቱ፣

5.6. የሰሜን ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ፣

አገልግሎት ሊሰጡ በማይችሉ ቋሚ ዕቃዎች ላይ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣

የቋሚና አላቂ ዕቃ ምዝገባ አለመከናወኑ፣

የቋሚና አላቂ ዕቃ ቆጠራ ያልተከናወነ መሆኑ፣

ለቋሚ ዕቃ መለያ ቁጥር አለመስጠቱ፣

- መምሪያው ካሉት 60 ተሽከርካሪመኪናዎች ውስጥ፣

| | ብዛት |
|---|---|
| - ከ1 ዓመት በላይ የቆሙ | 30 |
| - ሞተሮቻቸው በአካላቸው ላይ ያልተገኘ | 3 |
| - ሊብሬ ቀርቦ ተሽከርካሪዎቹ በአካል ያልተገኙ | 18 |
| - ሞተሩ የተቀየረ | 1 |
| - ሊብሬ የሌላቸው | 5 |
| - ሚችልኮትስ ለመግባቱ ማረጋገጫ ያልቀረበለት | 1 |

እንዳለው ታውቋል።

5.8. የደቡብ ወሎ ዞን ጤና መምሪያ፣

የቋሚና አላቂ ዕቃ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣

♦ አገልግሎት ሊሰጡ በማይችሉ ቋሚ ዕቃዎች ላይ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣

ከላይ የተጠቀሱት የአሰራር ድክመቶች፣ እንዲታረሙ የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅም የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ በሚያዘው መሠረት እንዲፈፀም ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እንደለባቸው ለየመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

6. <u>ልዩ ልዩ</u>

6.1. <u>ተራፊ በጀት ሣይኖር የተፈፀመ ዝውውር ብር 8123.00፣</u>

የሰሜን ጎንደር ዞን ጤና መምሪያ ተራፊ በጀት መኖሩን ሳይጣራ ብር 8123.00 ለገንዘብ ቢሮ ዝውውር ተፈጽሞ ተገኝቷል።

ይሁን እንጂ የተፈፀሙው ዝውውር ተራፊ በጀት ከሌለው መ/ቤት ላይ በመሆኑ ዝውውር ከመፈፀሙ በፊት ተገቢው ማጣራት እንዲደረግ ዝውውሩን ለፈፀመው የሰሜን ጎንደር ዞን ጤና መምሪያ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

6.2. <u>በካዝና ተገኝተው የተቆጠሩ በአዋጅ የተሻሩና</u>

**<u>የተበላሹ ቴምብሮች ሂሣብ ብር 34691.00፣</u>**

በወቅቱ መወገድ የሚገባቸው በአዋጅ የተሻሩና የተበላሹ ብር 34691.00 ዋጋ ያላቸው ቴምብሮች ያለአግባብ በካዝና ተቀምጠው ተገኝተዋል። ዝርዝሩም ቀጥሎ ተመልክቷል።

| | |
|---|---|
| ♦ የሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብ መምሪያ . . . . . . . | ብር 13996.20 |
| ♦ የምሥራቅ ጎጃም ዞን ገንዘብ መምሪያ . . . . . | 20694.80 |
| ድምሩ | 34691.00 |

ስለሆነም በሥራ ላይ የማይውሉ ቴምብሮች ሊወገዱ የሚችሉበት ሁኔታ እንዲመቻች በተላከው ሪፖርት አሳስበናል።

## 6.3. <u>በቀድሞ ዕቃ ግ/ቤት ሠራተኛ በጉድለት የሚፈለጉ ደረሰኞች</u>

የሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብ መምሪያ ከቀድሞ የመምሪያው ዕቃ ግ/ቤት ሠራተኛ በጉድለት የሚፈለጉ፣

| | |
|---|---|
| የተለያዩ የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች | 24 |
| የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) | 20 |
| የቴምብር ወጪ መጠየቂያ (ሞ/128) | 1 |
| በድምሩ | 45 |

በእነዚህ ደረሰኞች ላይ ሕገወጥ ተግባር ሊፈፀምባቸው እንደሚችል እየታወቀ እስካሁን ምንም ዓይነት እርምጃ አለመወሰዱ ታውቋል። አሁንም በጉዳዩ ላይ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 6.4. <u>የኦዲት ሪፖርት መልስ አለመሰጠትን በተመለከተ፣</u>

መ/ቤቶች ለተላከላቸው ኦዲት ሪፖርት በአዋጅ መሠረት በ30 ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት መልስ የሚሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ማጣራት ሲደረግ የክልሉ ጤና ቢሮ ለ1991 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት መልስ አልሰጠም። በግኝቶቹም ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወስድና ለኦዲት ሪፖርቶቹ መልስ እንዲሰጥ የሚመለከተው የበላይ አካል ክትትል ሊያደርግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
## የሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥስት
## የ1993 በጀት ዓመት የድጋፍና ድጎማ
## ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

በ1993 በጀት ዓመት ከፌዴራል መንግሥት ለክልሉ መንግሥት የተመደበውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎችን ሂሣብ በአዋጅ ቁጥር 68/1989 አንቀጽ 7/2 መሠረት የሁለት መ/ቤቶች ሂሣብ ኦዲት ተከናውኗል። መ/ቤቶቹም የክልሉ ጤና ቢሮ እና የክልሉ ትምህርት ቢሮ ሲሆኑ፤ የኦዲት ሪፖርቱ ለሁለቱም መ/ቤቶች በየአድራሻቸው የተላከ ቢሆንም በሪፖርቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት፣ በኦዲት ውጤቱ ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው ሁሉም መ/ቤቶች መልስ ሳይሰጡ ቀርተዋል።

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ</u>

1.1. <u>በብልጫ የተገኘ</u>

<u>ብር 107,078.07፣</u>

የክልሉ ትምህርት ቢሮ ከወጪ ቀሪ ሂሣብ ሲመዛዘን ብር 107,078.07 በብልጫ ተገኝቷል። በብልጫ ለታየው ሂሣብ የገቢ ደረሰኝ እንዲቆረጥለት በሪፖርታችን ያሳሰብን ቢሆንም ስለተወሰደው እርምጃ ከክልል ምክር ቤቱም ሆነ ከቢሮው ምላሽ አልተሰጠም።

1.2. <u>በካዝና ተገኝቶ የተቀጠረ</u>

<u>ብር 165,776.70፣</u>

የየመ/ቤቶቹ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በሚገባ መጠበቁንና በመመሪያ ከተፈቀደው ብር 5,000.00 በላይ በካዝና ውስጥ የማይቀመጥ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ብር 165,776.70 በመመሪያ ከታዘዘው በላይ በካዝና ውስጥ ተገኝቶ ተቆጥሯል። ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል።

| | | |
|---|---|---|
| በጤና ቢሮ - - - - - - - - - | ብር | 103,282.17 |
| በትምህርት - - - - - - - | | <u>62,494.53</u> |
| ድምር | | <u>165,776.70</u> |

በመመሪያው መሠረት ማንኛውም መ/ቤት ከብር 5,000.00 በላይ ጥሬ ገንዘብ በሣጥን ማሳደር እንደሌለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

1.3. <u>ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ብር 8,408,482.82</u>

ኦዲት በተደረጉት በሁለቱም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተወራረደ ብር 8,408,482.82 ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

- ጤና ቢሮ - - - - - - - - - - ብር 5,387,410.26
- ትምህርት ቢሮ - - - - - - - 3,021,072.56

በድምሩ ብር 8,408,482.82

ለወደፊቱ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ በተደነገገው መሠረት የሰነድ ሂሣብ በወቅቱ መወራረድ ስላለበት ያልተወራረደው ሂሣብ በአፋጣኝ እንዲወራረድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና መመዝገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1. <u>የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት</u>

<u>ብር 3,634,433.61</u>

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/89 አንቀጽ 32/1 መሠረት በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ ህጋዊ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡–

- በጤና ቢሮ - - - - - - - - - ብር 60,750.39

በትምህርት ቢሮ - - - - - 3,573,683.22

በድምሩ 3,634,433.61

የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሣብ እንዲቆረጥለትና ለወደፊቱም መንግሥት ባወጣው ደንብ መሠረት እንዲሠራ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሣቦች የተሟላ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን፣ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት መፈፀማቸውንና ጉልህ

ግድፈቶች አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

3.1. <u>የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት</u>

<u>**ብር 17,041,469.03**</u>

በወጪ የተመዘገበው ሂሣብ የተሟላ ማስረጃ የቀረበለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በጤና ቢሮ - - - - - - - - - - - ብር **8,132,097.00**

በትምህርት ቢሮ - - - - - - - - **<u>8,909,372.03</u>**

በድምሩ **<u>17,041,469.03</u>**

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም ውስጥ የኮንስትራክሽን ውል ፣ የጨረታ ሰነድ ፣ የግዥ መጠየቂያ እና የተሟላ የውሎ አበል ቅጽ ያልቀረበለት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ፡፡

ስለሆነም ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ማስረጃዎች የተሟሉ መሆናቸው መረጋገጥ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

3.2. <u>የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት</u>

<u>**ሂሣብ ብር 8,796,900.15**</u>

የተመዘገቡት ሂሣቦች ተገቢው ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በክልሉ ትምህርት ቢሮ ሕጋዊ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ ብር **8,796,900.15** ተገኝቷል፡፡

በወጪ ለተመዘገበው ሂሣብ ትክክለኛ ማስረጃ እንዲቀርብለት ወይም ጉዳዩ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

3.3. የ<u>ንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት</u>

<u>**ብር 6,805,698.00**</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዙት ዕቃዎች በሙሉ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በክልሉ ትምህርት ቢሮ በብር

6,805,698.00 የተገዛ ዕቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገበት የንብረት ገቢ ደረሰኝ አልቀረበም፡፡

በመሆኑም የተገዛው ዕቃ ለመ/ቤቱ አገልግሎት የዋለ መሆኑ በውስጥ ኦዲት በኩል ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

4. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ እንዲሁም በበጀት ዓዋጁ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውንና የበጀት ዓመቱ ከወጪ ቀሪ ሂሣብ በወቅቱ ፈሰስ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

| ተራ ቁ | የመቤቱ ሥም | ያልተሠራበት በጀት | ከበጀት በላይ የወጣ | ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ ሂሣብ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የክልሉ ጤና ቢሮ | 6,517,320.70 | 1,183,069.10 | 3,046,239.61 |
| 2 | የክልሉ ትምህርት ቢሮ | 5,368,266.52 | 31,310.75 | 3,767,874.85 |
| | ድምር | 11,885,587.22 | 1,214,379.85 | 6,814,114.46 |

ከላይ እንደተመለከተው በሁለቱም መ/ቤቶች ያልተሠራበት በጀት ብር 11,885,587.22 ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገ ብር 1,214,379.85 በወቅቱ ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ ብር 6,814,114.46 መኖሩ ታውቋል፡፡

የበጀት ዝግጅት በበቂ ጥናት የተደገፈና ሊተገበር የሚችል መሆን እንዳለበት፣ በበጀት ዓዋጅ ከተፈቀደው በላይ ሥራ ላይ ማዋልም ሆነ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተመለከተውን ከወጪ ቀሪ በወቅቱ ፈሰስ አለማድረግ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብን ያልተከተለ አሰራር መሆኑን በመግለጽ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

5. <u>ልዩ ልዩ</u>

በሁለቱም ቢሮዎች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ አልተቋቋመም፡፡

በጤና ቢሮ በደንቡ መሠረት በወቅቱ ያልተመዘገበ ማስረጃ የቀረበለት ሂሣብ ብር 498,576.38 ተገኝቷል፡፡

በጤና ቢሮ በብልጫ የተመዘገበ የወጪ ሂሣብ ብር 1,229.00 ተገኝቷል፡፡

በጤና ቢሮ በብር 2.9 ሚሊዮን የተገዙ የላውንደሪ የአይረኒንግ እና የድራይንግ ማሽኖች ከሁለት ዓመት በላይ ያለአገልግሎት ለፀሀይና ዝናብ ተጋልጠው ተገኝተዋል ፡፡

የትምህርት ቢሮ በ1991 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት ውጤትና አስተያየት ላይ እርምጃ አልወሰደም፡፡ ለተላከው ሪፖርትም መልስ አልተሰጠም፡፡

ከላይ የተመለከቱት የአሰራር ድክመቶች እንዲታረሙና እንዲስተካከሉ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

<u>**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**</u>

<u>**የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት**</u>

<u>**የ1993 በጀት ዓመት የድጋፍና ድጎማ ሂሣብ ኦዲት**</u>

በ1993 በጀት ዓመት ከፌዴራል መንግሥት ለክልሉ መንግሥት የተመደበውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎችን በአዋጅ ቁጥር 68/1989 አንቀጽ 7/2 መሠረት ኦዲት ለማድረግ አቅዶ በአስራ አንድ መ/ቤቶች ሂሣብ ኦዲቱን አከናውኗል፡፡

በዚህ መሠረት:-

የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ

የትምህርት ቢሮ

የከምባታና ጠምባሮ ዞን ትምህርት መምሪያ

የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መመሪያ

የሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ

የጌዲኦ ዞን ጤና መምሪያ

የከምባታና ጠምባሮ ዞን ጤና መምሪያ

የጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ

የሀዲያ ዞን ግብርና መምሪያ

የወላይታ ዞን ግብርና መምሪያ፣

የጌዲኦ ዞን ግብርና መምሪያ፣ መ/ቤቶቹ ኦዲት ተደርገው ሪፖርቱ ለኦዲት ተደራጊዎች በየአድራሻቸው የተላከ ሲሆን

በሪፖርቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት እና በኦዲት ውጤቱ ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው (3) መ/ቤቶች በወቅቱ መልስ የሰጡ ሲሆን 8 መ/ቤቶች ደግሞ መልስ አልሰጡም፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተ/ራ | የመ/ቤቱ ስም | በወቅቱ መልስ የሰጡ (✔) | መልስ ያልሰጡ (✔) |
|---|---|---|---|
| 1 | የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | | ✔ |
| 2 | የከምባታና ጠምባሮ ዞን ትምህርት መምሪያ | ✔ | |
| 3 | የትምህርት ቢሮ | | ✔ |
| 4 | የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መምሪያ | | ✔ |
| 5 | የሀድያ ዞን ትምህርት መምሪያ | ✔ | |
| 6 | የጌድዮ ዞን ጤና መምሪያ | | ✔ |
| 7 | የከምባታና ጠምባሮ ዞን ጤና መምሪያ | | ✔ |
| 8 | የጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ | | ✔ |
| 9 | የሀድያ ዞን ግብርና መምሪያ | ✔ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **10** | የወላይታ ዞን ግብርና መምሪያ | | ✔ |
| **11** | የጌድኦ ዞን ግብርና መምሪያ | | ✔ |

<u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ</u>

1.1 <u>ጥሬ ገንዘብ ማመዛዘን ያልተቻለ ስለመሆኑ</u>

ኦዲት የተደረጉት መ/ቤቶች በሙሉ ሂሳባቸውን በየወሩ የማይዘጉ፣ በመዝገብ የተመለከተውም ከወጪ ቀሪ በካዝናና በባንክ ካለው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ጋር በማገናዘብ ትክክለኛነቱን የማያረጋግጡ በመሆኑ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ማመዛዘን አልተቻለም:: በመሆኑም አሰራሩ እንዲስተካከል በላክነው ሪፖርት አሳስበናል::

1.2 <u>ውዝፍ የሰነድ ሂሳብ ብር 7,925,153.92</u>

ኦዲት በተደረጉ 11 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 7,925,153.92 ውዝፍ የሰነድ ሂሳብ ተገኝቷል::

ውዝፍ የሰነድ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል::

| ተ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | 5,618,552 | 63 |
| 2 | የትምህርት ቢሮ | 26,457 | 68 |
| 3 | የከምባታና ጠምባሮ ዞን ትምህርት መምሪያ | 54,266 | 10 |
| 4 | የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መምሪያ | 1,676,119 | 06 |
| 5 | የሀዲያ ዞን ጤና መምሪያ | 26,478 | 39 |
| 6 | የጌዲኦ ዞን ጤና መምሪያ | 13,124 | 52 |
| 7 | የጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ | 299,746 | 34 |
| 8 | የካምባታና ጠምባሮ ዞን ጤና መምሪያ | 3,997 | 79 |
| 9 | የሀዲያ ዞን ግብርና መምሪያ | 155,423 | 78 |
| 10 | የወላይታ ዞን ግብርና መምሪያ | 19,612 | 58 |
| 11 | የጌዲኦ ዞን ግብርና መምሪያ | 31,375 | 05 |
| | ጠቅላላ ድምር | 7,925,153 | 92 |

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 38/1 መሠረት ለሥራ ማስኬጃ በተለይ ለግዥ በሠነድ የወጣ ሂሳብ በሰባት የሥራ ቀናት፣ የደመወዝ

ሠነድ ሂሳብ ደግሞ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ መወራረድ እንዳለበት የታዘዘ ሲሆን፣ ኦዲት በተደረጉት 11 መ/ቤቶች ከላይ የተመለከተው ውዝፍ የሠነድ ሂሳብ ሊገኝ ችሏል፡፡ ስለሆነም መ/ቤቶቹ የተገኙባቸውን ውዝፍ የሰነድ ሂሳብ እንዲያወራርዱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. <u>የገቢ ሂሳብ</u>

ኦዲት የተደረጉት መ/ቤቶች የገቢ ሂሳብ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት መያዙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

- የከምባታ ጠምባሮ ዞን ትምህርት መምሪያ:- ......................ብር 10,154.43
- የወላይታ ዞን ግብርና መምሪያ............................................ብር 25,957.18

በድምሩ ብር 36,111.61 የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት በመገኘቱ ለሂሳቡ ደረሰኝ እንዲዘጋጅለትና ለወደፊቱ በፋይናንስ ደንብና መመሪያው መሠረት እንዲሰራ አሳስበናል፡፡

3. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በማስረጃ የተደገ| መሆኑን፣ ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያዎች መሠረት መፈፀማቸውን፣ የፋይናንስ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መከበራቸውንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

3.1 <u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ብር2,512,810.59</u>

ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች በዘጠኙ የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ብር 2,512,810.59 የተገኘ ሲሆን የመ/ቤቶቹ ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | 29,273 | 37 |
| 2 | የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ | 53,289 | 15 |
| 3 | የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መምሪያ | 467,654 | 06 |
| 4 | የሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ | 72,588 | 26 |
| 5 | የጌዲኦ ዞን ጤና መምሪያ | 1,791,552 | 32 |
| 6 | የጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ | 90,722 | 03 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7 | የጌዴኦ ዞን ግብርና መምሪያ | 5,369 | 55 |
| | ጠቅላላ ድምር | 2,512,810 | 59 |

ያልተሟሉ ማስረጃዎች ለመጥቀስ ያህል ተረካቢና አስረካቢ ያልፈረመበት የንብረት ገቢ ደረሰኝ፣ የዕቃ ግዥና የጥገና መጠየቂያ ያልቀረበለት፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት፣ የውል ስምምነት ያልቀረበለት ፣ ተገቢው ፋክቱር ያልቀረበለት፣ የከፋይ መ/ቤት ስም ያልያዘ ፋክቱር፣ የገንዘብ ያዥ ፊርማ ያልያዘ፣ የመኪና ሰሌዳ ቁጥር ያልተፃፈበት የነዳጅ ግዥ ፋክቱር፣ የመነሻና መመለሻ ሰዓት ያልተጠቀሰበት የውሎ አበል ቅጽ፣ ቀን ያልተፃፈባቸውና የተቀባይ ፊርማ የሌላቸው ፋክቱሮች የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ለወደፊቱ የወጪ ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት የተሟላ ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2 <u>ከደንብና መመሪያ ውጭ የተፈፀመ ክፍያ ብር 84,691.56</u>

ክፍያዎች ደንብና መመሪያዎች ተከብረው በአግባቡ መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡

| ተራ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | 11,686 | 05 |
| 2 | የትምህርት ቢሮ | 19,941 | 44 |
| 3 | የከምባታና ጠምባሮ ዞን ትምህርት መምሪያ | 4,181 | 74 |
| 4 | የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መምሪያ | 5,497 | 33 |
| 5 | የሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ | 6,050 | 64 |
| 6 | የጌዴኦ ዞን ጤና መምሪያ | 5,941 | 70 |
| 7 | የጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ | 12,391 | 90 |
| 8 | የከምባታና ጠምባሮ ዞን ጤና መምሪያ | 6,971 | 91 |
| 9 | የሀዲያ ዞን ግብርና መምሪያ | 9,900 | 50 |
| 10 | የወላይታ ዞን ግብርና መምሪያ | 1,040 | 35 |
| 11 | የጌዴኦ ዞን ግብርና መምሪያ | 1,088 | 00 |
| | ጠቅላላ ድምር | 84,691 | 56 |

ከደንብና መመሪያ ውጭ መስክ ላልሄዱ ሠራተኞች የተከፈለ ውሎ አበል፣ በብልጫ የተከፈለ የውሎ አበል፣ ከመመሪያ ውጭ ለደንብ ልብስ መግዣ የተከፈለና፣ ለኮንትራክተር በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ አሠራሩ ከደንብና መመሪያ ውጭ በመሆኑ መስክ ላልሄዱ እና ያለአግባብ በብልጫ የተከፈለው ሂሳብ እንዲተካ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3 <u>የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ ብር 32615.32</u>

መ/ቤቶች በተፈቀደላቸው በጀት መሠረት ወጪያቸውን ተቆጣጥረው የሚይዙ መሆኑንና ሂሳቡም በተፈቀደው በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

ከጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መምሪያ.................................ብር 31,315.32

ከሐዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ.....................................ብር 1000.00

ከጌዲኦ ዞን ጤና መምሪያ.............................................ብር <u>300.00</u>

ድምር ብር <u>32,615.32</u>

በድምሩ ለብር 32,615.32 የቀረቡት የወጪ ማስረጃዎች ከበጀት አመቱ ውጭ የተከፈሉ መሆኑ ታውቋል፡፡ አሠራሩ የበጀት አፈፃፀም ደንብና መመሪያን ያልተከተለ መሆኑን ገልጸን፤ ለወደፊቱ የወጪ ሂሳብ ክፍያ በተፈፀመበት የበጀት ዓመት እንዲመዘገብ አሳስበናል፡፡

3.4 <u>የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ብር 218,147.35</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በሙሉ በማስረጃ የተደገ| መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ

በጌዲኦ ዞን ጤና መምሪያ.......................................... ብር 217,967.35

በከምባታና ጠምባሮ ዞን ጤና መምሪያ...........................ብር 180.00

በድምሩ ብር 218,147.35 የክፍያ ማስረጃ ሳይቀርብ ተመዝግቦ የተገኘ ሲሆን ይህም አግባብ አለመሆኑን ገልጸን በወጪ ለተመዘገበው ሂሳብ ማስረጃ እንዲቀርብለት ይህ ካልተቻለ ደግሞ ገንዘቡ እንዲተካና ለወደፊቱም ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ እንደሚኖርበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.5 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ</u>

<u>ያልቀረበለት ሂሣብ ብር 29409.50</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዙት ዕቃዎች በሙሉ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ :-

- በከምባታ ጠምባሮ ዞን ትምህርት መምሪያ ..... ብር 12,166.53
- በሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ .................... ብር 16 ,782.97
- በሀዲያ ዞን ግብርና መምሪያ ...................... ብር 460.00

በድምሩ በብር 29,409.50

የተገዛ ዕቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የሆነበት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ ሂሣቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ይህ ተገቢ ስላልሆነ ተገዝቷል የተባለው ንብረት ገቢ መደረግ እንዳለበት አለዚያም ለግዥ የወጣው ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆንና ጉዳዩም በውስጥ ኦዲት በኩል ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

ኦዲት የተደረጉት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን፣ ከበጀት በላይ ወጪ ያለማድረጋቸውን እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የሚገኘውን ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

| ተራ/ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | ያልተሰራበት በጀት | | ከበጀት በላይ የወጣ | | ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ | 122,212 | 09 | | | 4,642,173 | 64 |
| 2 | የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ | 10,840,872 | 74 | | | 71,373 | 06 |
| 3 | የከምባታና ጠምባሮ ዞን ትምህርት መምሪያ | 694,214 | 81 | | | 6,066 | 98 |
| 4 | የጋሞጎፋ ዞን ትምህርት መምሪያ | 2,028,836 | 32 | | | | |
| 5 | የሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ | 798,083 | 11 | | | 129 | 51 |
| 6 | የጌዲኦ ዞን ጤና መምሪያ | 406,587 | 12 | | | 10,514 | 69 |
| 7 | የጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ | 229,635 | 90 | 753 | 89 | | |
| 8 | የከምባታና ጠምባሮ ዞን ጤና መምሪያ | 12,558 | 29 | | | 2,126 | 80 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | የሀዲያ ዞን ግብርና መምሪያ | 13,821 | 89 | 239 | 58 | 2,437 | 49 |
| 10 | የወላይታ ዞን ግብርና መምሪያ | 2,726 | 57 | 11,203 | 45 | | |
| 11 | የጌዲኦ ዞን ግብርና መምሪያ | 3,470 | 71 | | | | |
| | ጠቅላላ ድምር | 15,153,019 | 55 | 12,196 | 92 | 4,734,822 | 17 |

ከላይ እንደተመለከተው በአስራ አንድ መ/ቤቶች ብር 15,153,019.55 ያልተሰራበት በጀት፣ በሶስት መ/ቤቶች ብር 12,196.92 ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገ ሲሆን በሰባት መ/ቤቶች በወቅቱ ፈሰስ ያልተደረገ ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ብር 4,734,822.17 ተገኝቷል። የመ/ቤት የበጀት አጠቃቀም ደንብና መመሪያን ያልተከተለ መሆኑን በመግለፅ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በሪፖርታችን አስገንዝበናል።

5. <u>የንብረት ሂሳብ</u>

የመ/ቤቶቹ የንብረት አያያዝና አጠቃቀም ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል።

ኦዲት ከተደረጉት በዘጠኙ መ/ቤቶች በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ የዕቃ ቆጠራ በማድረግ የንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛ መሆኑን የማያረጋግጡ መሆኑ፣

ኦዲት ከተደረጉት በስድስቱ መ/ቤቶች በትውስት ቅጽ ወጪ መደረግ የነበረባቸው ቋሚ ዕቃዎች በዕቃ ወጪ ደረሰኝ ሞ/22 ወጪ የሚያደርጉ መሆኑ፣

ኦዲት ከተደረጉት በአራቱ መ/ቤቶች የዕቃ ገቢና ወጪ መቆጣጠሪያ መዝገብ ሳይቋቋም መገኘቱ፣

ኦዲት ከተደረጉት በአራቱ መ/ቤቶች የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊነትና የንብረት ፀሐፊነት ሥራዎች በአንድ ሠራተኛ ተደርበው የሚሰሩ መሆኑ፣

ኦዲት ከተደረጉት በአራቱ ከአገልግሎት ውጪ በሆኑ ዕቃዎች ላይ በመመሪያው መሠረት ተገቢውን እርምጃ ሳይወስዱ የተገኙ መሆኑ፣

- ኦዲት ከተደረጉት በሁለቱ ቀደም ብሎ የነበሩት የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊዎች በአዲስ ሲተኩ ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ኦዲት ሳይደረግ ተተኪው ሠራተኛ እንዲረከብ የተደረገ መሆኑ፣

ኦዲት ከተደረጉት በሶስት መ/ቤቶች ዕቃዎች ለብልሽት በሚጋለጡበት ሁኔታ ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ እና

ኦዲት ከተደረጉት በሰባቱ መ/ቤቶች አርባ ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት ለረዥም ጊዜ የቆሙና በአራቱ ደግሞ አስራ አምስት (18) ተሽከርካሪዎች ሊብሬ ያልወጣላቸው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል።

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን የአሰራር ግድፈቶች በማስተካከል የመንግስት ንብረት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውልና እንዲጠበቅ ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በመግለፅ ለየመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል።

6. ልዩ ልዩ

በትምህርት ቢሮ በድጋሚ የተመዘገበ የጥሬ ገንዘብ መገኘቱ፣

በሁለቱ መ/ቤቶች ገንዘብ ተከፍሎ በሚቀርበው ፋክቱር ላይ ገንዘቡን የከፈለው ሠራተኛ ፋክቱሩን ለማቅረቡ ምልክት የማያደርግ ወይም ፋክቱሩ ጀርባ ላይ የማይፈርም መሆኑ፣

በሶስት መ/ቤቶች ከሠራተኞች መሰብሰብ የሚገባው ዕዳ በወቅቱ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

አምስት መ/ቤቶች የስራ ሰዓት መቆጣጠሪያ ደብተር በተሟላ መልኩ የማይጠቀሙ እና የዓመት ፈቃድ ለመቆጣጠር የሚያስችል ምዝገባ የማያከናውኑ መሆኑ ፣

- በሁለት መ/ቤቶች የዕቃ ግዥና ተሽከርካሪዎች ጥገና ሲፈፀም የግዢና ጥገና መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- በሶስት መ/ቤቶች ገንዘብ ያገኙ ገንዘብ ለመከፈላቸው በወጪ ቫውቸር ላይ የማይፈርሙ መሆኑ ፣
- በከምባታና ጠምባሮ ዞን 717 መምሪያ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ መቆጣጠሪያ መዝገብ የየወሩ የገቢና የወጪ ያልተደመረና ከወጪ ቀሪውም በአግባቡ እንዲዞር ያልተደረገ መሆኑ፣
- በጋሞጎፋ ዞን ጤና መምሪያ በማቴርያልና በሙያ አገልግሎት የሚያገኘውን ዕርዳታ በገንዘብ እየተመነ በሂሳብ እንዲያዝ የማይደረግ መሆኑ፣
- በከምባታና ጠምባሮ ዞን ጤና መምሪያ የባለዕዳዎች /የተሰብሳቢ/ ሂሣብ መከታተያ መዝገብ /ሌጀር/ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- በጌድኦ ዞን ጤና መምሪያ በማሕደር ውስጥ የሚታሰሩ ደብደቤዎች ተከታታይ ቁጥር የማይሠጣቸው መሆኑ፣

- የአደራ ሂሳብ በመዝገብ የማይመዘገብ መሆኑ እና
- በሃዲያ ዞን ግብርና መምሪያ ኮንትራክተሮች ለተቀበሉት ገንዘብ ሕጋዊ ደረሰኝ /ፋክቱር/ የማይሰጡ መሆኑ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ የተጠቀሱት የአሰራር ግድፈቶችና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲታረሙ ለየመ/ቤቶች በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ</u>

<u>የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት</u>

<u>የ1993 በጀት ዓመት የድጋፍና ድጎማ</u>

<u>ሂሣብ ኦዲት</u>

በ1993 በጀት ዓመት ከፌዴራል መንግሥት ለክልሉ መንግሥት የተመደበውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ልዩ ድጎማዎችን በአዋጅ ቁጥር 68/1989 አንቀጽ 7/2 መሠረት ኦዲት ለማድረግ አቅዶ በአራት መ/ቤቶች ሂሣብ ኦዲቱን አከናውኗል፡፡ መ/ቤቶቹም፡–

የውሃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ

የግብርና ልማት ቢሮ፣

የጤና ቢሮ፣

የትምህርትና ባህል ቢሮ ሲሆኑ፣ መ/ቤቶቹ ኦዲት ተደርገው ሪፖርቱ ለኦዲት ተደራጊዎች በየአድራሻቸው የተላከ ቢሆንም በሪፖርቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት እና በኦዲት ውጤቱ ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው ሁሉም መ/ቤቶች መልስ ሳይሰጡ ቀርተዋል፡

በአጠቃላይ በአሠራርና በፋይናንስ ረገድ ከተገኙት ድክመቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ</u>

1.1 <u>የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 2,468.65</u>

በክልሉ ኦዲት ከተደረጉት አራት መ/ቤቶች ውስጥ በውኃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ብቻ ብር 2,468.65 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ ጉድለቱን የፈፀሙት ገንዘብ ያዥዎች ሂሣቡን ባንክ ገቢ ለማድረጋቸው ኦዲቱ ከመጠናቀቁ በፊት የባንክ ገቢ ደረሰኝ አቅርበዋል፡፡ ጉድለቱ ሊገኝ የቻለው በጥሬ ገንዘብ መዝገብ ላይ በየጊዜው ቁጥጥር እየተደረገ ሪፖርት የማይቀርብ በመሆኑ ነው፡፡ ለወደፊቱ ተመሣሣይ ጉድለት እንዳይከሰት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን ማጠናከር እንደሚገባ በሪፖርት ገልፀናል፡፡

1.2 <u>በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ</u>

<u>ብር 103,419.19</u>

የየቢሮዎቹ የሣጥንና የባንክ ሂሣብ ከወጪ ቀሪ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት የጥሬ ገንዘብ በካዝና ውስጥ ተገኝቶ ተቆጥሯል፡፡

| ተራ ቁጥር | የመሥሪያ ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የውሃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | 17,576 | 72 |
| 2 | የግብርና ልማት ቢሮ | 85,842 | 47 |
| | ድምር | 103,419 | 19 |

የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የሚሰበሰቡት የዕለት ገቢ ከብር 5,000 በላይ ከሆነ በዕለቱ ወይም በተከታዩ የሥራ ቀን ባንክ ገቢ እንዲደረግ መመሪያው የሚያዝ ሆኖ ሳለ ተግባራዊ ባለመደረጉ የተከሰተ መሆኑን በመግለጽ ሁኔታውን እንዲያስተካክሉ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

1.3. <u>ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ</u>

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 38/1 መሠረት ለሥራ ማስኬጃ በተለይ ግዥን በተመለከተ በሠነድ የወጣ ሂሣብ በሰባት የሥራ ቀናት፣ የደመወዝ ሰነድ ሂሣብ ደግሞ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ መወራረድ እንዳለበት የታዘዘ ሲሆን፣ ኦዲት ከተደረጉት በሁለት መ/ቤቶች ያልተወራረደ ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ብር 9,496,615.80 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ሁኔታውም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁ | የመሥሪያ ቤቱ ሥም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | በውሃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | 6,653,178 | 51 |
| 2 | በግብርና ልማት ቢሮ | 2,843,437 | 29 |
| | ድምር | 9,496,615 | 80 |

በመሆኑም ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ በደንቡ መሠረት በአፋጣኝ እንዲወራረድ እና ለወደፊቱም ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በማስረጃ የተደገፉ መሆኑን፣ ክፍያዎች በአግባቡ መመዝገባቸውንና ደንቦችና መመሪያዎች ተከትለው መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1. <u>የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሣብ</u>

<u>ብር 281,666.16</u>

በወጪ ለተመዘገቡት ሂሣቦች የቀረቡት ደጋፊ የወጪ ማስረጃዎች በበጀት ዓመቱ ገንዘብ የተከፈለባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሣብ ብር 281,666.16 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ሁኔታውም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁጥር | የመሥሪያ ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | በውሃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | **110,088** | **00** |
| 2 | የግብርና ልማት ቢሮ | **109,267** | **89** |
| 3 | የጤና ቢሮ | **1,616** | **83** |
| 4 | የትምህርትና ባህል ቢሮ | **60,693** | **44** |
| | ድምር | **281,666** | **16** |

የየበጀት ዓመቱ ወጪ ሥራ ላይ በዋለበት በጀት ዓመት መወራረድና መመዝገብ እንዳለበት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ የሚያዝ ስለሆነ ባለፉት ዓመታት ሥራ ላይ የዋለን ሂሳብ በተከታዩ በጀት በወጪ መመዝገብ ተገቢ እንዳልሆነና ለወደፊቱም ተመሣሣይ የአሠራር ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢው ቁጥጥር እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሣስበናል፡፡

2.2 <u>የተ◊ላ የወጪ ማስረጃ</u>

<u>ያልቀረበለት ብር 17,575,838.71</u>

በክልሉ ኦዲት ከተደረጉት አራት መ/ቤቶች በሁለቱ ውስጥ የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ብር 17,575,838.71 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ሁኔታውም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የውኃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ | 4,045,626 | 71 |
| 2 | ትምህርትና ባህል ቢሮ | 13,530,212 | 00 |
| | ድምር | 17,575,838 | 71 |

ያልተሟሉት ማስረጃዎች ዓይነት በርካታ ቢሆኑም ለአብነት ያህል የውሎ አበል ቅጽ ላይ መነሻና መድረሻ ሠዓት ያልተገለፀ፣ የባለሙያ ማረጋገጫ ያልቀረበለት የጥገና ሥራ፣ የጨረታ ሠነድ ወይም ዝርዝር የጨረታ ትንታኔና ቃለ ጉባኤ ያልቀረበለት፣ የሥራ ዝርዝርና የዋጋ ተመን ያልቀረበለት፣ የቅጥርና የውክልና ማስረጃ ያልቀረበለት ፣ የክፍያ መጠየቂያ (ቢል) ያልቀረበለት፣ የተጓዥ ሠራተኞች ብዛትና የጉዞ ዋጋ ተመን (ታሪፍ) ያልተገለፀለት የሚሉት ይገኙበታል፡፡ በመሆኑም ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ማስረጃዎች ተሟልተው መቅረባቸው መረጋገጥ እንዳለበት በመግለጽ ለወደፊቱ ተመሣሣይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሣስበናል፡፡

2.3. <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት</u>

<u>ብር 1,177,642.00</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዙት ዕቃዎች በሙሉ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በትምህርትና ባህል ቢሮ በብር 1,177,642.00 የተገዙ ዕቃዎች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረጉበት የንብረት ገቢ ደረሰኝ አልቀረበም፡፡ ስለሆነም የተገዛው ዕቃ ለቢሮው አልግሎት የዋለ መሆኑ ተጣርቶ በውጤቱ መሠረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና ለወደፊቱም ተመሣሣይ

ስህተት እንዳይፈፀም ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት የተገዛው ዕቃ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጉ መጣራት እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

## 2.4. የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ

### ያልተቻለ ሂሣብ ብር 17,070.50

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በበቂና አስተማማኝ ማስረጃዎች የተደገፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ብር 17,070.50 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ ቁጥር | የመሥሪያ ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | የውኃ ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ | 154 | 50 |
| 2 | የግብርና ልማት ቢሮ | 15,000 | 00 |
| 3 | የትምህርትና ባህል ቢሮ | 1916 | 00 |
| | ድምር | 17,070 | 50 |

ለመጓጓዣ ተከፍሎ የቀረቡት የተለያዩ ደረሰኞች አጠራጣሪ ሆነው በመገኘታቸው ወጪው ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ እና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈፀም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳበት በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

## 2.5. የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት

### ብር 23,437.10

በወጪ የተመዘገቡት ሂሣቦች ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ብር 23,437.10 የተሟላ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ሁኔታውም ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

| ተራ/ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | ጤና ቢሮ | 9,294 | 80 |
| 2 | ትምህርትና ባህል ቢሮ | 14,142 | 30 |
| | ድምር | 23,437 | 10 |

ይህም ሂሣብ ለውሎ አበል ተብሎ የተፈፀመ ክፍያ ሲሆን በመመሪያው መሠረት የውሎ አበል መፍቀጃና ማረጋገጫ ቅጽ ተሞልቶ ሣይቀርብለት የተፈፀመ ክፍያ በመሆኑ ሠራተኞች በመስክ ሥራ ላይ ለቆዩበት ጊዜ መከፈሉ ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና ለወደፊቱም በመመሪያው መሠረት የውሎ አበል ቅጽ እየተሞላ እንዲሰራ በላክነው ሪፖርት አሣስበናል፡፡

## 2.6. <u>ከደንብና ከመመሪያ ውጪ</u>

**<u>የተፈፀሙ ክፍያ ብር 14580.89</u>**

መ/ቤቶች የወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች ተከትለው ክፍያን የሚፈጽሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሁለት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያን ሣይጠብቅ የተፈፀመ ክፍያ ብር 14,580.89 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ተራ/ ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| 1 | ጤና ቢሮ | 9,689 | 45 |
| 2 | ውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ | 2188 | 24 |
| 3 | ግብርና ልማት ቢሮ | 1641 | 60 |
| 4 | ትምህርትና ባህል ቢሮ | 1061 | 60 |
| | ድምር | 14,580 | 89 |

ከዚህም ውስጥ ብር 8,069 አግባብ ባለው ባለሥልጣን ክፍያው እንዲፈፀም ሣይፈቀድ የተፈፀመ ክፍያ፣ መስክ ላልወጡ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበል፣ በብልጫ የተከፈለ የውሎ አበል፣ በድጋሚ የተከፈለ የውሎ አበልና፣ ከታሪፍ በላይ የተከፈለ የትራንስፖርት ሂሳብ እና ብር 182 ደግሞ የሠራተኛ ደመወዝ ከፋይናንስ ቢሮ ተጠይቆ ሳይመጣ ከሥራ ማስኬጃ የተከፈለ ነው፡፡ አሠራሩ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ መሆኑን ገልፀን አለአግባብ የተከፈለው ሂሣብ ተመላሽ እንዲሆን ለወደፊቱ ተመሣሣይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.7. <u>ደንብና መመሪያ ሳይጠብቅ</u>

<u>የተፈፀመ ግዥ ብር 3558.00</u>

በበጀት ዓመቱ የተከናወነው ግዥ በወጡት ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በክልሉ ግብርና ቢሮ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡ ድርጅቶች የብር 3558.00 የዕቃ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ አሰራሩ ከፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ እንዲታረም በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. <u>የንብረት ኦዲት</u>

3.1. የየቢሮዎቹ አላቂና ቋሚ ዕቃ በመንግሥት ንብረት አያያዝ መመሪያ መሠረት መያዙን በኦዲት ለማረጋገጥ ተሞክሮ፣

በግብርና ልማት ፣ በትምህርትና ባህል እና በውኃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮዎች፣

መዝገብ ያልተቋቋመና የንብረት ምዝገባ የማይከናወን በመሆኑ፣

ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ባለመስጠቱ፣

በጤና ቢሮ

በኦዲቱ ወቅት በሥራ ላይ የነበሩት የንብረት ክፍል ሠራተኛ ሥራውን ሲጀምሩ የንብረት ከወጪ ቀሪ ተረጋግጦ ርክክብ ባለመደረጉ

ኦዲት ለማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በመሆኑም አሠራሩ የመንግሥት ንብረት አያያዝ መመሪያን የሚጻረርና የየቢሮዎቹን ንብረት ለብክነት የሚዳርግ በመሆኑ ቢሮዎቹ በመመሪያው መሠረት በአፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

3.2. <u>ተሽከርካሪ መኪናዎች</u>

የቢሮዎቹ ተሽከርካሪ መኪናዎች ሁኔታ ሲጣራ፡-

በግብርና ልማት ቢሮ ፡-

16 ተሽከርካሪ መኪኖች ከባድ ብልሽት ደርሶባቸው ከ1-5 ዓመታት የቆሙ ሲሆን ቀደም ባለው ጊዜም ሪፖርት የተደረገበት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን፣

በጤና ቢሮ

7 ተሽከርካሪ መኪናዎች በብልሽት ምክንያት የቆሙ መሆኑን፣

በትምህርትና ባህል ቢሮ :–

5 የተለያዩ መኪናዎችና 5 ሞተር ሣይክሎች በብልሽት ምክንያት መቆማቸው፣

1 ተሽከርካሪ መኪና በመንግሥት ለውጥ ጊዜ የጠፋ መሆኑ፣

1 ተሽከርካሪ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ለጥገና አ.አ ተልኮ የኦዲቱ ሥራ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተመለሰ መሆኑ፣

ተበላሽተው ከቆሙት ሞተር ሳይክሎች የአንዱ ሞተር ቁጥር ሊብሬው ላይ ካለው የሞተር ቁጥር ጋር የማይገጥም መሆኑ፣

በውኃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ :–

4 የተለያዩ ተሽከርካሪ መኪኖች ከ1ወር–9 ዓመታት በብልሽት ምክንያት መቆማቸው፣

በብልሽት ከቆሙት ሁለቱ እና በኦዲቱ ወቅት አገልግሎት ላይ ከነበሩት አንዱ በድምሩ ሦስት ተሽከርካሪ መኪኖች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑ ታውቋል:

በመሆኑም በብልሽት ምክንያት የቆሙት ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ወይም በደንቡ መሠረት እንዲወገዱ ጉዳዩ ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት እንዲደረግ፤ ጋራዥ ገብቶ ያልወጣ ተሽከርካሪ እንዲወጣ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ፤ የጠፋው ተሽከርካሪ እንዲፈለግ፣ የሞተር ቁጥሩ የተለወጠው ሞተር ሣይክል ሁኔታ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ እና ሊብሬ ለሌላቸው ደግሞ ተገቢው ክትትል ተደርጎ መፍትሄ እንዲፈለግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 5. <u>የበጀት ሂሣብ</u>

በክልሉ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ እንዲሁም በበጀት ዓዋጁ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል።

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤቱ ስም | ከበጀት በላይ የወጣ | | ያልተሠራበት በጀት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የውኃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ | -- | | 3,085,566 | 24 |
| 2 | የግብርና ልማት ቢሮ | 20,581 | 44 | 1,705,240 | 72 |
| 3 | የጤና ቢሮ | -- | -- | 2,973,763 | 26 |
| 4 | የትምህርትና ባህል ቢሮ | 89,972 | 38 | 786,579 | 51 |
| | ድምር | 110,553 | 82 | 8,551,149 | 73 |

ከላይ እንደተመለከተው በሁለት መ/ቤቶች ከበጀት በላይ የወጣ ብር 110,553.82 እና በአራት መ/ቤቶች ያልተሠራበት በጀት ብር 8,551,149.73 መገኘቱ ተረጋግጧል:: ስለሆነም መ/ቤቶች የበጀት ዕቅዳቸው በበቂ ጥናት የተደገፈ እንዲሆን፣ አጠቃቀማቸውና አያያዛቸው የበጀት አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ተከትሎ እንዲፈፀም በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል::

6. <u>ልዩ ልዩ</u>

በውሃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ

- ርክክብ ያልተደረገለት የጥሬ ገንዘብ፤ የባንክና የሰነድ ሂሣብ ብር 617,681.61 የተገኘ መሆኑ፣

በግብርና ልማት ቢሮ

ርክክብ ያልተደረገለት ጥሬ ገንዘብ፣የባንክና የሰነድ ሂሣብ ብር 8,353.82 መገኘቱ፣

በባዶ (ልሙጥ) ቼኮች ላይ ተፈርሞ መገኘቱ፣

በትምህርት እና ባህል ቢሮ

- ሳይከፈል በወጪ ተመዝግቦ በገ/ሂ/29 የተያዘ የደመወዝ ሂሣብ ብር 26,832.00 መገኘቱ

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

አሠራሩ የመንግሥትን ገንዘብ ለብክነት የሚዳረግ መሆኑን ጠቅሰን አሠራሩ መታረም እንደሚገባው አሳስበናል::

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
## የሐረሪ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
## የ1993 በጀት ዓመት የድጋፍ ድጎማ
## ሂሳብ ኦዲት ውጤት

በ1993 በጀት ዓመት ከፌዴራል መንግሥት ለክልሉ የተመደበውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ልዩ ድጎማዎች በአዋጅ ቁጥር 68/1989 አንቀጽ (7/2) መሠረት ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ በሶስት መ/ቤቶች ሂሣብ ላይ ኦዲቱን አከናውኗል፡፡

መ/ቤቶቹም፡–

የክልሉ የትምህርት ቢሮ

የጤና ቢሮ

የፋይናንስ ቢሮ

ሲሆኑ፣ ኦዲት የተደረገው ሂሣብ ውጤትና አስተያየት በየአድራሻቸው የተላከ ቢሆንም በሪፖርቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት እና የተወሰደውን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው ሁሉም መ/ቤቶች መልስ ሣይሰጡ ቀርተዋል፡፡ በአጠቃላይ በአሰራርና በፋይናንስ ረገድ ከታዮት ድክመቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ተጠናቅረው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ</u>

አዲት በተደረገበት በሦስቱም ቢሮዎች የባንክ ሂሣብ ምዝገባ እና የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ በአግባቡ የማይዘጋጅ በመሆኑ ለወደፊቱ አሰራሩ በደንቡ መሠረት እንዲስተካከል በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

**1.2** <u>ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ብር 976,098.13</u>

የሰነድ ሂሣብ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ በተደነገገው መሠረት በወቅቱ የሚወራረድ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ :-

| | | |
|---|---|---|
| የጤና ቢሮ - - - - - - | ብር | 913,876.26 |
| የፋይናንስ ቢሮ - - - - | ብር | <u>62,221.87</u> |
| በድምሩ | ብር | <u>976,098.13</u> |

በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ የሰነድ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

በውዝፍ የተገኘው የሰነድ ሂሣብ እንዲወራረድና ለወደፊቱም በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ መሠረት ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

2.1 <u>ከባለዕዳዎች ያልተሰበሰበ ሂሣብ ብር 26,654.55</u>

በ1990 ዓ.ም የፋይናንስ ቢሮ የበጀት ክፍያና ሂሣብ መምሪያ ኦዲት ሲደረግ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 26,654.55 ከባለዕዳዎቹ ያልተተካ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም በፍ/ቤት ክስ በተመሰረተበት ጉዳይ ላይ ክትትሉ ተጠናክሮ ገንዘቡ እንዲተካ፣ ክስ ያልተመሠረተባቸው ጉዳዮች ደግሞ በአስቸኳይ እንዲመሰረት ተገቢው ክትትል መደረግ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

3.1. <u>የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ</u>

**<u>ያልተቻለ ሂሣብ ብር 8,532.00</u>**

በወጪ የተመዘገቡት ሂሣቦች በበቂና አስተማማኝ ማስረጃዎች የተደገፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ :-

በጤና ቢሮ - - - - - - - - ብር 1,600.00

- በትምህርት ቢሮ - - - - - - - ብር <u>6, 932.00</u>

በድምሩ ብር <u>8,532.00</u>

ተከፍሎ በወጭ የተመዘገበ ቢሆንም የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በጤና ቢሮ የተገኘው ብር 1,600.00 የተከፈለበት ቀንና በወጪ የተመዘገበበት የወጪ ቫውቸር ቁጥር ባለመጠቀሱ ማስረጃዎቹ ባለፉት ዓመታት በወጪ ያልተመዘገቡ ለመሆናቸው ማረጋገጥ አለመቻሉና፣ በትምህርት ቢሮ ደግሞ ለሴሚናር ተሳታፊዎች ተብሎ ለተከፈለው ብር 6,932.00 ተሳታፊዎቹ በሴሚናሩ ላይ በትክክል ለመሳተፋቸው የሚገልጽ ማረጋገጫ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

በመሆኑም ጉዳዩ ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና አሰራሩም እንዲታረም በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2. <u>የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሣቦች ደጋፊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

በትምህርት ቢሮ - - - - - - ብር 1,797,497.58

በጤና ቢሮ - - - - - - 3,695,279.22

በድምሩ 5,492,776.80

ሕጋዊ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈፀም ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግና በወጪ ለተመዘገበውም ሂሣብ ትክክለኛ ማስረጃ እንዲቀርብለት ወይም ጉዳዩ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3. ያለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ ብር 59,078.95

በበጀት ዓመቱ የተፈፀመው ክፍያ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ በደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:-

በትምህርት ቢሮ - - - - - - - - ብር 56,824.20

በጤና ቢሮ - - - - - - - - - <u>2,254.75</u>

በድምሩ <u>59,078.95</u>

ያለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተመለከተው ያለአግባብ የተፈፀመ ሂሣብ ውስጥ በብልጫ የተከፈለ ሂሣብና በባለሥልጣን ሳይፈቀድ የተፈፀመ ክፍያ ይገኙበታል፡፡

በመሆኑም አሰራሩ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ያልተከተለ በመሆኑ እንዲታረምና ያለአግባብ በተከፈለውም ሂሣብ ላይ ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4. <u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ ብር 1,338,078.78</u>

በወጪ የተመዘገበው ሂሣብ የተሟላ ማስረጃ የቀረበለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ

በፋይናንስ ቢሮ - - - - - - - - - ብር 1,328,307.60

በጤና ቢሮ 9,771.18

በድምሩ 1,338,078.78

የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
በቀረበው ሂሣብ ላይ ያልተሟላውን ማስረጃ ለመጥቀስ ያህል የጥገና መጠየቂያ ያልቀረበለትና የገንዘብ ከፋይ ፊርማ የሌለው የሚሉት ይገኙበታል፡፡
ስለሆነም ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ማስረጃዎች የተሟሉ መሆናቸው መረጋገጥ እንዳለበት በላክናቸው ሪፖርቶች አስገንዝበናል፡፡

3.5. <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ሂሳብ ብር 250,272.50</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዙት ዕቃዎች በሙሉ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በክልሉ ጤና ቢሮ በብር 250,272.50 የተገዛ ዕቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የሆነበት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጭ ተመዝገቦ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የተገዛው ዕቃ ለመ/ቤቱ አገልግሎት የዋለ ለመሆኑ የንበረት ገቢ ደረሰኝ እንዲቀርብ፣ካልሆነም ለግዥ የወጣው ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባ ጉዳዩም በውስጥ ኦዲት በኩል ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

ቢሮዎች የተመደበላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና በበጀት ዓዋጁ መሠረት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

| ተ.ቁ | የመ/ቤቱ ሥም | ያልተሠራበት በጀት | | ከበጀት በላይ የወጣ | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ትምህርት ቢሮ | 4,110,641 | 68 | -- | -- |
| 2 | ጤና ቢሮ | 9,015,215 | 53 | 47,711 | 38 |
| | ድምር | 13,125,857 | 21 | 47,711 | 38 |

በሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ብር 13,125,857.21 እና ከበጀት በላይ የወጣ ብር 47,711.38 ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የመ/ቤቶቹ የበጀት አቀራረብ በበቂ ጥናት የተደገፈና ሊተገበር የሚችል መሆን እንዳለበት፣ በበጀት ዓዋጅ ከተፈቀደው በጀት በላይ ሥራ ላይ ማዋልም የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብን ያልተከተለ በመሆኑ ለወደፊቱ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

5. <u>የንብረት ኦዲት</u>

ቋሚና አላቂ ዕቃዎች በአግባቡ መመዝገባቸውንና ከወጪ ቀሪውም ትክክለኛ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፡-

5.1. <u>የትምህርት ቢሮ</u>

ብር 110.60 የሚያወጡ አላቂ ዕቃዎች በጉድለት እና ብር 24.89 የሚያወጣ የታይፕ ወረቀት ደግሞ ብልጫ መገኘቱ፣

የአንድ ተሽከርካሪ በሊብሬውና በተሽከርካሪው አካል ላይ ባለው የሻንሲ ቁጥር ላይ ልዩነት መኖሩ፣

በተሽከርካሪ ስምሪትና በነዳጅ አጠቃቀም ላይ ተገቢው ቁጥጥር አለመደረጉ፣

በብልሽት ምክንያት ከ5 ዓመት በላይ የቆሙ ተሽከርካሪዎች መገኘታቸው፣

የሚሉት ዋናዋናዎቹ ሲሆኑ የተጠቀሱት ጉዳዮች እንዲታረሙና ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የጤና ቢሮ</u>

የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ያለመቋቋሙ፣

- ዕቃዎች በዓይነታቸው ተለይተው በአግባቡ ያልተቀመጡ መሆኑ፣

- በተሽከርካሪዎች ስምሪትና በነዳጅ አጠቃቀም ላይ ተገቢው ቁጥጥር አለመደረጉ፣

በዓመቱ መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ያለመከናወኑ እና ሦስት ተሽከርከሪዎች በቀላልና ከባድ ብልሽት ምክንያት ለረዥም ጊዜ ያለአገልግሎት መቀመጣቸውና አንድ ተሽከርካሪ ደግሞ ሊብሬ የሌለው መሆኑ፣

ታውቋል። በመሆኑም ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱት ድክመቶች እንዲታረሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

## 6. ልዩ ልዩ

### 6.1. የፋይናንስ ቢሮ

የቢሮው የአስተዳደር መምሪያና ሂሣብ መምሪያ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጥሬ ገንዘብና የሠነድ ሂሣብ ቆጠራ ያለመደረጉና የመዝገብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት አለመረጋገጡ፣

- ለኦዲት የቀረበው መዝገብ ሥርዝ ድልዝ የበዛበት መሆኑ፣ የወጪ ማስረጃዎችና ሰነዶች በገንዘብ ያዥ እጅ የሚጠበቁ መሆኑ፣ የወጪ ማስመስከሪያ /ቫውቸሮች/ ቁጥር አሰጣጥ እና የሂሣብ ምዝገባ የተዘበራረቀና ቅደም ተከተሉን ያልጠበቀ ሆኖ መገኘቱ፣

### 6.2. የጤና ቢሮ

ባለፉት ዓመታት የኦዲት ሪፖርት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሣብና አስተያየት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

- የሰራተኞች የግል ማህደር በፔርሶኔል ክፍል የማይጠበቅ መሆኑ፣
- የዓመት ፈቃድ መከታተያ መዝገብ ያለመቋቋሙ፣
- የተበላሸ ደረሰኝ ቁጥሩ በመዝገብ የማይመዘገብ መሆኑ፣

### 6.3. የትምህርት ቢሮ

- ግለሰቦች ያቀረቡት የፋክቱር ብዛት በወጪ ማስመስከሪያ ላይ የማይገለጽ መሆኑ፣

- በቻናል 2 ወጪ የሚደረግ የዕርዳታ ሂሣብ ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ የአሰራር ድክመቶች ሲሆኑ፣ ከላይ በዝርዝር እንደተገለፀው በሦስቱም ቢሮዎች የተጠቀሱት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲታረሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡